‹‹አንዱ መንግስት ሄዶ ሌላኛው ሲመጣ እያፈረሱ መገንባት ብዙ ነገር አሳጥቶናል››

- አቶ በላይ ገብረ ፃድቅ
የቀድሞ የመረጃና ደህንነት ባለሙያ እና ዲፕሎማት



ገጽ 6

ኩፍኝና አሁናዊ ደረጃው

ገጽ 8


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 323 ሐምሌ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# መንግስት ከሕወሓት ጋር የሚያደርገው የሠላም ንግግር በጥንቃቄ ሊያዝ እንደሚገባ ተገለፀ

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ሲል ከሕወሓት ጋር ለማድረግ ያቀደውን የሠላም ንግግር በጥንቃቄ ሊያዝ እንደሚገባ የቀድሞ የመረጃና ደህንነት ባለሙያና ዲፕሎማት አቶ በላይ ገብረ ፃድቅ አስታወቁ፡፡

አቶ በላይ ገብረፃድቅ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ መንግስት በተለይም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን እያደረገ ያለው ጥረትና ለሰላም ያለው ቁርጠኝነት የሚደነቅ ነው፡፡ በአንጻሩ ሕወሓት በውጭ ሃይሎች እየተገፋ በየጊዜው አቋሙን የሚለውጥበት ሁኔታ በመኖሩ መንግስት ከሕወሓት ጋር የሚያደርገውን የሠላም ንግግር በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል፡፡

‹‹እንደ አንድ ለአገሩ የሚያስብ ሰው ጦርነቱ ሙሉ ለሙሉ ቆሞ መላው ህዝብ በሰላም እንዲኖር ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ ያሉት አቶ በላይ፤ ሕወሓት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ በመነጋገር መፍታት እየቻለ አገሪቱን የበለጠ ችግሩ ውስጥ መክተቱም ከታሪክ ተወቃሽነት እንደማያድነው አስረድተዋል፡፡

‹‹ባለመደራደር ብዙ የሚታጣ ነገር አለ፡፡ የሰው ህይወት በከፍተኛ ደረጃ ይጠፋል፤ ኢኮኖሚ ይወድማል፤ ሰብአዊ ቀውሱም በቀላሉ የሚታይ አይደለም›› የሚሉት ዲፕሎማቱ፤ በጦርነቱ ምክንያት እየደረሰ ያለውን አገራዊ ኪሳራም ሆነ የችግሩ ዋነኛ ገፈት ቀማሽ ህዝቡ በመሆኑ ጉዳዩ

መንግሥት ከሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ፡- ሃዲሽ አብርሃ

አቶ በላይ ገብረፃድቅ









# በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር እስካሁን ከ5 ነጥብ 3 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ተተክለዋል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከተያዘው እቅድ ውስጥ መርሀ ግብሩ ሳጠይጠናቀቅ እስካሁን ከአምስት ነጥብ ሦስት ቢሊየን በላይ ችግኞችን መትከል እንደተቻለ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በዘንድሮው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ከደንብና መመሪያ ውጪ 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል”

- ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ከደንብና መመሪያ ውጭ 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉን የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ ገለጹ። ወደ አንድ ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብም ከግለሰቦች ኪስ ወደ መንግስት ካዝና እንዲመለስ መደረጉንም አመልክተዋል።

ዋና ኦዲተሯ ወይዘሮ መሠረት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ውስን ሀብት ያለበት አገር ውስጥ የተመደበው በጀት ከታለመለት ዓላማ ውጪ ያለ አግባብ ወጪ ማድረግ በአገር ላይ የሚያሳድረው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ከፍተኛ ነው። በቂ መረጃና ማስረጃ ሳይኖር ወጪ የሚደረግ የህዝብ ሀብት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። በተለያዩ የመንግስት ተቋማት 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር በላይ ከደንብና መመሪያ ውጪ ወጪ ተደርጓል።

“በተለያዩ የመንግስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









ገጽ 10

ቀልድ የጠራው ሞት



ዜና



## ሰርጎ ለመግባት የሞከረው አልሸባብ የሽብር ቡድን ዳግም ከፍተኛ ኪሳራ ተከናንቦ ወደ መጣበት ተመልሷል

**- ሜጀር ጀኔራል ተስፋዬ አያሌው**

አዲስ አበባ፡- ወደ ኢትዮጵያ ሰርጎ ለመግባት የሞከረው የአልሸባብ የሽብር ቡድን በጸጥታ ኃይሉ በተወሰደበት እርምጃ ዳግም ከፍተኛ ኪሳራ ተከናንቦ ወደ መጣበት መመለሱን የመከላከያ ኃይል ስምሪት ኃላፊና ጊዜያዊ የፀጥታ ኮማንድ ፖስት አስተባባሪ ሜጀር ጀኔራል ተስፋዬ አያሌው ተናገሩ።

ሜጀር ጀኔራል ተስፋዬ ለኢዜአ እንደተናገሩት፤ ባለፉት ቀናት ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል ጋር በመቀናጀት በተወሰደው እርምጃ የሽብር ቡድኑ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ያዘጋጃቸውን የትጥቅና ስንቅ ዴፖዎች ማውደም ተችሏል፡፡

ነገር ግን የሽብር ቡድኑ ዛሬ ሌሊት ላይ የተበታተነ ኃይሉን በማሰባሰብ ኢትዮጵያና ሶማሊያ በሚዋሰኑበት አካባቢ ወደ ሀገር ውስጥ ሰርጎ በመግባት ጥቃት ለመፈጸም መሞከሩንም ሜጀር ጀኔራሉ ተናግረዋል፡፡

ሆኖም የጸጥታ ኃይሉ በወሰደው እርምጃ የሽብር ቡድኑ ዳግም ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራዎችን ተከናንቦ ወደ መጣበት መመለሱን አብራርተዋል።

እስካሁን ባለው መረጃም ከ150 በላይ የሽብር ቡድኑ አባላት መደምሰሳቸውንና የሽብር ቡድኑ ለአጥፍቶ መጥፋት ያዘጋጃቸው ተሽከርካሪዎች መውደማቸውን እና የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች እንደተማረኩ ገልፀዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የመከላከያ ሰራዊትና ጥምር የፀጥታ ኃይሉ የሽብር ቡድኑን ትንኮሳዎች ለመመከት በሙሉ ቁመና ላይ መሆኑን የጠቀሱት ሜጀር ጀኔራል ተስፋዬ፤ የሶማሌ ክልል ህዝብ ለመከላከያ ሰራዊቱና ለክልሉ ልዩ ኃይል ያለውን ደጀንነት በተግባር እያሳየ መሆኑን ጠቁመዋል።

የመከላከያ ሰራዊትና የሶማሌ ክልል ልዩ ኃይልን ጨምሮ የፀጥታ ኮማንድ ፖስቱ በአካባቢው የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለመድፈር በሚሞክር የትኛውም ኃይል ላይ እርምጃ ለመውሰድ በተጠንቀቅ ላይ መሆኑንም አረጋግጠዋል፡፡

የሶማሌ ክልል መስተዳደር ሰኞ ዕለት ሐምሌ 18/2014 ዓ.ም. እንዳሳወቀው የክልሉ ልዩ ኃይል "ዳግም ድንበር አቋርጦ ለመግባት እየሞከረ ያለውን የአልሸባብ ታጣቂ ቡድን መደምሰሱን ገልጿል።

የአልሻባብ ታጣቂዎች ከአጎራባች ሶማሊያ ሂራን ግዛት ተነስተው ድንበር በማቋረጥ ኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ሸበሌ ዞን ፌርፌር ወረዳ ለመግባት እንደሞከሩና የሽብር ቡድኑ ኤል ቁዱን በሚባል ቦታ ላይ በተደረገ ውጊያ መመታቱን አመልክቷል።

ክልሉ እንዳለው በዚህ ውጊያ ከተገደሉት በተጨማሪ በርካቶች መማረካቸውን እንዲሁም የጦር እና የመገናኛ መሣሪያዎች መያዛቸው ተነግሯል።

የሶማሌ ክልል ልዩ ኃይል ባለፉት ቀናት በበርካታ መኪኖች የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግረው ከገቡት የአልሻባብ አባላትን ጋር ተዋግተው በርካታ የሽብር ቡድኑ አባላት መግደላቸውን ተገልፆ ነበር።

# የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎትን ውጤታማ ለማድረግ በፖሊሲ የተደገፈ ሥራ እየተሰራ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**




አዲስ አበባ፡- የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎትን ውጤታማ ለማድረግ በፖሊሲ የተደገፈ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የቻካ ዲጂታል ፋይናንሺያል ሰርቪስ አክሲዮን ማህበር የሞባይል ገንዘብ አገልግሎት ለመስጠት በ200 ሚሊዮን ብር የተፈቀደ ካፒታል ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ማግኘቱን አስመልክቶ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት የትውውቅ መርሃግብር አካሂዷል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ የትውውቅ መርሃግብሩ ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ለዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ትኩረት በመስጠትና በዘርፉ የሚሰማሩ አካላትን በማበረታታት ለአገር ኢኮኖሚያዊ ዘላቂ እድገት አጋዥ እንዲሆኑ እየተሰራ ነው። በተለምዶ ከምናውቃቸው የንግድ ዘርፎች በተጨማሪ ቀጣይነት ባላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ለመሰማራት ያሉት አማራጮችን ጥናት በማድረግ አዋጭነታቸውን በመገምገም በፖሊሲ የመደገፍ ስራ እየተሰራ ነው።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከብሔራዊ ባንክና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የዲጂታል ግብይትን ለማሳደግ ፖሊሲ እየቀረጸ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ፍኖተ ካርታን በመቅረጽና በቴክኖሎጂ ግብይት የሚሰማሩ ድርጅቶችን ፈጠራ የታከለበት የቁጥጥርና የድጋፍ ስራ በመስራት አገልግሎቱ ውጤታማ እንዲሆን እየተደረገ ነው ብለዋል።

የቻካ ዲጂታል ፋይናንሻል ሰርቪስ አክሲዮን ማህበር በኢትዮጵያዊያን የተመሰረተ በመሆኑ ወደፊት አገራችን በዲጂታል ፋይይናንስ ክፍያ ረገድ የተቀላጠፈ ግብይትን በማስፋት ውጤታማ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የአገሪቱ የግል ዘርፍ ከተለመዱት የንግድ ስምሪቶች ባሻገር በዲጂታል አሠራሮች መታገዝ አለበት ያሉት ሚኒስትሩ ዶክተር በለጠ፤ ካቻ ፋይናንሻል ሰርቪስ ወደ ዘርፉ መቀላቀሉ ሌሎች ኩባንያዎችን የሚጋብዝ ሁኔታ እንደሚፈጥር ተናግረዋል። እንዲሁም የገንዘብ ዝውውር ተደራሽነትንና አካታችነትን በማቀላጠፍ ለአገር ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን ገልጸዋል።

የቻካ ዲጂታል ፋይናንሺል ሰርቪስ አክሲዮን ማህበር ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ አብርሃም ጥላሁን እንደገለጹት፤ ካቻ የሞባይል ገንዘብ ዝውውር አገልግሎት የስራ ፈቃድ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በማግኘት ከግሉ ዘርፍ የመጀመሪያው የዲጂታል ፋይናንስ ኩባንያ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ስራ አስኪያጁ ገለጻ፤ ኩባንያው ያልተለመዱ የፋይናንስ አሠራሮችን በመተግበር ከፋይናንስ ስርአት ውጪ ያሉ ዜጎችን ያገለግላል። ካቻ ፋይናንሻል ሰርቪስ በቂ ልምድ ያላቸውን ሰራተኞች በመያዝ በጥናት ላይ የተመሠረተ ችግር ፈቺ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ይሰጣል ብለዋል።

የፋይናንስ ተደራሽነት እየጨመረ ቢመጣም አንድ ቅርንጫፍ በአማካኝ ለ12 ሺህ ሰዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ በመሆኑ በዘርፉ ያለውን ከፍተኛ ክፍተት ለመሙላት የቻካ ዲጂታል ፋይናንሺያል ሰርቪስ በቅርቡ ወደ ስራ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

ካቻ ፋይናንሺያል ሰርቪስ በ13 ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች የተመሠረተ ኩባንያ መሆኑ ታውቋል።

# በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ ባለሃብቶች የሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት አድርገው ሲሰሩ እንደሚገባ ተጠቆመ

**መሳኩ ኤሮሴ**



አዳማ፡- በቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ከህንጻዎች እና መሰረተ ልማቶች ግንባታ ጎን ለጎን ብቁ የሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት አድርገው ሊሰሩ እንደሚገባ ተጠቆመ፡፡

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከኤን ሲአር(NCR) እና ፈርስት ኮንሰልት( First consult) ጋር በመተባበር ሲያሰለጥናቸው ለነበረው 729 የአዳማ ከተማ የሆቴል ባለሙያዎች ሰርተፊኬትና እውቅና ተበርክቶላቸዋል።

የኢፌዴሪ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በሰርተፊኬት እና እውቅና አሰጣጥ ፕሮግራም ላይ እንደተናገሩት፤ የኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ የቱሪዝም ሀብት ያለበት ቢሆንም የሰው ሀብት ልማት ላይ የተሰራው ስራ ውስን በመሆኑ ከዘርፉ የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም፡፡ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ ጎን ለጎንም የሰው ሀብት ልማት ላይ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል።

ከዚህ ቀደም በአውሮፓና በአሜሪካ ተንጠልጥሎ የነበረው የቱሪዝም ዘርፍ ፊቱን ወደ አፍሪካ፣ እሲያ እና ደቡብ አሜሪካ እያዞረ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ስለሺ፤ ሀገሪቱ ከዚህ ዘርፍ የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ መሆን የሚትችለው የሰለጠነ የሰው ሀይል ማፍራትና ለቱሪስቶች ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ስትችል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በቱሪዝም ዘርፍ የሰለጠነ የሰው ሀይል ለማፍራት ጥረት ሲደረግ እንደነበር የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤በዘርፉ ለተሰማሩት ባለሙያዎች በየጊዜው ስልጠናዎች እየተሰጡ መቆየታቸውን አንስተዋል፡፡ ሆኖም ዘርፉ ከሚፈልገው አንጻር እጅግ አነስተኛ መሆኑን ነው የጠቆሙት፡፡ ሰሞኑን በኦሮሚያ እና በሀገር ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ በርካታ ባለሙያዎች ስልጠና አጠናቀው ሰርተፊኬት እና እውቅና ማግኘታቸውን እንደ መልካም ጅምር አንስተዋል፡፡

የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሰዓዳ ኡስማን በፕሮግራሙ ላይ እንዳሉት፤ ከቱሪዝም ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ ከፍ ለማድረግ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎችን አቅም ማሳደግ ወሳኝ በመሆኑ ስልጠናው ተዘጋጅቷል።

ሰልጣኞች በስልጠናው ያገኙትን እውቀትና ክህሎት ተጠቅመው በየተቋሞቻቸው የሚመጡትን ደንበኞች በአግባቡ በማስተናገድ ለከተማዋና ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ አስተላልፈዋል። ቢሯቸው አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግም ቃል ገብተዋል።

በስልጠናው ላይ አንድ ሪዞርት እና 34 ሆቴሎች ባለሙያዎቻቸውን ያሳተፉት ሲሆን፤ ስልጠናው ምግብና መጠጥ አቀራረብ፣ ምግብና መጠጥ አዘገጃጀት፣ ደንበኛ አያያዝ እና ሌሎች ወሳኝ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መሆኑ ተገልጿል፡፡ እውቅናና ሰርተፊኬት ከተበረከተላቸው የሆቴል ሰራተኞች መካከልም 533ቱ ሴቶች ናቸው፡፡ ስልጠናው በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ አስተዋፅኦ ላበረከቱ አካላትም ሰርተፊኬትና እውቅና ተበርክቶላቸዋል።

ስልጠናውን አጠናቀው ሰርተፊኬት የወሰዱት ባለሙያዎች ስልጠናው ለስራቸው አጋዥ መሆኑን ጠቁመው፤ መሰል ስልጠናዎች በየጊዜው ሊሰጥ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

ተመሳሳይ ስልጠና በቢሾፍቱ ከተማ እየተሰጠ መሆኑን የጠቆሙት የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሁንዴ ከበደ፤ በቀጣይም መሰል ስልጠናዎች በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ከተሞች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች መስጠቱ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል፡፡

# የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ከእያንዳንዱ ፈጣን መልእክት አንድ ብር ለመቄዶንያ ለመስጠት ወሰነ

## • ማዕከሉ የተረጂዎችን ቁጥር ወደ 20ሺ ለማሳደግ መወሰኑን ገለጸ

**ዘላለም ግዛው**




አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ከእያንዳንዱ ፈጣን መልእክት አንድ ብር እየተቆረጠ ለመቄዶንያ ለመስጠት ወሰነ፡፡መቄዶንያ በየአካባቢው ቅርንጫፎቹን በማስፋት 24 ለማድረስ፣ የተረጂዎቹን ቁጥርም ወደ20 ሺህ ለማሳደግ እየሰራ እንደሚገኝ አመልክቷል፡፡

አገልግሎቱ ለመቄዶንያ አረጋውያንና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል ቃል በገባው መሰረት አንድ ሚሊዮን ብር ቼክ አስረክቧል፡፡ በርክክቡ ወቅት ሰራተኞቹና አመራሩ በማዕከሉ ከሚገኙ ሰባት ሺህ 500 ከሚደርሱ አረጋውያን ጋር ማዕድ ተጋርተዋል፡፡

የፖስታ አገልግሎት ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ሃና አርአያስላሴ በማዕከሉ እየተሰራ ባለው የጽድቅ ስራ በመሳተፋቸው ትልቅ ክብር እንደተሰማቸው ገልጸው፤ተቋማቸው ከሐምሌ ወር 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከእያንዳንዱ ፈጣን መልእክት አንድ ብር ለመቄዶንያ ገቢ ለማድረግ መወሰናቸውን ጠቁመዋል፡፡

‹‹የሁላችን ኃላፊነት የሆነውን የወደቁና የተረሱ ሰዎችን አንስቶ ማክበር ትልቅ ነገር ነው፡፡ በእዚህ እየረዳችሁን ያላችሁት እናንተ ናችሁ እንጂ እኛ አይደለንም፡፡ በስራው እየተሳተፋችሁ ያላችሁ ሁሉ ልትመሰገኑ ይገባል›› ብለዋል፡፡

የአገልግሎቱ ሰራተኛ ማህበር በወሰነው መሰረት ሰራተኞች ከ10 ብር ጀምሮ በየወሩ ከደመወዛቸው ተቆራጭ በማድረግ ለማዕከሉ ገቢ ይሆናል፡፡ በአመራሩ ውሳኔ መሰረትም የማዕከሉን መልእክቶች በነጻ የማድረስ ኃላፊነትን ወስደናል ብለዋል ወይዘሮ ሃና፡፡

ከአንድ ወር በፊት ባደረጉት ጉብኝት ለስራው መስፋፋት ሃብት እንደሚያስፈልግ መገንዘባቸውን በመጠቆምም፤ ከማዕከሉ ጋር የሚኖረው አጋርነትና ድጋፍ እንደሚቀጥልም አመልክተዋል፡፡

በየእለቱ ይህንን ያህል ሰው መመገብ ትልቅ ኃላፊነት ነው፤ እየተሰራ ያለውን መልካም ስራ በማስተዋወቅ ተቋማት ማዕከሉን እንዲደግፉ ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡም ቃል ገብተዋል፡፡

የመቄዶንያ መስራች አቶ ቢንያም በለጠ በበኩላቸው፤ የአገልግሎቱ አመራርና ሰራተኞች በመቄዶንያ በመገኘት ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት አንድ ሚሊዮን ብር ለመስጠት ቃል ገብተው እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ ጊዜ ሰጥተው ከአረጋውያን ጋር በማሳለፋቸው ሊመሰገኑ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

ከአንድ ሚሊዮን ብር ልገሳው በተጨማሪ በማዕከሉ ለሚገኙ የምሳ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ማዕድ መጋራታቸው ለማዕከሉ የሰጡትን ትኩረት እንደሚያሳይ ጠቁመዋል፡፡

የፖስታ አገልግሎት ድርጅት ኃላፊ ወይዘሮ ሃና የመቄዶንያ አምባሳደር ሆነዋል፣ የትም ስፍራ ተወካያችን ሆነው የማዕከሉን አላማ በመደገፍ ከጎናችን እንዲቆሙ አደራ ጥለናል፤ ይህንን ኃላፊነት እንደሚወጡም እንተማመናለን ብለዋል፡፡

የድርጅቱ ሰራተኞች ሌላ ቦታ ከማሳለፍ ይልቅ ለራሳቸው፣ ለቤታቸውና ለልጆቻቸው መንፈሳዊ በረከት በሚያስገኝ ስፍራ መርጠው በመገኘታቸው ሊኮሩ ይገባቸዋል፡፡

ራሳቸውን ችለው መንቀሳቀስና መመገብ የማይችሉ አረጋውያንንና አዕምሮ ሕሙማንን ከተለያዩ ከተማ ጎዳናዎች ላይ በማንሳት ከአዲስ አበባ በተጨማሪ፤ በደሴ፣ ድሬዳዋ፣ ጎሬ፣ አዳማ፣ ሐረር፣ በኬ፣ ጋምቤላ አዳዲስ ቅርንጫፎች በመክፈት ስራ መጀመሩን ተናግረዋል፡፡

ማዕከሉን ለማገዝ አዲስ አበባ መምጣት ሳያስፈልግ በቅርበት የሚገኙ ማዕከላትን ማገዝ እንደሚቻልም ነው የተናገሩት፡፡ የመጠለያ፣ የምግብ፣ የልብስ፣ የሕክምና አገልግሎትና ቤተሰባዊ ፍቅር በመስጠት ደጋፊና ጧሪ የሌላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚደረገው ድጋፍ በአዳዲስ አካባቢዎች የሚቀጥል መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በቀጣይ በአማራ ክልል ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ደብረብርሃን፣ በኦሮሚያ ክልል ሻሸመኔ፣ ወሊሶ፣ አምቦ፣ መቱ በደቡብ ክልል ወላይታ ሶዶ፣ ሆሳዕና፣ አርባምንጭ፣ ኮንሶ፣ ዲላ፣ ወልቂጤ፣ በሲዳማ ክልል ሐዋሳ፣ በሶማሌ ክልል ጂግጂጋ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በአፋር ክልሎች አሶሳና ሰመራ በቅርቡ ለመጀመር እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ማዕከሉ ቅርንጫፎቹን እያስፋፋ እንደሚገኝና በቀጣይ ወደ 24 ለማድረስ እየሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡ ምንም አይነት የውጭ ርዳታ የሌለው ማዕከሉ ከአገር ውስጥ ከሚሰበስበው ገንዘብ አረጋውያንና የአእምሮ ህመምተኞችን ሰብስቦ በማኖር እየመገበ፣ ህክምና እንዲያገኙ እያደረገና ህንጻ ግንባታ እያከናወነ መሆኑንም ነው የተናገሩት፡፡ ለስራው በጸሎት፣ በአይነትና በገንዘብም ሁሉም በሚችለው እንዲያግዝም ጠይቀዋል፡፡

ተረጂዎች መንፈሳዊ ፍላጎታቸውንም ለማሟላት ሙስሊሞች ሐጅ እንዲያደርጉ፣ ኦርቶዶክሶች እስራኤል ተጉዘው እንዲሳለሙ ማድረግ ደረጃ ደርሰናል፡፡ በሽተኞችና ደሃዎች የሚያርፉበት፣ አረጋውያን ክብራቸው ተጠብቆ በእድሜያቸው ተከብረው የሚኖሩበት መሆኑ ያስደስተኛል ብለዋል አቶ ቢኒያም፡፡

የአረጋውያኖች ተወካይ አቶ ተከስተብርሃን መንክር በጉብዝና ጊዜያቸው በተለያየ ሙያ አገር ማገልገላቸውንና በአሁኑ ጊዜም በማዕከሉ እንደሚገኙና ማዕከሉ በቀን ሶስቴ እየመገበ እንደሚገኝም አንስተዋል፡፡

‹‹ድርጅቱ ከወደቅንበት በማንሳት በክብር እንድንኖር በማድረጉ እናመሰግነዋለን፣ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅትም ሃሳቡን በመደገፍ ላደረገው ድጋፍ ምስጋና እናቀርባለን›› ብለዋል፡፡ በአገር ሰላም እንዲሰፍን መጸለይ እንደሚገባ፣ በሃይማኖት፣ በዘር መከፋፈልን በመተው ለአገር ልማት መተባበር እንደሚገባም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ዓለም አቀፉ የነፍስ አድን ድርጅት በኦሮሚያ ለ150 ሺህ ዜጎች ድጋፍ ማድረጉን አስታወቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**



ሮቤ፡- በኦሮሚያ ክልል በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ለችግር ለተጋለጡ ከ150 ሺህ በላይ ዜጎች ድጋፍ ማድረጉን ዓለም አቀፉ የነፍስ አድን ድርጅት /IRC/ አስታወቀ።

ድርጅቱ በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን ደሎ መና ወረዳ ለሁለት ሺህ 40 አባወራዎች 183 ሺህ ዩሮ የሚያወጡ የተለያዩ የሰብዓዊ ድጋፎችን አድርጓል።

የዓለም አቀፉ የነፍስ አድን ድርጅት የአዳማ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት የአስቸኳይ ጊዜ ርዳታ ምላሽ ሥራ አስኪያጅ አቶ አብዲሳ መሐመድ እንዳስታወቁት፤ ከፌዴራል መንግሥትና ከክልሉ ጋር በመተባባር ከ150 ሺህ በላይ ለሆኑ ዜጎች ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

በኦሮሚያ ክልል በድርቅ፣ በጎርፍ አደጋና በተለያዩ ተፈጥሯዊ ምክንያቶች እንዲሁም በፀጥታ ችግር ምክንያት ሰዎች ለችግር ይጋለጣሉ። በዚህ ወቅት ድርጅቱ አስፈላጊውን የሰብዓዊ ርዳታ ድጋፎችን በማቅረብ ችግሮችን በጋራ ለማለፍ የሚደረገውን ጥረት እየደገፈ ይገኛል ብለዋል።

የዓለም አቀፉ የነፍስ አድን ድርጅት በተለያዩ ክልሎች ቅርንጫፍ ማስተባበሪያዎች አቋቁሞ እየሰራ መሆኑን የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ በኦሮሚያ ክልልም በተለያዩ ወረዳና ቀበሌዎች ላይ በመጠለያዎች ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች የጤና፣ የውሃ አቅርቦት፣ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በክልሉ በተለይም በባሌ ዞኖች፣ በምዕራብና ምስራቅ አርሲ ዞኖች፣ በሐረርጌ ዞኖች፣ በጉጂ ዞን ፣ በምስራቅ ሸዋና በወለጋ እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የነፍስ አድን ጥረቶችን በማከናወን የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን አቶ አብዲሳ ገልጸዋል።

ድርጅቱ ከነፍስ አድን ሥራዎች ባለፈ የማህበረሰቡን ኢኮኖሚ ለማጠናከር ጥረት እንደሚያደርግ ጠቁመው፤ የሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች እንዳሉም ተናግረዋል።

በተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ቤት ንብረታቸውን ላጡ ዜጎችም ድርጅቱ ገንዘብና የተለያዩ ቁሳቁሶችን በቀጥታ በማቅረብ ከችግር እንዲወጡ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በጋራ እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ አቶ አብዲሳ ገለጻ፤ በቅርቡም ድርጅቱ ከመንግሥት የረቀበውን የድጋፍ ጥሪ ተከትሎ አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት በፀጥታ ምክንያት ከአጎራባች ወረዳዎች ለተፈናቀሉ ዜጎች የተለያዩ ርዳታዎችን አቅርቧል።

በተለይም በኦሮሚያ ክልል ባሌ ዞን ደሎ መና ወረዳ ለሚገኙ ለሁለት ሺህ 40 አባወራዎች 183 ሺህ ዩሮ የሚያወጡ የተለያዩ የሰብዓዊ ድጋፎችን ማድረሱን አስታውቀዋል።

በድጋፉም 16 ዓይነት ድጋፎችን ለእያንዳንዱ አባወራ እንዲዳረስ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብርድ ልብሶች፣ የንጽህና መጠበቂያዎች፣ የተለያዩ ማብሰያ ዕቃዎች፣ አጎበር፣ ለጊዜያዊ መጠለያዎች የሚውሉ የፕላስቲክ ንጣፎች ፣ የጸሃይ ኃይል ብርሃን የሚሰጡ ዕቃዎች እንደሚገኙበት ጠቁመዋል።

ድጋፉ የቀረበላቸው አባወራዎች ምስጋናቸውን አቅርበው፤ ከተለያዩ ወገኖች ተጨማሪ ድጋፍ እንዲቀርብላቸው ጥሪ አቅርበዋል።

በተለይም የመድኃኒትና የዘላቂ መጠለያ አቅርቦቶች ካልተመቻቸላቸው የከፋ ችግር ውስጥ ሊወድቁ እንደሚችሉ ስጋታቸውን አስቀምጠዋል።

ዓለም አቀፉ የነፍስ አድን ድርጅት /IRC/ ዋና ጽህፈት ቤቱን አሜሪካ ላይ ያደረገ ሲሆን፣ በኢትዮጵያም ከኦሮሚያ በተጨማሪ በሶማሌ፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦችና በሌሎችም ክልሎች እየሰራ እንደሚገኝ ታውቋል።

# ኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክርን በስኬታማነት ካጠናቀቁ ሀገራት ልምድ መውሰድ እንደሚገባት ምሁራን ገለፁ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን ሀገራዊ ምክክርን በስኬታማነት ካጠናቀቁ ሀገራት ልምድ መውሰድና ሀገራዊ ምክክር አድርገው ስኬታማ ካልሆኑ ሀገራት ትምህርት መውሰድ እንደሚገባት ምሁራን ገለፁ፡፡

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህር የሆኑት መምህር ሮባ ጴጥሮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ሀገራዊ ምክክር በዓለም ላይ በተለያዩ ሀገራት በሰላማዊ ለውጥ የማይናቅ አስተዋፅዖ አብርክቷል፡፡ ባለፉት ዓመታት 181 የሚጠጉ ሀገራት ሀገራዊ ምክክር አድርገው ከ30 በላይ የሚሆኑት ሀገራት ውጤታማ ሆነዋል፡፡

ኢትዮጵያም ውጤታማ ከሆኑ ሀገራት ተሞክሮ መውሰድ እንደሚገባት እና ሀገራዊ ምክክሩን በስኬት ካላጠናቀቁ ሀገራትም ያለውን ችግር በመመርመር በቂ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባት ጠቁመዋል፡፡

መምህር ሮባ፤ ሀገራዊ ምክክሩ በዋናነት ቅድመ ዝግጅት፣ ዝግጅት እና ትግበራ የሚባሉ ሦስት ምዕራፎች እንዳሉት ጠቅሰው፤ እያንዳንዱ ሂደት ትልቅ ጥንቃቄ የሚፈልግ እና አከዋወኑ አካታች፣ አሳታፊና ሁለንተናዊ ሰላምን በማምጣት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክር ካካሄዱት በርካታ ሀገራት የቱኒዚያ ተሞክሮ ሊጠቀስ የሚገባው ነው የሚሉት መምህር ሮባ፤ በሀገሪቱ በተካሄደው ሀገራዊ ምክክር ለሕገ መንግሥታዊ እና ተቋማዊ ማሻሻያ የፖለቲካ መሠረት በመገንባት ግንባር ቀደም የሆኑ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የኖቤል የሰላም ሽልማት መቀበላቸውን ለአብነት አንስተዋል፤ በዚህ መንገድም ቱኒዚያን ከመፈራረስ ሊታደጉ እንደቻሉ አብራርተዋል፡፡

በተመሳሳይ የቀድሞው የየመን አምባሳደር ዶክተር ቶፊቅ አብዱላሂ ለሀገር ውስጥ ሚዲያዎች በሰጡት ቃለ ምልልስ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ያደሩ የፖለቲካ ችግሮችን፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን መፍትሄ ለማበጀት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አቋቁማለች፡፡

ለዘመናት የዘለቀውን ፖለቲካዊ እና ሌሎች ማህበራዊ አለመግባባቶችን ይቀርፋል ተብሎ የሚጠበቀውን ሀገር አቀፍ ውይይት በውጤታማነት ለማጠናቀቅ፤ ሀገራዊ ምክክር አድርገው በስኬት ካጠናቀቁ ሀገራት ልምድ መውሰድ ይገባል፡፡

ሀገራዊ ምክክሯ ስኬታማ ያልነበረ ነው ያሏትን የመንን እንደ አብነት ያነሱት ዶክተር ቶፊቅ፤ ኢትዮጵያ ከእንደዚህ ዓይነት ሀገራትም ያሉትን ክፍተቶች በመውሰድ ትምህርት ልትቀስም እንደሚገባት ተናግረዋል፡፡

የየመን ሀገራዊ ምክክር ያልተሳካው አካታች ባለመሆኑና የተወሰነ ቡድን በገፍ በመሳተፉ ነው ያሉት ዶክተር ቶፊቅ፤ ከዚያም ባሻገር የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት የሚጥሩ የጎረቤት ሀገራት እና የምዕራባዊያን እጅ ለየመን ስኬት አልባ ሀገራዊ ምክክር ዋና ምክንያት እንደነበሩ አብራርተዋል፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር አወቃቀሩና አሠራሩ ገለልተኛ መሆኑ እንዲሁም ሁሉን የሚመለከታቸውን ከሁሉም የኑሮ ደረጃ፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና ሌሎችንም ያካተተ እና አሳታፊ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሂደቱ የእያንዳንዱን ግለሰብ የጋራ ጥረት የሚፈልግ በመሆኑ እያንዳንዳችን ሚናችንን ልንወጣ ይገባል ብለዋል ዶክተር ቶፊቅ፡፡

ከኢትዮጵያ ምሁራን የምክክር መድረክ ኢንጂነር ጌታሁን ሁሴን በበኩላቸው፤ በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ደስተኛ ያልሆኑና ሂደቱን ለማደናቀፍ የሚሠሩ አሉ ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል እኩይ ፍላጎት ያላቸው ምዕራባዊያን በታዳጊ ሀገራት ላይ አዲስ የኒዮኮሎኒያሊዝም ማዕበል በሚመስል መልኩ ተፅዕኖ እያደረሱ ነው፡፡ ኢትዮጵያም የዚህ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መሰል ተፅዕኖ ሰለባ እንዳትሆን መሥራት ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# በአዲሱ በጀት ዓመት

# 16 አዳዲስ የመስኖ ፕሮጀክቶች ይጀመራሉ

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት 16 አዳዲስ የመስኖ ፕሮጀክቶች ይጀመራሉ፤ ለፕሮጀክቶቹ 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በጀት መመደቡን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በ2014 በጀት ዓመት የተቋራጮች አቅም ማነስና የግብዓት አቅርቦት ችግርና የዋጋ መናር በበጀት ዓመቱ ያጋጠሙ ችግሮች መሆናቸውን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ኢንጅነር አይሻ መሐመድ ገልጸዋል፡፡

ለመስኖ ፕሮጀክቶች ግብዓት እንዲሟላ ሰፊ ጥረት ተደርጓል። በድርቅ የተጎዱ አካባቢዎችን በ19 ሚሊዮን ዶላር የማቋቋም ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት እየተሰሩ የነበሩ 23 መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ሥራ፣ 17 የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክቶች፣ 184 በፌዴራል መንግሥት ልዩ ድጋፍ የሚሰሩ ንዑስ ፕሮጀክቶች፣ በቆላማ አካባቢዎች ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት በኩል የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ትግበራ ተከናውኗል።

በቆላማ አካባቢዎች ምርምርና ልማት ዘርፍ 11 ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ግንባታ ተጠናቋል፡፡

ለ2015 በጀት ዓመት ለመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር 15 ነጥብ 16 ቢሊዮን ብር ተመድበዋል። ከዚህ ውስጥ ከመንግስት 11 ቢሊዮን ብር ለፕሮጀክቶች ካፒታል በጀት እና 532 ሚሊዮን ብር ለመደበኛ በጀት እንዲሁም 3 ነጥብ 63 ቢሊዮን ብር ከዕርዳታና ብድር የተመደበ መሆኑን የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል።

በ2015 በጀት ዓመት 16 አዳዲስ የመስኖ ፕሮጀክቶች ይጀመራል። ከዚህ ውስጥ 10 የግንባታ እና 6 የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ ለፕሮጀክቶቹ 3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በጀት ተመድቧል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ አካሂዷል።



# “በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ከደንብና መመሪያ

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በጀቱ ከታለመለት ዓላማ ውጪ ያለ አግባብ ወጪ መደረጉና የአገር ሀብት ብክነቱ በእጅጉ ያሳሰባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩና የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠታቸው እስካሁን ወደ አንድ ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ከግለሰቦች ኪስ ወደ መንግስት ካዝና እንዲመለስ ተደርጓል፤ አሁንም ብዙ ይቀራል ብለዋል።

ገንዘቡ ወጪ የተደረገበት ሁኔታ በዝርዝር ሲታይ፣ የተሟላ መረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሒሳብ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ክፍያዎችና ግዥዎች፣ በብልጫ የተከፈለ ወጪ፣በተሰብሳቢ ሒሳብ መመዝገብ ሲገባው የቅድሚያ ሒሳብ ክፍያዎች መሆናቸውን ያብራሩት ወይዘሮ መሠረት፤ ብዙ ተቋማት ወጪዎቹን እንደ ወጪ ከመያዝ በዘለለ መረጃና ማስረጃ ማቅረብ ያልቻሉበት ሁኔታ መኖሩንና አንዳንዶቹ ደግሞ አሳማኝ ማስረጃ ያላቀረቡበት መሆኑን አስገንዝበዋል።

ከደንብና መመሪያ ውጭ ወጪ የተደረገው 4 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ሙሉ በሙሉ የባከነ ገንዘብ ባይባልም ደንብና መመሪያ ሳይከተል ከታለመለት ዓላማ ውጪ ወጪ መደረጉ ራሱ ትልቅ ኪሳራ መሆኑን ያስረዱት ወይዘሮ መሠረት፣ የዚህ ችግር መንስኤዎች ሲጠቃለሉ፣ ቸልተኝነት፣የእውቀትና ግንዛቤ ማነስ እንዲሁም ደንብና መመሪያን ጠንቅቆ ያለማወቅ መሆኑን አመልክተዋል።

ምን ይሁን ምን የህዝብ ሀብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ተቋማትን የሚመሩ አመራሮች ከባድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ ብክነት ሲያጋጥምም ግንባር ቀደም ተጠያቂ መሆናቸወን ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም ያሉት ዋና ኦዲተሯ፣ መሥሪያ ቤታቸውና ሌሎች የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች በመንግስት ተቋማት ጠንካራ የተጠያቂነት ሥርዓት እንዲሰፍን ለአስፈጻሚው አካል ትክክለኛ መረጃ የማቅረብ ሚናቸውን በአግባቡ እየተወጡና እንደሚወጡም ገልጸዋል።

በተቋሙ ችግር ምክንያት የቀረ የኦዲት ሥራ ባይኖርም በአገሪቱ በተከሰቱ የጸጥታ ችግሮች ምክንያት የኦዲት ሪፖርት ያላቀረቡ ተቋማት መኖራቸውን ያነሱት ወይዘሮ መሠረት፣ የነበረው የጸጥታ ችግር የኦዲት መሥሪያ ቤቱ ሥራ ላይ እንቅፋት አልፈጠረም ወይም ለባከነው ሀብት አስተዋጽኦ አልነበረውም ማለት እንዳልሆነ አስገንዝበዋል።

መሥሪያ ቤቱ የአቅም ክፍተት ላለባቸው ባለሙያዎች የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና እንደሚሰጥና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም ከድጋፍና ክትትል ባሻገር የተጠያቂነት ሥርዓቱ ላይ አስተማሪና ተግባር ተኮር ሥራ እንዲሰሩ ጠይቀዋል።

# መንግስት ከሕወሓት ጋር የሚያደርገው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በሰላማዊ ሁኔታ ቢቋጭ ተመራጭ በመሆኑም ህዝቡ ጫና ማድረግ እንደሚኖርበት አቶ በላይ አመልክተዋል።

መንግስት ሰላም ለማስፈን እያደረገ ያለው ጥረት ቁርጠኝነቱን የሚያሳይ ቢሆንም፤ በዚያው ልክ በሕወሓት በኩል ጥረት ሊታይ እንደሚገባ ተናግረዋል። ‹‹እርግጥ ነው የሕወሓት የመወላወል ሁኔታ የሚታየው አጀንዳው የእነሱ ብቻ ባለመሆኑ ነው። ከጀርባ የሚገፋ ሌላ ሃይል ሊኖር ስለሚችል ይህንን የሠላም ንግግር የፌዴራሉ መንግስት በጥበብ ሊይዘው ይገባል›› ብለዋል። በተለይም የዲፕሎማቲክ ጨዋታውንም በቅጡ ሊያጤነው እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

‹‹ይህች አገር ዛሬ ብቻ አይደለም ጠላት ያላት፤ እውነቱን ለመናገር መልኩን እየቀየረ እንጂ እኛ በነበርንበትም ጊዜ የነበረ ነው። አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ጉዳያቸውን ለማስፈፀም የሚፈልጉ ሃይሎች ከእነዚህ ሰዎች ጀርባ የሉም ልንል አንችልም›› በማለት አስረድተዋል።

ሕወሓት በዝርዝር በማን እንደሚደገፍ ማወቁም ጠቃሚ እንደሆነ የተናገሩት አቶ በላይ፤ በዋናነትም የመረጃና ደህንነት ተቋሙ ይህንን ሊያውቅ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ‹‹ምክንያቱም ከጀርባ ሆኖ የሚገፋው ሃይል በቅጡ ሲታወቅ ነው ማንኛውንም ቀጣይ አቅጣጫ መወሰን የሚቻለው›› ብለዋል።

ምዕራባውያኑም ሆነ አረቦቹ እዚህ አገር ውስጥ ያስቀመጧቸውና የሚፈልጉትን ነገር የሚያደርጉላቸው ብዙ ሰዎች ያሏቸው መሆኑን መዘንጋት እንደማይገባ ጠቁመው፤ ዘላቂ ሰላም ማምጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የድርድሩ ሂደት በአግባቡ መያዝ አለበት። ከሠላማዊ አማራጩ ጎን ለጎን ውስጣዊ የመከላከል አቅምን ማሳደግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ‹‹ምክንያቱም ሰላም ያልገዛውን ሃይል ይገዛዋል። ደግሞም በመለመን ብቻ የሚሆን ነገር የለም›› ብለዋል።

እንደ አቶ በላይ ገለፃ፤ የውስጡንም ሆነ የውጭ ጠላትን መከላከል የሚቻለው ሁሉም አካል ተቀናጅቶ ሲሰራ ነው። ችግሩን ለመፍታት ቁርጠኝነትና ትጋት አስፈላጊ ነው። ለሁሉ ነገር ከመሸበር ይልቅ አገር መውደድን እንደትልቅ ግብዓት በመጠቀም በራስ የመተማመን አቅምን ማጎልበት ይገባል። በተጨማሪም ዲፕሎማሲውም ቢሆን ከመከላከል ወደ ማጥቃት መግባት አለበት። ይሄ ደግሞ በአንድ ጀንበር የሚመጣ አይደለም። ብቃት ያላቸውንና አገር ወዳድ የሆኑ ሰዎችን ከየቦታው መሰብሰብ ለአገር አንድነት የሚከፈለው ዋጋ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል።

# በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ ተፈራ ታደሰ፤ የችግኝ ተከላው የበልግ ዝናብ በሚያገኙ አንዳንድ አካባቢዎች ቀድሞ የተጀመረ ቢሆንም፤ ከ90 በመቶ በላይ ተከላ የተከናወነው ግን በክረምት ላይ እንደሆነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል፡፡ ወደ ሥራ ከተገባ ጊዜ ጀምሮ ይህ መረጃ እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ ከአምስት ነጥብ ሦስት ቢሊየን በላይ ችግኞችን መትከል እንደተቻለም አስታውቀዋል፡፡

በበጋ ወቅት የተከላ ቦታ ልየታ በአግባቡ ተከናውኗል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለዩት ላይ የሰውና የቴክኖሎጂ አቅም ባማከለ መልኩ የመልከአምድራዊ መገኛ ቦታዎችን የመለየትና ካርታ የማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ተገብቶ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ ይህም የቱጋ ምን አይነት ችግኝ እንደተተከለና ምን ያህል እንደጸደቀ የሚያሳይ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በየክልሉ ችግኞችን ከማፍላት ጀምሮ በቅድመ ተከላው የነበሩ ዝግጅቶች በአግባቡ ተፈጽመዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአገር አቀፍ ደረጃ መርሀ ግብሩን ይፋ ካደረጉ በኋላ ክልሎች እንደየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ክልላዊ የማስጀመሪያ መርሀ ግብር በማዘጋጀት ሥራዎችን ሲያከናውኑ ነበር፡፡

ሥራው ከዚህ ቀደም የባለሙያ ሥራ ተደርጎ ይወሰድ እንደነበር በመጥቀስ ይህ ንቅናቄ ከተጀመረ ወዲህ ግን አገራዊ ቅርጽ እንዲኖረው በመደረጉና የሁሉም ዜጋ ተሳትፎ ስላለበት ጥሩ በሆነ መልኩ መከናወን ችሏል ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፡፡ በድህረ ተከላ ወቅት ማህበረሰቡ ችግኞችን እንዲንከባከብ ግንዛቤ መሰጠቱንም ጠቁመዋል፡፡

የሥራው አያያዝ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተጀመረው አካሄድ የቀረውን ሥራ በቀጣይ ሳምንታት ውስጥ ለማጠናቀቅ እንደታሰበ ገልጸው፤ መርሀ ግብሩ በይፋ እንደተጀመረ ሁሉ በይፋ ለመጨረስ የማጠናቀቂያ ፕሮግራም እየተዘጋጀ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

የተዘጋጁት ችግኞች ከሰባት ቢሊየን በላይ በመሆናቸውና የጉድጓድ ቁፋሮውም ይህንኑ ስለሚያሳይ የችግኞች ጉድጓዶችን ቁጥር ከግምት ባስገባ መልኩ መርሀ ግብሩ እስከሚያልቅ ድረስ ተከላው ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል፡፡ ከመደበኛው ተካላ መርሀ ግብር ባሻገር ክልሎች ሥራውን በተሳካ መልኩ እያስኬዱት እንዳለም ተናግረዋል፡፡

መርሀ ግብሩ ሲጀምር የመሬት መራቆት የተስፋፋ ስለነበር ችግሩን ለመቅረፍ ህብረተሰቡና አመራሩ በመተጋገዝ እየሰሩ መቆየታቸውን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ተግባሩ የታለመለትን ዓላማ በአግባቡ ማሳካት እየቻለ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ አራት አመታት በሁሉም የአገሪቱ



አካባቢዎች ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ሲካሄድ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

በዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርም ስድስት ቢሊየን ችግኞችን ለመትከል የታቀደ ሲሆን፤ ከሰባት ቢሊየን በላይ ችግኞች መዘጋጀታቸውን ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት



ከአስከፊ የሕይወት ገጽታ ወደ ኦፓል ማእድን ሳኪነት

ገጽ 13



የመንገድ ዘርፍ ችግሮችን እንደሚፈታ የታመነበት አዲሱ የመንገድ ፖሊሲ

ገጽ 14



## ‹‹አንዱ መንግሥት ሄዶ ሌላኛው ሲመጣ እያፈረሱ መገንባት ብዙ ነገር አሳጥቶናል››

- አቶ በላይ ገብረ ፃድቅ
የቀድሞ የመረጃና ደህንነት ባለሙያ እና ዲፕሎማት

ገጽ 6



ህይወትን - በማምሻ ዕድሜ

ገጽ 16

## በውስጥ ገጾች


የባሩድ ጭስ ሱሰኞች ገጽ 9

አጋጣሚን ለለውጥ መነሻ ገጽ 11

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹አንዱ መንግሥት ሄዶ ሌላኛው ሲመጣ እያፈረሱ መገንባት ብዙ ነገር አሳጥቶናል››

አቶ በላይ ገብረ ፃድቅ

የቀድሞ የመረጃና ደህንነት ባለሙያ እና ዲፕሎማት



ፎቶ፡ በሀዲስ አብርሃ

ማህሌት አብዱል

የዛሬው «የዘመን እንግዳችን» ለረጅም ዓመታት የመረጃና ደህንነት ባለሙያ እንዲሁም ዲፕሎማት ሆነው ሀገራቸውን ያገለገሉ ጉምቱ ሰው ናቸው። እንግዳችን አቶ በላይ ገብረፃድቅ ይባላሉ። የተወለዱት አዲስ አበባ ከተማ ራስ ዳምጠው ሆስፒታል አካባቢ ሲሆን እድሜያቸው አስር ዓመት ከሆነ በኋላ ደግሞ ኮልፌ አካባቢ ነው ያደጉት። የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አዲስ ከተማ ልዑል ወሰንሰገድ እንዲሁም ልዑል መኮንን እየተባሉ ይጠሩ በነበሩ ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁም አባዲና ፖሊስ ኮልጅ ገብተው በምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ በንጉሠ ነገሥቱ እጅ ተመርቀዋል። ከ1965 ዓ.ም ጀምሮ በወቅቱ የመከላከል መረጃ ተቋም ይባል በነበረው የህዝብ ፀጥታ ጥበቃ ዋና መሥሪያ ቤት ተመድበው አስፈላጊውን ሙያዊ ሥልጠና በዘመኑ ወዳጅ በነበሩት እስራኤሎችና አሜሪካውያን ከወሰዱ በኋላ አስተባባሪ በመሆን እስከ መሥከረም 1967 ዓ.ም ድረስ ሠርተዋል።

በመቀጠልም የመከላከያ መረጃ መምሪያ እየተባለ ወደሚጠራው የሥራ ክፍል ተዛውረው መስራት ጀመሩ፤ እዚህም መምሪያ ሳሉ የመረጃን ስራ ጨምሮ የበረራ ደህንነት ጥበቃን ማለትም ፀረ-አውሮፕላን ጠላፊዎችን ምድርና አውሮፕላን ላይ ሆኖ የመቆጣጠር ሃፊነት ተሰጥቷቸው ወደ ቀጣዩ የሲቪል እርከን እስከተዘዋወሩበት ጊዜ ድረስ በሠራዊቱ ውስጥ በሻምበልነት ማዕረግ አገልግለዋል። ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ አራት ዓመታት ደግሞ አዲስ ተቋቁሞ በነበረው የሀገርና ሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ሚኒስቴር በሚኒስትሩ ፅህፈት ቤት የመምሪያ ኃላፊ ፤ የሚኒስትሩ ልዩ ረዳትና የመረጃ ሰነዶች አስተባባሪ ሆነው ሰርተዋል። በዚህ ጊዜ በመረጃ ተቋም ሥልታዊ መረጃ ትምህርት ቤት ሙያዊ ክህሎት ላይ አስተምረዋል።

እንግዳችን የደርግ መንግሥት እስከ ወደቀበት ጊዜ ድረስ ደግሞ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዛውረው በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ኤምባሲ አንደኛ ጸሃፊ ዲፕሎማት፤ በምስራቅ ጀርመን በርሊንና በመጨረሻም እስራኤል ቴላቪብ አማካሪና ላይዘን ሆነው አገልግለዋል። ይሁንና በወቅቱ መንግሥታዊ ሥልጣኑን በተቆጣጠረው የሕወሓት ደህንነት በተፃፈ ደብዳቤ ከስራ በመታገዳቸው ወደ እንግሊዝ ለመሰደድ ተሰደዱ።

ጀርመን በነበሩበት ጊዜም በሥልጣን ላይ የነበረው መንግሥት ረጅሙን የአገልግሎት ዘመናቸው፣ ለስራው ያሳዩትን ታታሪነት፣ ሙያተኝነትና ለሀገራቸው ያላቸውን ፍፁም ታማኝነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሦስተኛ ደረጃ የሕብረተሰዊነት ኢትዮጵያ ጀግና ሜዳይ ተሸላሚ በማድረግ ካሉበት ሥፍራ ድረስ እንዲደርሳቸው ተደርጓል። ዲፕሎማት ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ጀምረውት የነበረውንና ሦስተኛ ዓመት ላይ ያቋረጡትን ትምህርት በመቀጠል የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስና በሰው ሃይል እቅድ ትምህርት ዘርፍ ማግኘት ችለዋል።

በስደት ቆይታቸው በተለያዩ ሥራ ዘርፎች ላይ የሰሩ ሲሆን በዋናነትም በአማካሪ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው በጥናትና ምርምር ቀጥሎም በአንድ የክልል መንግሥታት አቅም ግንባታ መስሪያ ቤት በአማካሪነትና ለሥራ ፈላጊዎች ሥልጠና በመስጠት ተቀዳሚ ባለሙያ በመሆን አገልግለዋል። በቅርቡ ደግሞ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው «የመረጃና ደህንነት ሙያና የኢትዮጵያ ገፅታው» የተሰኘ መፅሐፍ ለአንባቢያን አድርሰዋል። በመፅሐፉና በኢትዮጵያ የመረጃና ደህንነት ዘርፉ ዙሪያ የመረጃና ደህንነት ባለሙያና ዲፕሎማት ከነበሩት ከአቶ በላይ ገብረፃድቅ ጋር ያደረግነውን ቃለ-ምልልስ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሀገር ወጥተው የቀሩበትን አጋጣሚ ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አቶ በላይ፡-** እንደሚታወሰው ሕወሓት በ1983 ዓ.ም ሀገሪቱን ሲረከብ እኔንና 78 የሚሆኑ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶችን ውጭ እያለን ከስራ አሰናበተን። ወደ ሀገር ቤት እንድመለስ ብጠራም አጠራራቸው በጎ አይነት ስላልነበርና አዝማሚያው ስላላማረኝ ቤተሰቤን ይዤ ተሰደድኩኝ። በዚያ ጊዜ አሳዛኙ ታሪክ እነዚህ 78 የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች መሰደጃ ቦታ እንኳን እንዳያገኙ ደብዳቤ ተፅፎ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርታቸው እንዳይሰራ ተደርጎ ሰርኩላር ተላልፎ ነበር። ግን እድለኛ ሆኜ የእንግሊዝ መንግሥት ያቀርብኩትን የጥገኝነት ጥያቄ ተቀበለው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንግዲህ በስደት ሕይወት ነው የቆየሁት። እውነቱን ለመናገር ግን እንግሊዝ ሀገር በቆየሁባቸው ዓመታት ሁሉ ይሄ ነው የሚባል ችግር አልደረሰብኝም። እንዲያውም ብዙ መማር እንድችል፤ ዴሞክራሲ ምን እንደሚመስል እንድረዳ አድርጎኛል። አድሎ የሚባል ነገር አላየሁኝም። ስለዚህ በቆየሁበት መልካም ዘመን ለሀገሩ ሕግና መንግሥት ምስጋና ይግባው እላለሁ። ምክንያቱም ስደት አፀያፊ ነገር ነው፤ ሌላ ቦታ ብሆን ደግሞ ችግር ሊያጋጥመኝ ይችል ስለነበረ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመረጃና ደሕንነት ሙያ ዙሪያ በቅርቡ ለንባብ ያበቁትን ሙያና ታሪክ ቀመስ መፅሀፍ ለመፃፍ ያነሳሳዎት ምክንያት ምን እንደሆነ ቢያስረዱን?**

**አቶ በላይ፡-** በእኔ ግምት የመረጃ ተቋሙ፣ ሙያውና ሙያተኞቹ ለአንድ ሀገር ወሳኝ ግብዓቶች ስለሆኑ ሕብረተሰቡ በአግባቡ ሊያውቃቸው ይገባል። ምክንያቱም ስለዚህ ተቋም የሚባለውን አውቅ ስለነበር ነው። የሚገርምሽ በዚህ ተቋምና ሙያ ላይ የነበረው ጥላቻ ምንም ከማይረዳው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ከላይ የተቀመጡ ትልልቅ የመንግሥት ሃላፊዎችና የጉዳዩ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ሳይቀሩ ፍፁም የሆነ ጥላቻ ነበራቸው። ስለዚህ ይህ ሁኔታ መቀየር ስላለበት ሰዎች እንዳልኩት ተቋሙንም ሆነ ሙያውን እንዲሁም ሙያተኞችን በአግባቡ ሊረዱ ይገባል ከሚል መነሻ ነው የፃፍኩት። ይሄ ደግሞ በዝርዝር መፅሐፉ ውስጥ ስለተጠቀሰ አንባቢያን እንዲያነቡት እጋብዛለሁ። ሁለተኛ መውደድም ሆነ መጥላት እውነቱን ለመናገር በአጀብ ከሚሆን ይልቅ በምክንያት ቢሆን ይሻላል። አንዳንዶቻችን ሌላው የነገረንን ብቻ አምነን እንቀበላለን። ያ ከሚሆን ይልቅ በማወቅ ላይ ተመስርተን ነው መጥላትም ሆነ መውደድ ያለብን። ምክንያቱም በማወቅ ላይ የተመሰረተ ጥላቻ በራሱ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ነው።

በመሰረቱ የመረጃ ደህንነት ተቋም የሀገርና ሕዝብ ጠባቂ እንጂ በየወቅቱ የሚቀያየሩ መሪዎች ጠባቂ አይደለም። ይህንን ስል እዚያ ተቋም ውስጥ መሪውን የሚጠብቅ ክፍል የለም እያልኩኝ አይደለም። ሌላው ግን በኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ወታዳራዊ ጉዳዮችና ሕብረተሰብ ላይ ችግር እንዳይደርስ የሚከላከል ነው። ከዚያ ባሻገር ሙያው በእውቀት ላይ ተመስርቶ የሚሰራበት ነው። ስለሆነም ለሙያው የሚመጥኑና የሚችሉ ፍቃደኞች የሆኑ ወጣት ኢትዮጵያውያን በሙሉ በውስጡ መካተት አለባቸው። ምክንያቱም ሙያው ሀገር አድን በመሆኑ ነው። ይህንን የበለጠ ለመረዳት ግን መፅሐፉን ማንበብ የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

በተጨማሪም ስለመረጃ ምንነት የሚያውቁ ካሉ የበለጠ እንዲያውቁ፤ የማያውቁ እንዲያውቁ፤ አውቀው ግር ያላቸው ደግሞ የበለጠ እንዲረዱ ያደርጋል ብዬ ስለማምን ነው ይህንን መፅሐፍ የፃፍኩት። ደግሞስ እኛ ትናንት የነበርነው ሰዎች ካልፃፍን ማን ይጻፈው?። በእኔ ግምት እስካሁን ድረስ ይህንን መሰል መፅሐፍ አልተፃፈም፤ ብዙ ነገሮችን ያካተተ መረጃ ያለው በመሆኑ ጠቃሚ ነው ብዬ በማሰብ ነው። በዋናነት ግን ለመፃፍ አነሳስቶኛል የምለው ቶድ ሄነሪ የሚባል ጸሃፊ መፅሐፉን ሲፅፍ የመፅሀፉን አርዕስት « ባዶህን ሙት» ብሎ ነው የሰየመው፤ ይህም ማለት ሁላችንም ወደዚህ ስንመጣ ምንም ይዘን እንዳልመጣነው ሁሉ ስንሄድም ምንም ይዘን አንሄድም፤ ስለዚህ እኔም ቢያንስ የማውቀውን ሰጥቼ ባዶዬን ልሙት ብዬ በማሰብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለ መረጃ ደህንነት ሙያና ስራ ሕዝቡ ላይ የተዛባ ግንዛቤ እንዲኖር ያደረገው ምንድን ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ በላይ፡-** አስቀድሜ እንደገለጽኩት እዚህ ሀገር ትልቁ ችግር በማህበር መውደድና መጥላት እንደባህል ሥር የሰደደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ነው የሚመስለኝ። ለጥላቻም ሆነ ለፍቅራችን ምክንያታዊ ያለመሆኑ ነገር አለ። ሙያው ሀገር አድን ነው፤ እኔ መፅሐፉን ስፅፍ ምክንያቶቼን እንደገለፅኩልሽ ከእነዚህ አንዱ ሙያውንም ሆነ ዘርፉን ሰዎች የሚጠሉት በቅጡ ስለማያውቁት ነው። ቢያውቁት ኖሮ ሀገር አዳኝ መሆኑን ይረዱ ነበረ። በጭራሽ ይሄ ተቋም የመንግሥት ዙፋን ጠባቂ አይደለም። ይልቁኑም የፖለቲካ አለመረጋጋት በሀገር ውስጥ እንዳይፈጠር መንግሥትን ይመክራል፤ የኢኮኖሚ ቀውስ እንዳይከሰት ያሉ ችግሮችን ያያል፤ ሕብረተሰቡ ያለበትን ችግር ይጠቁማል፤ ሊስተካከሉ በሚገቡ ፖሊሲዎች ላይ ሃሳብ ይሰጣል፤ ወታደራዊ ጉዳይን በሚመለከት ከወታደሩ ቀድሞ መረጃ በማግኘት ሀገርን ይታደጋል። ምክንያቱም ወታደሩ ከመዝመቱ በፊት የሚያስፈልገውን መረጃ ካላገኘ የእሳት ራት ነው የሚሆነው። መረጃው ከተገኘ ጠላት የሚሰበስባቸው መሳሪያዎች፣ ታንኮች፣ ሚሳኤሎች ሁሉ ልክ እንደልጆች አሻንጉሊት ሊቆጠሩ ይችላሉ። መረጃው ቀድሞ ከተገኘ የወገን ሃይል በቀላሉ የጠላትን መሳሪያ ማደባየት ይችላልና ነው።

ስለዚህ እኔ ሕብረተሰቡ መረጃ ላይ የተመሰረተ ጥላቻ አለው ብዬ አላምንም። ከዚህ በመነሳት ጥላቻው መሰረተ ቢስ ነው ባይ ነኝ። እርግጥ ነው፤ አንዳንድ ጊዜ እነዚህ የመረጃና ደህንነት ሰዎች ከሚገባው በላይ ሃይል በመጠቀም መረጃን ለማውጣጣት የሚያደርጉት ጥረት በሕዝብ ዘንድ ጥሩ ምልከታ እንዳይኖራው አድርጎ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ይህንን የሚያደርጉት በተለይ የጠላት ምርኮኞች የሚፈለገውን መረጃ የሚደብቁ በመሆኑ ነው። ይህም ቢሆን ምክንያታዊ ነው ብዬ አላምንም፤ ሃይል ከመጠቀም ይልቅ ሰውን አለመጉዳትና ቀስ ብሎ በዘዴ ማውጣቱ ነው ተመራጭ።

**አዲስ ዘመን፡- በመፅሐፎት ላይ እንደተጠቀሰው የመረጃና ደህንነት እንዲሁም የስለላ ስራ ከኢዛና ዘመነ-መንግሥት ጀምሮ የነበረ፤ በዚህ ዘርፍ ኢትዮጵያ ዘመናትን ያስቆጠረ ታሪክ እንዳላት ያነሳሉ። ስመሆኑ በየትኛው ዘመነ መንግሥት ነው የበለጠ የመረጃና ደህንነት ሥራ በሙያ ደረጃ ጎልቶ የወጣውና የዳበረው?**

**አቶ በላይ፡-** እንግዲህ ታሪካዊ ሂደቱ ምን ይመስል እንደነበር መፅሐፉ ውስጥ በዝርዝር ተጠቅሷል። በሀገራችን በተለይም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ-መንግሥት መሰረቱ ተጥሎ ነበር። እውነቱን ለመናገር እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ሰርቷል። ከዚያ በኋላ ቀዳማዊ ኃይለሥላሤ ሲረከቡት የተሻለ ተቋም ተገንብቷል። ምክር የሚሰጡትም ሰዎች ከሰለጠነው ዓለም አካባቢ የመጡ ስለነበሩ መረጃውን ዘመናዊ በሆነ መንገድ ለማቋቋም የሚቻለው ሁሉ የተደረገ ይመስለኛል። ይህም ስለሆነ በየዘርፉ የተደራጀ መረጃ በአግባቡና መልክ ባለው ሁኔታ የመረጃ ተቋሙ እንዲመሰረት የተደረገው። በዚያ ጊዜ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከማሰልጠኛዎች ተማሪዎች ተመልምለው፤ ሰልጥነው ለስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል። እንደየአስፈላጊነቱም ውጭ ሀገር እየተላኩ አስፈላጊውን ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

እናም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተሻለ ሁኔታ የመረጃ ተቋሙ መልክ ኖሮት ተደራጅቶ ነበር ማለት ይቻላል። በዚህም ምክንያት ሀገራችን ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ችግሮች በተለይም ከውጭ የሚመጡ ሰላዮችን ማምከን ችሏል። እናም የተዋጣለት የመረጃ ተቋም ነበርም ማለት ይቻላል። በቁጥር ደረጃ በጣም አነስተኛ ግን ደግሞ በአግባቡ የሰለጠነና ያወቀ፤ አመራሩም በጣም የጎለበተ እውቀት ያለው ስለነበረ በጥሩ ሁኔታ ተደራጅቶ ነበር ብዬ አምናለሁ። የደርግ መንግሥት ሲመጣ ግን የመረጃውን ተቋም የንጉሱ ዙፋን ጠባቂ አድርጎ ያየው ስለነበር አላስፈላጊ ጥላሸት ሲቀባው ለተወሰነ ጊዜ ከርሟል። ግን የውጭ ጠላቶች ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ከተማ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ይርመሰመሱ

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



ስለነበር፤ በተለይም ደግሞ አንድ ክስተት ከተፈጠረ በኋላ ክፍተቱ ስለታያቸው ነው ዳግሞ እንዲቋቋም ያደረጉት።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ነበር የተከሰተው?**

**አቶ በላይ፡-** አንደኛ በጠላትነት የሚያዩን ሃይሎች ነበሩ፤ ይህ ምንም የማይታበል ነው። ምክንያቱም የአባይና የድንበራችንም ጉዳይ እንዲሁም በሱማሌ በኩል የነበረው የመሬት ቅሚያም በዚያን ጊዜ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም አላስፈላጊ ነገሮችን መፈፀም የመረጃው ተቋም ነበር የሚጠቁመው። ከዚያ ባሻገር ከተማ ውስጥ በሽማቂው ድርጅት አንዳንድ ቦታ ላይ ፍንዳታ እንዲፈፀም ሆነ። በዚህ ምክንያት የመረጃውን ተቋም ሲስተናገድ የነበረው አላግባብ ስለነበር ወደ ልቦናችን ተመልሰን የመረጃው ድርጅት እንዲሰራ ብናደርግ ይህ ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ ነው የመረጃውን ድርጅት እንደገና በተሻለ መልኩ ማቋቋም ሊያስፈልግ ይችላል ተብሎ ታምኖበት ሃሳባቸውን የለወጡት።

የሚያሳዝነው ግን በዚያን ጊዜ የነበሩ ከፍተኛ መኮንኖች ከንጉሱ ጋር ንክኪ አላቸው፤ ወይም ደግሞ በረጅም ጊዜ ቆይታቸው ይህንን ያህል ያስመዘገቡት ነገር የለም የሚል ሃሳብ መነሻ በማድረግ ሥልጣናቸውን እንዲለቁ በመደረጉ የመረጃው ድርጅት በጣም ሳስቶ ነበር። ስለዚህ ወደኋላው ላይ የሀገር ደህንነትን የማስጠበቁ ነገር ያለመረጃው ተቋም ምንም ሊደረግ እንደማይችል ግንዛቤ ተይዞ ድርጅቱ እንዲጠናከር ተደረገ። በውስጡ በርካታ ክፍሎች ያሉት፤ የመከላከል መረጃ ያለው፤ የውጭ መረጃን የሚያጠናቅር፤ የኢኮኖሚ መረጃን የሚያሰባስብ፣ የምርመራ ዘርፍ ኖሮት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጠናከር ተደረገ።

ይሁንና ቀደም ሲል የነበረው የሰለጠነው የሰው ሃይል ስላልነበር ከውጭ የመጣው ሃይል የሚፈለገውን ያህል ለመስራት አልተቻለውም። ምክንያቱም ሰው ስለመጣ ብቻ ሥራውን ይሰራል ማለት አይደለም። ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ ጠንካራ የሚባል አልነበረም፤ ግን በሂደት ጥሩ እየሆነ ሄዶ እንዳውም ትክክለኛውን ምንጭ ባላስታውስም በአፍሪካ በሶስተኛነት ከሚመደቡ ጠንካራ የመረጃ ተቋም ውስጥ አንዱ ነበር። ባለፉት 27 ዓመታት ግን ብዙ የጠለቀ እውቀት የለኝም፤ ምክንያቱም አስቀድሜ እንደገለፅኩልሽ በወቅቱ የመረጃ ሃላፊ በአቶ ክንፈ ገብረመድህን ደብዳቤ የተባረርኩኝ በመሆኑ ከዚያ በኋላ ያለውን አላውቀውም። ከሰማሁት ነገር ተነስቼ ግን መናገር ያስቸግረኛል። ምክንያቱም ቦታው ላይ የነበረው ሰው ቢናገረው ነው የሚሻለው።

**አዲስ ዘመን፡- የመረጃ ደህንነት ስራ በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ያለው እንደመሆኑ ሙያውም ሆነ ተቋሙ የዚያኑ ያህል ማደግ ያልቻለበት ምክንያት ምንድነው ይላሉ?**

**አቶ በላይ፡-** ለዚህ ትክክለኛውን ምክንያት ለመናገር መረጃና ማስረጃ ባላቀርብም ግን የሚሰማኝን ሃሳብ ነው የምሰጠው። በእኛ ሀገር አንዱ መንግሥት ሄዶ ሌላኛው ሲመጣ እያፈረሱ መገንባት ብዙ ነገር አሳጥቶናል ብዬ አስባለሁ። ለምሳሌ በንጉሡ ዘመነ-መንግሥት የነበሩ ትላልቅ ጉምቱ የነበሩ ሃላፊዎች ነበሩ። እንደኮሎኔል ሰለሞን ከድር፣ እንደ ጀነራል አምደሚካኤል በላቸው፣ እንደአቶ ነብየ ልኡል ክፍሌ የመሳሰሉ ሰዎች በአንድ ቀን የሚገኙ ወይም የሚመረቱ አይደሉም። ረጅም ጊዜ የወሰደ ትምህርት፣ ልምድ፣ የውጭ ተሞክሮ ያላቸው ሰዎች ናቸው። የመምራት ብቃት የነበራቸው ናቸው። እነዚህን ሰዎች በምንም አይነት በዓመታት መተካት አይቻልም። ደርግ እንደመጣ እነዚህን ሰዎች እንዲረሸኑ አድርጓል።

እነዚህን ሰዎች ማጣት ማለት ከፍተኛ ክስረት ነው። ከዚያም በኋላ በርካታ ሰዎችን በተዋረድ አጥተናል። እሱ ብቻ ሳይሆን እነዚህን ሰዎች ማጣት ከፍተኛ ክስረት ሆኖ ተቋማቱንም እንደዚሁ አፍርሰናል። እናም የመረጃው ተቋም ትናንት የነበረውን አፍርሶ መገንባቱ በርካታ ችግሮች ፈጥሯል። በደርግ ጊዜ ደግሞ ጠንካራ ተቋም ተቋቁሞ ብዙ ነገር የሰራ ቢሆንም ወያኔ ሲመጣ ፎቁንና የቴክኖሎጂ ቁሳቁሱን ወስዶ ሰዎቹን በሙሉ እስር ቤት ነው የከተተው። እናም ከዚህ በላይ የበለጠ ክስረት አይኖርም።

በመፅሐፌም ላይ «በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም» በሚል ርዕስ የካተትኩት ሃሳብ በሱማሊያ በኩል የነበረውን ችግር የፈታው የደህንነቱ መስሪያ ቤት ነው። ሌላው ይቅርና ከሽማቂዎች ጋር ድርድር እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቸው የመረጃው መስሪያ ቤት ነው። በርካታ ምክረ-ሃሳቦችን ከመረጃው ጋር የሰጠው ይኸው መስሪያ ቤት ነው። በአጠቃላይ በርካታ ሥራዎችን የሰራ ወደፊትም ሊሰራ የሚችል ተቋም ነበር። ያ በነበረበት ሁኔታ እንዲቀጥል ባለመደረጉ እንደሀገር ብዙ ጉዳት የደረሰብን ይመስለኛል። አሁንም ቢሆን ወደፊት እያፈረስን የምንገነባ ከሆነ በውስጡ ያሉትን ሰዎቻችንን እንደማይፈለግ እቃ የምንወረውራቸው ከሆነ ችግሩ የከፋ ነው የሚሆነው። ስለዚህ የሚመለከተው አካል ማስታወሻ ሊወስድበት የሚገባ ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፡- በመፅሐፎት ላይ ‹‹የሙያተኞችን ወኔ ሰላቢ ባለሥልጣናት›› ሲሉ ጠቅሰዋል፤ ለመሆኑ ይህን ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?**

**አቶ በላይ፡-** በመጀመሪያ እንዲያው ሊሆን የሚገባው በከፍተኛ ማዕረግና ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች የመረጃ «ሀ፣ ሁ» እንዲያውቁ ቢሆን መልካም ነው። ምክንያቱም መረጃው ተቋም የሚሰራውን የሚያውቁ ከሆነ ጥላቻው ቦታ እንደማይኖረው በቂ ማስገንዘቢያ ሊሆን ይችላል። አስቀድሜ እንዳነሳሁት በጅምላ የመጥላት ባህሉ ባለሥልጣናቶቻችን ዘንድ ሳይቀር ዘልቋል። አንድ ምሳሌ ልጥቀስልሽ፤ በአንድ ወቅት እኔ ማታ ላይ ከቢሮ ስወጣ መንገድ ላይ አንድ ሚኒስትር የመኪናቸው ጎማ ተንፍሶ ተመለከትኩኝ፤ እሳቸው ባያውቁኝም እኔ ስለማውቃቸው ዝም ብዬ ማለፍ ስላላስቻለኝ ከፊት መኪናዬ አቁሜ አጠገባቸው ሄጄ ጌታዬ ምን ልርዳዎት ስላቸው ፊት ለፊት ያቆምኩትን መኪና አይተው «ማን ነው የላከህ?፤ እከሌ ነው ወይ?» ብለው ነው የጠየቁኝ። እንግዲህ አንድ ሚኒስትር ከተሰላይነት ውጪ ካላሰበ እኔ ተራው ሰው የፈለገውን ቢሆን ምንም ሊገርመኝ አይችልም።

ስለዚህ ጥላቻው ሕዝቡ ብቻ ውስጥ ያለ ሳይሆን ባለሥልጣናቱ ውስጥም ያለ መሆኑን ለማሳየት ነው። ወደፊትም ለመሄድ አንዱ ማነቆ ይሄ ይመስለኛል። እነሱ በስራው ካላመኑ፤ በሰዎቹ ላይ እምነት ካልጣሉ፤ ለሀገር ይበጃል ካላሉ ሌላው ተራው ሰው የፈለገውን ቢል ብዙ ሊደንቀን አይችልም። በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች ይህ አይነት ጥላቻ ነበራቸው። ግን ሁሉም ናቸው ለማለት ያስቸግራል።

**አዲስ ዘመን፡- በባለሥልጣናቱ የነበረው እርስ በእርስ የመጠላለፉ ነገር የሀገር ደህንነት ላይ የጣለው አደጋ ምን ነበር?**

**አቶ በላይ፡-** እውነቱን ለመናገር ተደጋግፎ በመስራት የሚገኘውን ውጤት ያህል በተናጠል የሚደረገው ሙከራ ውጤታማ ይሆናል ማለት ያስቸግራል። በጋራ ማሰብና መስራት ውጤታማ ያደርጋል። እኛ ስለተጠላን ሥራችንን አላቆምንም። ምክንያቱም የምንሰራው ለሀገርና ለሕዝብ ነው እንጂ ለግለሰቦች አልነበረም። ያ ማለት ጥላቻው ጫና አልነበረውም ማለት አይደለም፤ ግን ጫናም ቢኖረው የተሰጠንን አደራ ሀገርና ሕዝብ መጠበቅ ስለሆነ በአቅማችንና ሙያችን በሚፈቅደው መሰረት ሥራው ተሰርቷል። የበለጠ ግን መስራት ቢቻል ኖሩ ውጤቱ የተሻለ ይሆን ነበር። እናም ዝም ብለው የሚጠሉ ግለሰቦች አልጠፉም፤ ግን የመረጃው ተቋም በዚያ ጊዜ ከእነዚህ ሰዎች የጥላቻ ጦር ይወረወራል ብሎ ስራውን አላቆመም፤ ይሰራ ነበር። እናም መጠላለፉ ጎድቷል፤ ግን ሥራ እንዳንሰራ አላደረገንም።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ የመረጃ ተቋም ባለፉት 27 ዓመታት ኢትዮጵውያን ለደህነታቸው የሚተማመኑና ልክ እንደ ምዕራብውያና የስለላ ድርጅቶች የሚኮሩበት መሆን ያልቻለበት ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ በላይ፡-** ባለፉት 27 ዓመታት ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ዛሬ ባልመልሰው ደስ ይለኛል። ምክንያቱም ሁለተኛው መፅሐፌ ላይ በስፋት የተሄደበት ስለሆነ ነው። ደግሞም ከምሰማውና ከሚዲያ ከማየው ባለፈ ውስጡ ስልነበርኩኝና ተጨባጭ መረጃ በእጄ ሳይኖር ይሄ ነው፤ ያ ነው ብሎ ለመናገር ያስቸግረኛል። ምክንያቱም ክህሎቴም እምነቴም ተጨባጭ በሆነ ነገር ላይ መናገር በመሆኑ ነው። ያልተጨበጠ ነገር ደግሞ አሉባልታ ነው የሚሆነው። በጥቅሉ ግን ትናንትና የእኛን መስሪያ ቤት ሲያጠለሽ የነበረው ይሄኛው ቡድን እሱ ራሱ በዚያ ስህተት ውስጥ ተዘፍቆ እንደነበር እረዳለሁ። እሱ ሲያደርገው ምንም ችግር የለውም ብለው ነበር የሚያስቡት። እኛ በስደት ሳለንም ስለዚህ ተቋም ብዙ ሰዎች ብዙ ነገር ሲናገሩ አድምጠናል።

ወያኔ ተቋሙን ሆነ ሕዝቡን ይመራበት የነበረው አይነት አሰራር በአንድ ወቅት ምስራቅ ጀርመን በርሊን ሆኜ ምስስል ያለው ነገር አጋጥሞኝ ነበር። የመረጃ መስሪያ ቤቱ ሰዎችን ጠርንፎ መያዙ ነገር ተመሳሳይነት ነበረው። ያኛው የሚለየው በዘመናዊነቱ ነው። እንደሚታወሰው አንድ ለአምስት የሚባል ጥርነፋ ነበር። እዚያም ያን አይነት መልክ የነበረው የመረጃ ተቋም ስለነበር መጨረሻ ላይ እ.ኤ.አ 1985 እንደገና ማወቅር ስራ በመስራት ኮምዩኒዝምን የመተው ሁኔታ ሲመጣ ያ የተጠረነፈ ህዝብ እንዳለ ነቅሎ ወጥቶ ወደ መረጃው መስሪያ ቤት ነው የሮጠው። ያንን በአይኔ አይቻለሁ። እርግጥ እዚህ ያ አልሆነም፤ አለመሆኑ ጥሩ ነው። ምክንያቱም በመካከሉ ሊፈጠር የሚችለውን ችግር ማንም አያውቅምና ነው።

በአጠቃላይ ግን እንዳው በአይኔ ባላይም በጣም ብዙ በጎ ያልሆኑ ነገሮች እንደተደረጉ እረዳለሁ። ትናንትም እኛ በነበርንበት ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች በተለይ እነሱ በነበሩበት ቦታ ላይ ሲደረግ የነበረ ነው። ይሁንና የመረጃ ተቋማት የሚቋቋሙት ሀገርና ህዝብን ለመርዳት እንጂ እንደዚህ አይነት የማይገባ ነገር ለማድረግ አይደለም። በመሆኑም ይህንን ሊቆጣጠር የሚችል አካል መኖር አለበት። ብዙ ጊዜ እንደምለውም ኢትዮጵያ ከ 115 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ አላት፤ ይህ ሕዝብ በሺዎች የሚቆጠሩ የመረጃ ሰራተኞች አይጠበቁም። ኢትዮጵያን የሚጠብቃት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። በተቻለ መጠን በመረጃው ተቋም ውስጥ ያሉ ሰዎች የሕዝብ አሽከር ነው መሆን ያለባቸው። ምክንያቱም የሕዝብን ወገናዊነት ማግኘት እስካልተቻለ ድረስ የትኛውንም ጠላት መመከት አይቻልም።

**አዲስ ዘመን፡- በመረጃ ደህንነት ተቋሙ በሚሰሩበት ጊዜ ቢሆን ብለው የሚቆጩበት ነገር አለ?**

**አቶ በላይ፡-** አለ፤ አንደኛ የሚቆጨኝ ነገር አስቀድሜ እንዳነሳሁልሽ የመረጃው መስሪያ ቤት የሕዝብ ግንኙነት ስራ ሰርቶ ሕዝብን ከጎኑ ቢያሰልፍ ኖሮ ለእኔ ትልቅ ስኬት ነበር። ምክንያቱም እኛ መጨረሻ ላይ ሕዝብ ጠልቶን ነው፤ አይናችሁ ለአፈር ብሎን ነው። ያ ሊሆን አይገባውም። እናም ትልቁ ነገር ሕዝብን ወገናዊ አድርገው ቢሆን ኖሮ በእውነት ትልቅ ስራ ነበር።

ሁለተኛ አመራሩ ላይ ያሉ ባለሥልጣናትን መረጃውን አቅርበው መሪውን የመሞገትና የማሳመን በዚያ መሰረት ውሳኔ እንዲሰጥ አድርገው ቢሆን ኖሮ ትናንት የደረሰው ነገር አይደርስም ነበር። ምክንያቱም የእነሱ መድከም እውነት ይዘው በእጃቸው ማሳመን አለመቻል ትልቅ እንቅፋት ነው።

ሌላው በመስሪያ ቤት ውስጥ በአንድ ወቅት ከሙያው ጋር የማይገናኙ ሰዎች በብዛት እንዲመጡ ተደርጓል። እነዚያ ሰዎች እውነቱን ለመናገር የሚሰሩ ሳይሆን እዳ ሆነው ነው የቆዩት። ያም ስራ በመቻልና ባለመቻል መካከል ባለ ሰው አይሰራም። ብቃት፣ እምነት፣ ድፍረት፣ ንፁህና ከውሸት የፀዱ ሰዎች ያስፈልጋል። በሌላው ሰው መረጃ የሚሰበስብ አካል መጀመሪያ ራሱ የፀዳ መሆን አለበት። እናም በዚያ ጊዜ የማይችሉ ሰዎች ተቋሙን እንዲቀላቀሉ ባይደረግ ኖሮ ምንአልባትም የተሻለና ጥሩ ስራ በሰራን ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- በመፅሐፎት ላይ የደርግ አመራሮች ፕለው ከመውጣትና ሀገሪቱም በሕወሓት እጅ ሳትወድቅ፤ ኤርትራም ሳትገነጠል፤ ኢትዮጵያም ወደብአልባ ሳትሆን መደራደር ይቻል የነበረበት እድል እንደነበር አንስተዋል። ምን ነበር ያ እድል?**

**አቶ በላይ፡-** በእግጠኝነት ድምዳሜ ላይ ባልደርስም ግን ምንም የማይቻል ነገር እንደሌለ እምነቴ ነው። ለምሳሌ ከሻቢያና ወያኔ ሽማቂ ቡድኖች ጋር ድርድር እንዲኖር መንገዱ የመረጃው መስሪያ ቤት ነው። ውይይቱ በእኛ መስሪያ ቤት ይጀመር እንጂ በአብዛኛው መሰል ችግር ያለባቸው ሀገራት በድብቅ ዲፕሎማሲ ግንኙነት ነው። በእኛ በኩል እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ተሞከረ፤ በሙከራ ላይ እንዳለን ፓርቲው በዚህ ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት ፈለገ፤ እኛ የሌለበት ድርጅት ጨርሶ ሊሆን አይችልም የሚል አቋም ተያዘ። በመካከል የፓርቲ ወኪሎች እንዲገቡበት ተደረገ፤ እነሱ ሲገቡ ደግሞ ውጭ ሆነው የሚደራደሩት የሽማቂው ቡድን አባላት ከእነዚህኞቹ ጋር መደራደር አልፈለጉም። ከዚያ በኋላ የጉዳዩ ባለቤት እንዲሆን ፓርቲው ጉዳዩን በበላይነት እንዲመራ ተደረገ። ብዙ ጊዜ ሙከራ ቢደረግም ግን ምንም መፍትሄ አልተገኘም። ለማንኛውም ድርድር የሃይል የበላይነት ወሳኝ ሚና አለው። ሃይል ካለ ጠላት ያጎነብሳል። የምንፈልገውን የመደራደሪያ ነጥብም ማስቆጠር እንችላለን። ያ ግን አልሆነም። እኛ ሃይል ባለን ጊዜ ያንን ወቅት መጠቀም አልቻልንም። ለምሳሌ በቀይ ኮከብ ዘመቻ ጊዜ የእኛ ሃይል ከሚገባው በላይ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ነበር። እንኳንስ ለአንድ ሽምቅ ተዋጊ ይቅርና ከዚያም የላቀ ሃይል ካለው አካል ጋር መጋፈጥ የሚችል ስለነበር ከውጊያ ይልቅ ሰላማዊ ድርድር እንዲኖር ሃሳብ ሲሰጥ እላይ ያለው አካል አሻፈረኝ አለ። ችግሩን በመከላከያ ሃይል ለመፍታት ነበር እቅዳቸው። ያ ባይሆን ኖሩ ድርድሩን እንዲቀበሉ ቢጠየቁ ኖሮ ያለንበትን ሁኔታ ያውቁ ስለነበር ምንም እንኳን መገንጠል የሚፈልጉ ቢሆንም በፌዴራል ሥርዓት መፈታት የሚችል እንደነበር ምንም የሚያጠራጥር አልነበረም። እንግዲህ ያ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ኤርትራም አትገነጠልም፤ ኢትዮጵያ የባህር ወደብም አታጣም፤ የኤርትራ ወገኖቻችንም ከእኛ አይነጠሉም ነበር። ስለዚህ ስህተት ተፈጥሮ ነበር ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ወቅት ባለመምረጣችን የተፈጠረ ነው። እውነቱን ለመናገር የነበረው መንግሥት ብዙ ነገር መልክ እንዲኖረው ሳይፈልግ አልቀረም። ግን መፈለግና ለማድረግ መቻል ወይም የአዕምሮ አቅምን መጠቀም መቻል የተለየ ነው። በዚህ ሁኔታ የምንፈልገውን ነገር ሳናገኝ ቀርተናል ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ማብራሪያ በአንባቢዎችና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ በላይ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ኩፍኝና አሁናዊ ደረጃው

ጽጌረዳ ጫንያለው

የኩፍኝ በሽታ ለሕፃናት ህመም፣ የአካል ጉዳትና ሞት ምክንያት ከሆኑት በሽታዎች አንዱ ነው። መነሻው የኩፍኝ ቫይረስ የሚባል ረቂቅ ተህዋስያን ሲሆን፤ በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው የሚዛመት የበሽታ ዓይነት ነው። በሽታው ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው የኩፍኝ በሽታ ከያዘው ሰው አፍንጫና ጉሮሮ በሚወጡ ፈሳሾች ንክክኪና በትንፋሽ አማካኝነት ነው።

በኩፍኝ በሽታ የተያዙ ሰዎች የበሽታው ምልክቶች መታየት ከጀመሩ በኋላ ባሉት ቀናትና ምልክቶቹ ከመታየታቸው ከበርካታ ቀናት በፊት ጭምር በሽታውን ወደ ሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ሆኖም የበሽታው አምጪ ተህዋስ ወይም ቫይረስ በከፍተኛ ሁኔታ የመሰራጨት አቅም የሚኖረው የበሽታው ምልክቶች መታየት በሚጀምርበት ወቅት እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

ሕፃናት በሚሰባሰቡበት ቦታ ማለትም በትምህርት ቤቶች፣ በጤና ተቋማት እና በሌሎች ቦታዎች በተለይም በሽታው በቀላሉ ሊዛመት ይችላል። በኩፍኝ በሽታ የተያዘ ሰው (ሕፃን) የሚያሣያቸው ዋና ዋና ምልክቶች ከፍተኛ ትኩሳት፤ ከራስ ፀጉር ጀምሮ ወደ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች የሚዛመት ሽፍታ፣ የዓይን መደፍረስ ወይም መቅላት፣ ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ መብዛት፣ የዓይን እንባ ማዘልና ሣል ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ።

ምልክቶች በማንኛውም ሕፃን ላይ ከታዩ ሕፃኑን በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋማት መውሰድ እንደሚያስፈልግ የሚጠቁሙት የዘርፉ ምሁራን፤ የኩፍኝ በሽታ መከላከል የሚቻለው ሕፃናትን በመደበኛ ክትባት መርሐ ግብር እና በዘመቻ መልክ የሚሰጠውን የክትባት አገልግሎት መጠቀም ሲቻል ነው። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ሕፃናት ከዘጠኝ ወር ጅምሮ በክትባቱ መሳተፍ አለባቸው። መደበኛ የክትባት መርሐ ግብሩንም ያለማቋረጥ መውሰድ ይገባቸዋል ሲሉ ይመክራሉ።


በኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶች የኩፍኝ በሽታ ወረርሽኝ ይከሰታል። በመሆኑም የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት በዘመቻ መልክ መስጠት አስፈላጊ ነው። እንደአገርም ተግባሩ በጊዜውና በወቅቱ እንደሚከወን በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚወጡ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህንን የኩፍኝ በሽታ ወረርሽኝ ችግር በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ብሎም በዘላቂነት ለመፍታት በየዓመቱ በአገር አቀፍ ደረጃ እድሜያቸው ከዘጠኝ ወር በላይና ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት እንዲሁም በተመረጡ አካባቢዎች ደግሞ ከዘጠኝ ወር በላይና ከ 15 ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት በዘመቻ መልክ ይሰጣልም።

የክትባት ዘመቻ የሚሰጠው በቋሚነት በተመረጡ ጤና ጣቢያዎች ፣ ጤና ኬላዎች ፣ ትምህርት ቤቶች እና በጊዜያዊ የክትባት መስጫ ጣቢያዎችም ነው። ምክንያቱም በዘመቻው ወቅት ማንኛውም ወላጅ ወይም አሳዳጊ በአካባቢው በሚገኝ የክትባት መስጫ ጣቢያ ሳይቸገር እንዲሄድና ሕፃናትን እንዲያስከትብ ያግዛልና ነው። በዚያ ላይ በአንድ ስፍራ ብዙ ሰው እንዳይሰበሰብና እንዳይጠጋጋ ስለሚያደርግ በሽታው ከአንዱ ወደ አንዱ እንዳይተላለፍ ለማድረግም ይረዳል።

የኩፍኝ በሽታው ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ዓለምአቀፍ መረጃዎች ያመላክታሉ። ክትባቱ ቢኖርም መከሰቻ አጋጣሚው ብዙ በመሆኑ ሁኔታው አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱንም የዓለም ጤና ድርጅት ጭምር ይገልጻል። እንደውም የኮሮና ተሐዋሲ መላ ዓለምን ሲያምሳት በአፍሪካ እንደ ኮንጎ አይነት አገራት ትልቅ አደጋ ውስጥ እንደነበሩም ተጠቁሟል።

ኮንጎ በዓለም ላይ ከተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ሞት የበለጠ ዜጎቿን በአንድ ቀን ውስጥ በኩፍኝ ወረርሽኝ ገብራ እንደነበርም ተዘግቧል። አዘጋገቡም እንደ አፍሪካ የተዘነጉ የመሰሉ በሽታዎች የሰዎችን ሕይወት መቅጠፍ ጀምረዋል ተብሎ ነበር። ይሁን እንጂ ይህም ሆኖ ትኩረቱ አናሳ ነበር።

በአንድ ወቅት በዓለም ጤና ድርጅት የአፍሪቃ የድንገተኛ መከላከል ክፍል ኃላፊው ሚኬል ያኦ ለፈረንሳይ ዜና አገልግሎት እንደገለጹት «በርካታ ሕጻናት ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ በሕይወታቸው ሙሉ አንዳችም ክትባት አላገኙም፤ ይሄም ነገሮችን እጅግ አስቸጋሪ ያደርጋል» ብለዋል። በእርግጥ በኩፍኝ ተሐዋሲ የሚያዙ ሕጻናት ቁጥር ከበፊቱ አንጻር መቀነስ ይታይበታል። ግን ክትባቱ



በኩፍኝ የተያዘ ሰው በቆዳ ላይ የሚታዩ ሽፍታዎች ይኖሩታል

የማይወሰድ ከሆነ አደጋው የከፋ እንደሚሆንም አንስተዋል።

እድሜያቸው ከአምስት ዓመት እስከ 16 ያሉትን ልጆች ለመከተብ የገንዘብ እና የክትባት እጥረት ከፍተኛው ተግዳሮት መሆኑን የጠቆሙት ሚኬል፤ ያልተከተቡ ልጆች ቁጥር መጨመር እና የክትባት እጥረት ምናልባትም ወረርሽኙ ይበልጥ እንዲስፋፋ ሊያደርግ ይችላል ሲሉም ስጋታቸውን ገልጸዋል።

የዓለምጤና ድርጅት እንዳስታወቀው፤ የኩፍኝ በሽታ በ79 በመቶ ጨምሯል። ሶማሊያ፣ የመን አፍጋኒስታንና ናይጀሪያም የችግሩ ሰለባ ናቸው።

በተያዘው ዓመት ማለትም 2022 ከጥር ወር ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ብቻ ከ19 ሺህ በላይ የኩፍኝ በሽታች ተከስቷል። በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ በኩፍኝ በሽታ የተጠቁ ሰዎች ብዛት ከአምናው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ79 በመቶ እንዲጨምር አድርጎታል።

ድርጅቱ በድረገጹ እንዳብራራው፤ የኩፍኝ በሽታ እንደ አዲስ አገርሽቷል። ለዚህ ደግሞ መንስኤው የኮሮና ቫይረስ እና ግጭቶች እንዲሁም የሰዎች መፈናቀል እና የጤና መሰረተ ልማት በጦርነት መውደማቸው ነው። በኢትዮጵያ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ 3 ሺህ 39 ሰዎች በኩፍኝ በሽታ የመጠቃታቸው ምስጢርም ይኸው ነው። 58 በመቶዎቹ ደግሞ የመጀመሪያ ዙር ክትባት ማግኘታቸው ተገልጿል።

በአብዛኛው ሕጻናትን የሚያጠቃው የኩፍኝ በሽታ ተላላፊ በሽታ ስለሆነ ተገቢው የሕክምና ክትትል ስላልተደረገለት ችግሩን በቀላሉ መግታት እንዳልተቻለም ተነስቷል። በበሽታው ላለመጠቃት አስቀድሞ ክትባት መውሰድም ይመከራል። ነገር ግን ተገቢውን የህክምና ክትትል ስላላገኘ የከፋ ጉዳት እስከማድረስ እየዘለቀ ነው። በሽታው በደንብ መታከም ካልቻለ ከመግደል ጀምሮ ዘላቂ ለሆነ የአዕምሮ ጉዳት፣ ለሳንባ ምች፣ ያለጊዜው ጽንስ መውለድ፣ ለመስማት ችግር እና ለሌሎች ጉዳቶች የሚያጋልጥ እንደሆነም መረጃው ያመላክታል። በፈረንጆቹ 2020፣ 20 ሚሊዮን ሕጻናት የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት መውሰድ እያለባቸው ያልወሰዱ በመሆናቸው አሁን ለተከሰተው የኩፍኝ በሽታ የራሱ አስተዋጽኦ ማድረጉንም ድርጅቱ በመግለጫዎቹ አስቀምጧል።

ክትባቱ ባለመሰጠቱ ምክንያት 73 ሚሊዮን የዓለማችን ሕጻናት የኩፍኝ ወረርሽኝ ሰለባ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስጠነቀቀው የዓለም ጤና ድርጅት፤ ሀገራት እና ዓለም አቀፍ የክትባት ኩባንያዎች ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጡም አሳስቧል።

የኩፍኝ በሽታ መከሰቻ አጋጣሚዎቹ ከላይ እንዳነሳነው በተለይ መፈናቀልና ግጭቶች ናቸው። ኢትዮጵያ ደግሞ አሁን ያለችበት ሁኔታ በብዙ መልኩ ይታወቃል። እናም ሰሞኑን የወጣው መረጃ ደግሞ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ እንዳለው፤ በሽታው በስፋት እየተሰራጨ መጥቷል። በተለያዩ ክልሎችም ወረርሽኙ ተከስቷል።

የኩፍኝ ወረርሽኝ በተለያዩ ክልሎች መከሰቱን ያነሱት የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ደረጀ ድጉማ ሲሆኑ፤ በ2014 ዓ.ም 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች በወረረሽኙ ተይዘዋል ብለዋል። ወረርሽኙ ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ብቻ 10 በመቶ እንደጨመረም ተናግረዋል። ወረርሽኙ በአምስት ክልሎች ማለትም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች እንዲሁም በሶማሌ ክልል በ45 ወረዳዎች ላይ መከሰቱንም አስረድተዋል። ይሁን እንጂ በእነዚህ አካባቢዎች በተሰሩ ፈጣን ምላሽ ሥራዎች አብዛኞቹን መቆጣጠር መቻሉን ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ በ 11 ወረዳዎች ወረርሽኙ መስፋፋቱን ያነሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በኢትዮጵያ በተከሰቱ የተለያዩ ምክንያቶች የኩፍኝ ክትባት ሽፋን ዝቅተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች የተከሰተውን የኩፍኝ በሽታ ወረርሽኝ የጤና ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከክልል ጤና ቢሮዎች እና አጋር አካላት ጋር በመተባበር ፈጣን ምላሽ የመስጠት ስራዎች እየተሰሩ ናቸውም ብለዋል።

ኩፍኝና መሰል ተላላፊ በሽታዎች በአገር ደረጃ የሉም የሚያስብላቸውን ሁኔታ ይዘው እንደነበር የሚያነሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ጠንካራ ክትትልና ሥራም ስለነበረ ለረጅም ዓመታት በሽታው ችግር ሳይሆን ቆይቷል። አሁን ግን በተለይም መከሰቻ አጋጣሚው ሰፊ በመሆኑ የመጨመር አዝማሚያ አሳየ እንጂ ይህንን መመከት አይቻልም አልተባለም። እናም በተጠና መልኩ ጠንካራ ክትትልና ሥራ ተደርጎበት መፍትሄ እንዲያገኝ እንደሚደረግም አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የተላላፊ በሽታዎች ህክምናን የሚፈታተኑ 10 ምልከታዎችን የሚዘረዝረውን ‹‹የጤና ወግ›› በሚል ርዕሰ ጉዳይ በዶክተር ትንሳኤ አለማየሁ የተጻፈውን አንድን ጽሁፍ እናስቃኛችሁና ጽሁፉን እንቋጭ። የመጀመሪያው ያለ ሀኪም ትእዛዝ መድሃኒት ገዝቶ መጠቀም ሲሆን፤ ብዙ ባለሙያዎች ባደረጉት ጥናት መሰረት ሕብረተሰባችን ያለ ሀኪም ትእዛዝ መድሃኒት የመጠቀም ልምዱ ከፍተኛ እንደሆነም ይናገራል።

ሌላው በባለሙያዎች መሀል ያለ የግንዛቤ እጥረት ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ 33 የህክምና ት/ቤቶች የተላላፊ በሽታዎች እና የፀረ ተህዋስያን መድሃኒቶች የድህረ-ምረቃ ሥልጠናን ለሀኪሞች የሚሰጠው የጥቁር አንበሳ የህክምና ት/ቤት ብቻ መሆኑንም ያስቀምጣል። እናም የሁለቱ አካላት ልዩነት ለጉዳት ሰለባ ከሚያደርጉ መካከል እንደሆነም መረጃው ያነሳል።

ሦስተኛው የመድሃኒት ዝውውር ቁጥጥር መላላት ሲሆን፤ የሀገራችን የመድሃኒት ዝውውር ቁጥጥር በቂ አይደለም። በሕገወጥ መንገድ የሚዘዋወሩ የፀረ ተህዋስያን መድሃኒቶች በአብዛኛው በሚመከረው መንገድ (ሙቀታቸው ተጠብቆ፣ የአገልግሎት ዘመናቸው ሳያልፍ ወ.ዘ.ተ.) ከአምራቹ ወደ ተጠቃሚው አይደርሱም። ስለዚህም ውጤታማ አይሆኑም።

አራተኛው የሚዲያው ለፀረ ተህዋስያን መድሃኒቶች መላመድ እና ውጤታማነት መቀነስ ትኩረት አለመስጠት ሲሆን፤ የፀረ ተህዋስያን መድሃኒቶች መላመድ በዓመት ውስጥ ከማንኛውም ህመም የበለጠ ታካሚዎች ይገድላሉ። ነገር ግን ሚድያዎች ይህንን ለማህበረሰቡ አያሳውቁም በሚባል ደረጃ ላይ ናቸው።

አምስተኛው ከፀረ ተህዋስያን ህክምና በፊት መሟላት ያለባቸው ምርመራዎች ትኩረት ሰጥቶ እንዲሟሉ አለማድረግ ሲሆን፤ እንደማንኛውም ህክምና የተላላፊ በሽታዎች ህክምና ከመሰጠቱ በፊት ለህሙማን ስላስከተለው ተህዋስ ተገቢው መረጃ በምርመራ መደረግ ይገባል። ነገር ግን በኢትዮጵያ ያሉ ሆስፒታሎች የፀረ ተህዋስያን መድሃኒቶች ግዢን እንጂ ምርመራ ላይ ትኩረት አያደርጉም። ይህ ደግሞ ለበሽታው ይበልጥ መስፋፋት መንስኤ ሆኗል።

መረጃው በስድስተኝነት የሚያነሳው የውሃ አቅርቦት አለመኖር ወይም መቆራረጥን ሲሆን፤ የተላላፊ በሽታዎች ህክምና እና መከላከልን በእጅጉ የሚፈትነው መሆኑን ይጠቁማል። “በሽታ ለመከላከል እጃችሁን በሳሙና እና በውሃ ታጠቡ” የዘወትር የህክምና ባለሙያዎች ምክር ቢሆንም ያን ለማሟላት በተለይ በህክምና መስጫ ተቋማት መቼም የማይቆራረጥ ውሃ መሟላት ግደታ ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ የለምና ችግሩ ይሰፋል።

ሰባተኛው የጤና መድህን አገልግሎት አለመስፋፋት ነው። በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደረው ሕብረተሰብ በሚታመምበት ሰዓት ሁለት አማራጮችን ይጋፈጣል። የመጀመሪያው ሆስፒታል በመሄድ ምርመራ አድርጎ መድሃኒት ገዝቶ መታከም ሲሆን፤ ሁለተኛው ቀጥታ ፋርማሲዎችን በመጎብኘት ያለ ሀኪም ትዕዛዝ መድሃኒት ገዝቶ መጠቀም ነው (ቢያድንም ባያድንም)። እናም ከገቢ ውስንነት የተነሳ ተላላፊ በሽታን መከላከል የማይቻልበት ምክንያት ይህ እንደሆነም ይነሳል።

ስምንተኛው የህክምና ባለሙያዎች እና የሚድያ መራራቅ ሲሆን፤ በሙያው የተሰማሩ ሰዎች በተለያዩ የሚድያ መድረኮች እየቀረቡ (በራሳቸው ተነሳሽነት) ሕብረተሰቡን አያስተምሩም። የተላላፊ በሽታዎች ህክምና በሀሰተኛ መረጃዎች ስህተት ከሚፈጠሩ በሽታዎች አንዱ በመሆኑ ይህንን እንዳያከሙም ያደርጋቸዋል።

የህክምና መስጫ ተቋማት ቁጥራቸው በበዛ ታካሚዎች እና አስታማሚዎች መጣበብም ሌላውና በዘጠነኛነት የሚነሳው ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የህክምና መስጫ ተቋማት ብዙ ታካሚዎች ያስተናግዳሉ። በተጨማሪም ቁጥራቸው በበዛ አስታማሚዎች ይጣበባሉ። ይህ ደግሞ ከታማሚው የተላላፊ በሽታዎች እና ተህዋስያን ወዳልታመሙ ሰዎች እንዲሄድ እና ታማሚውም ለሌሎች ህመሞች እንዲጋለጥ ያደርጋል።

የመጨረሻውና አስረኛው ከሀገሪቱ ነባራዊ የፀረ ተህዋስያን ህክምና ጋር ተዛማጅ የሆኑ ምርምሮች እጥረት ነው። ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የፀረ ተህዋስያን ህክምና ምርምሮች እጥረት አለ። ያሉትም ጥቂት ተመራማሪዎች በቂ ድጋፍ እና ማበረታቻ ያንሳቸዋል። እናም የተላላፊ በሽታዎች ህክምና ፖሊሲን መሰረት አድርገው እንዲሰራባቸው አይሆኑም። ይህ ደግሞ የበሽታው ተስፋፊነት ላይ የጎላ ሚና እንዲኖረው ያደርጋል።

# ነፃ ሃሳብ



በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የባሩድ ጭስ ሱሰኞች

**የምስለ ባሩድ ወግ፤**

ደጋግመን ከምንሰማቸውና ውስጣችንን እያወኩ ጤና ከሚነሱን "መንግሥታዊ ዜናዎች" መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው፤ "ይህንን ያህል የጦር መሣሪያ በሕገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር በቁጥጥር ሥር ዋለ" የሚለው ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል። "በባሩድ" የመስለነውም ይህንን አሳሳቢ ወቅታዊ ጉዳይ ነው። ለሕዝብ የሚደርሰውን እንዲህ አይነቱን መረጃ "ዜና" ብሎ ከመጥራት ይልቅ "መርዶ" ማለቱ ይቀላል። "ለምን ቢሉ?" በቁጥጥር ሥር በዋሉት የጦር መሣሪያዎች አማካይነት አዘዋዋሪዎቹ ሴረኞች የተመኙት ድርጊት ባይፈጸም እንኳን የመጓጓዙ ዓላማ የብዙዎችን ነፍስ ለመንጠቅ ታቅዶ ስለሆነ "እሳት ካየው ምን ለየው!" ነውና "መርዶ" ቢሰማኝ አያስከፋም።

"በሕገ ወጥ መንገድ ሲዘዋወር" የሚለው የተለምዶ አገላለጽም "ሕጋዊ የጅምላ የጦር መሣሪያ ዝውውርስ አሁን እያስተዋልን ባለው መልኩ ይፈቀዳልን?" ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን። ከሕጋዊ የጸጥታ ተቋማት አሠራር ጋር ለመለየት ታስቦ ከሆነም ይህ ጉዳይ ለሚመለከታቸው ተቋማት ኃላፊነታቸው ብቻም ሳይሆን የተሰጣቸው መብትም ጭምር ስለሆነ በማነጻጸሪያነት መቅረቡ "አግባብ ይሆንን?" ብለን ደግመን እንሞግታለን።

**የትውፊታችን መዘዝ፤**

የ "ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውሩን" የዜና አቀራረብ በተመለከተ በበርካታ ጉዳዮች ግራ ሲያጋቡን ለሚውሉት ለሀገራችን ሚዲያዎች እና "ዜናውን አስተላልፉልኝ" በማለት መልዕክቱን ለሚልከው ክፍል እንተወውና ወደ ዋናው ጉዳያችን እንመለስ። የሀገር ወግ ናቸው ብለን በእለት ተእለት ኑሯችን እንኮኮ እያልን ተሸክመንና በስሜታችን ጀርባ ላይ አዝለን እንደ በኩር ልጅ እሶሶ የምንላቸው የአንዳንድ ነባር ባህሎቻችን ጉዳይ እንዲህ በዋዛ የሚታረም ስላልሆነ ከዋናው ርእሳችን እንዳያርቀን በመስጋት ከመነሻ ርእሳችን ጋር የሚጎዳኘውን አንዱን ጉዳይ ብቻ ነጥለን እናስታውሳለን።

እንደ መርግ ተሸክመን ካጎበጡንና አልላቀቅ ብለው ከተጣቡን አንዳንድ የባህላዊ ትውፊቶቻችን መካከል በተለይም ከጦር መሣሪያ ጋር የተቆራኘንበት ፍቅር ወደር ያለው አይመስልም። ከገጠር እስከ ከተማ በመሣሪያ "ቃንዛ" (ጥዝጣዜ፣ ሕመም) ያልተለከፈ ዜጋ ይኖራል ብሎ ለማሰብ እስከሚያዳግት ድረስ "አፍቃሬ መሣሪያ" ሆኖ መታየት የብዙዎች መለያ ነው።

**"ገዳይ እወዳለሁ፣ ተኳሽም አልጠላ
ሲደክመኝ አርፋለሁ፣ በጎፈሬው ጥላ። "**

እየተባለ እስክስታ በሚወረድበት ሀገር እየኖርን ስለ "ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር" እና ስለ አፍቅሮተ መሣሪያ ምርር ብለን ብንተች ጅራፉ መልሶ የሚያንባርቀው በራሳችን ብዕር ላይ እንደሚሆን አይጠፋንም። "ና ደሞ ገዳይ! ገዳይ ደሞ!" እየተባለ በሰርክ የዘፈን ግጥም "ገዳይነት" በሚሞገስበት ሀገር እየኖርን "ሞት ቢረክስብን" ምን ያስደንቃል? እኛው በፈጠርነው ጉዳይ ፈጣሪን ማስቸገር አይገባም ካልተባለ በስተቀር አንዱ ፈውስ ፈላጊ ሕመምተኛው የባህላችን ክፍል ኪነጥበቡ ስለሆነ እግረ መንገዳችንን "ፈጣሪ እንዲፈውስልን" ተማጥኖ አኑረን ብናልፍ አይከፋም።

የጥንቶቹ ምንሽርና ዲሞትፎር ሳይቀሩ ዘመነ ሥልጣኔ በእርጅና ምክንያት ከውድድር ውጭ ካደረጋቸው በኋላና በተፈበረኩበት ሀገርም ሳይቀር ባይተዋር እስከ መሆን ደርሰው እያለ በእኛ ቀኤ ግን "እሹሩሩ" እየተባሉ በዜማ መሞገሳቸወ አልቀረም። በእነዚህ ምክንያቶች የተነሳም በባሩድ ጭስ መታጠንን አጥብቀን ስንኮንንም የምናገኘው ምላሽ "ሥራችሁ ያውጣችሁ" እንዳይሆን ሥጋት ገብቶናል።

ለጉድ በጎለታቸው አንዳንድ መንግሥታዊ ሚዲያዎች ሳይቀር "ገዳይ ደሞ" በሚል የዜማ አዝማች ተለብጦ አንድ የሕጻናት ወተት ማስታወቂያ በይፋ ደጋግሞ ሲተላለፍ እንደነበር አንዘነጋም። ቆሽታችን ደበነ አልደበነ ማን ግድ ሰጥቶት? ማስታወቂያው ዛሬም ድረስ እየተላለፈ ከሆነ በርግጥም እንደ ሀገር ለመደንቆራችን ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

በየቤታችን ያሉትን ሕጻናት የምናሳድግበት ወተት "በገዳይ ደሞ" ማስታወቂያ መድመቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ለልጆቻችን ልደት ወይም ለፍቅራችን መግለጫነት በስጦታ የምናበረክትላቸው መጫዎቻዎች ሳይቀሩ አርቴፊሻል ሽጉጦችና የዘመናዊ ጦር መሣሪያ አምሳያዎች መሆናቸውን በትዝብት የምናልፈው "ቤቱ ይቁጠረው" በማለት ነው።

ዛሬ በአርቴፊሻል የጦር መሣሪያ ስጦታ በደስታ የምናስፈነድቃቸው ልጆቻችን ነግ ተነገ ወዲያ ነፍስ ሲያውቁ በምሩ የጦር መሣሪያ ፍቅር ወድቀው ለመራር ለቅሶ ምክንያት ቢሆኑን ልንፈርድባቸው እንዴት ይቻላል? ልብ ቢኖረን ከሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ጋር ተያይዞ በአሜሪካ ትምህርት ቤቶች የሚፈጸመው የንጹሐን ተማሪዎች የእልቂት ትራጄዲ ትምህርት በሆነን ነበር።

**ከግል ገመና ወደ ሀገር ጉዳ፤**

ምልከታችንን ሰብሰብ እናድርግና "በባሩድ ጭስ" በመሰልነው የጊዜያችን ፈተና ጥቂት እንቆዝም። ሚዲያዎቻችንን ያጨናነቀው "የሕገ ወጥ" የጦር መሣሪያ ዝውውር "መርዶ" ለምን ሊበራከት እንደቻለ ጥናትን መሠረት አድርጎ በሚመለከተው ክፍል በኩል ሊደርሰን የሚገባው መረጃ ሩቅ ስለሆነብን እኛ የምንሰጠው መላምት "የቢቸግር መልስ" መሆኑን ልብ ይሏል።

ምክንያት አንድ፤ ተደጋግሞ እንደሚገለጽልን "በሕገ ወጥ" መንገድ የጦር መሣሪያዎችን የሚያጓጉዙት የሽብር ተልዕኮ የተጠናወታቸው የሰላም ፀር ተላላኪዎች ናቸው።

ምክንያት ሁለት፤ በሰላም ወጥቶ መግባት ያሳሰባቸው ዜጎች ለነፍሳቸውና ለንብረታቸው ሲሉ የጦር መሣሪያ አጥብቀው ስለሚፈልጉ ነው። ምክንያት ሦስት፤ ህሊናቸውን ለከንቱነት ያስገበሩ፣ ከሆዳቸው ውጭ የማያስቡና ጊዜያዊ ሀብት አጋብሶ በአቋራጭ ለመክበር የሚፈልጉ ዜጎች መበራከት ለጦር መሣሪያ ዝውውሩ እንደ ምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል። እነዚህ ሦስት መላምቶች በጥናት የተደገፉ ሳይሆኑ በይሆናል ግምት የተሰነዘሩ መሆናቸው ይሰመርበት።

ለማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ በፈጣን ዝውውር ላይ ያለው የጦር መሣሪያ ብዛትና ዓይነት እንኳንስ እኛን ተራ ዜጎች ቀርቶ ጉዳዩ ጉዳዬ ነው የሚሉ ተጠሪ መንግሥታዊ ተቋማትን ሳይቀር በእጅጉ እንደሚያሳስብ አይጠፋንም። በየጊዜው የምንሰማው "በሕገ ወጥ የሚዘዋወሩ" የጦር መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት በዜጎች ላይ ሊያሳድር የሚችለው ሥነ ልቦናዊ ተጽእኖ ቀላል እንደማይሆንም መገንዘብ አይገድም። ሽጉጦች፣ ክላሽንኮቭና የስናይፐር ጠብመንጃዎች፣ መትረየሶች፣ ብሬኖችና እነዚህ መሣሪያዎች የሚጎርሷቸው ጥይቶች፣ ቦንቦች ወዘተ. በመቶዎችና በሺህዎች (በተለይም ጥይቶቹ በሚሊዮን) ሲቆጠሩ ማየት ምን ዓይነት አሉታዊ ስሜት ሊፈጥር እንደሚችል መገመቱ አይከብድም።

**ሀገር በማፍረስ ያለ ሀገር መኖር የሚቻል መስሏቸው ከሆነ ጅልነት ነው። በንጹሃን ደም እጃቸውን እየተለቃለቁ መኖር እጥፍ ዋጋ እንደሚያስከፍል አልተገነዘቡት ከሆነም የእጃቸውን ሲያገኙ እውነቱን ይረዱታል። ዳሩ የሚያቅበዘብዛቸው የባሩድ ጭስ ሱስ ወደ ህሊናቸው እንዲመለሱ መች ያበረታታቸዋል**

በዚህ አስጨናቂና ክፉ ክስተቶች ቀለባችን ሆነው ኑሮው አቅል ባሳጣን፣ ፖለቲካውም ጨቅይቶ ድጥና ማጡ ስጋት ላይ በጣለን ወቅት፣ ማሕበራዊ ሚዲያውም ከጥቅሙ ይልቅ ጥፋቱ አይሎ "በአሉ ተባባሉ" ዐውሎ ነፋስ እየተነዳን ባለበት "ዘመነ ግርምቢጥ (ሀሰት የበዛበት)"፣ የሃይማኖት ክብር ተቃሎ "እግዚአታችን ፀባኦትን በሚነቀንቅበት"፣ ማሕበራዊ ተራክቦውም በጥርጥርና ባለመተማመን በተሳከረበት በዚህ ወቅት "መከራችን ያነሰ ይመስል" ይህንን መሰሉን "የጦር መሣሪያ የገፍ ዝውውር" "መርዶ" ቀን በቀን ማድመጡ "ወየው ለነገ!" አሰኝቶ ቢያሸብረን ሊፈረድብን አይገባም። ለከፋቱ ደግሞ የአዘዋዋሪዎቹ መኪኖች ታርጋ እንጂ እነማን እንደሆኑ ያለመገለጹም ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ጥፋቱ ተገልጦ አጥፊው መሸሸጉም ግራ ያጋባናል። ይመለከተናል ባዮቹ ክፍሎች አሳማኝ ነው የሚሉትን ምክንያት ቢያስረዱን ስሜታችን ገርገብ ሊል ይችላል።

**የባሩድ ሱሰኞቹ ግብ፤**

የባሩድ ሽታ ሱስ ከሌሎች ሱሶች እጅግ የከፋ ስለመሆኑ የእኛ ሀገር ተሞክሮ ለሌሎች ሀገራትም ሳይቀር በጥሩ ማሳያነት ሊጠቀስ የሚችል ይመስለናል። በረሃ ውስጥ ተወልደውና አድገው ለመከራችን ምክንያት የሆኑ "በሞት ንግድ ላይ የተሰማሩ" አሸባሪ ድርጅቶችን ታሪክ ወደ ኋላ ዞር ብለን ብንፈትሽ ያለምንም ጥርጥር መዳረሻቸን የባሩድ ሱሰኛ ብቻ ሳይሆኑ ሱሱ አልለቅ ብሎ የሚያቅበዘብዛቸው በሽተኞች መሆናቸውንም ጭምር እንረዳለን።

በባሩድ ጭስ ታጥኖ ሀገር ለማፈራረስ መሞከር እብደት ተብሎ ብቻ የሚታለፍ አይደለም። ሌላ ቃል ሊገልጻቸው ስለማይችል ይህንኑ የተለምዶ ቃል እንጠቀምና እነዚህ የባሩድ ጭስ አምላኪዎች ሀገርን የውጥር ይዘው ለመከራ የዳረጓት በእውነት የሕዝብ ጥቅም ግድ ብሏቸው ነው? በፍጹም።

ከባእዳን ጠላቶቻችን ጋር በማበር ሰላማችንን እያወኩ ያሉት የሽብር ቡድኖች ሲላቸው በሰሜን፣ አልሆን ሲላቸው በምዕራብ፣ የበረቱ ሲመስላቸው በደቡብ፣ ክንፋቸው ሲሰበር በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተፈናጠሩ የሽብር ተልእኳቸውን የሚያስፈጽሙት፣ ንጹሃንን እየጨፈጨፉና ንብረት እየዘረፉ በማውደም የሚያቅራሩት በርግጡ ለሕዝብ አርነት አስበው ነው? ወይንስ በጠላቶቻችን ማማለል ተማርከው? መልሱ አጭርና ግልጽ ነው።

ሀገር በማፍረስ ያለ ሀገር መኖር የሚቻል መስሏቸው ከሆነ ጅልነት ነው። በንጹሃን ደም እጃቸውን እየተለቃለቁ መኖር እጥፍ ዋጋ እንደሚያስከፍል አልተገነዘቡት ከሆነም የእጃቸውን ሲያገኙ እውነቱን ይረዱታል። ዳሩ የሚያቅበዘብዛቸው የባሩድ ጭስ ሱስ ወደ ህሊናቸው እንዲመለሱ መች ያበረታታቸዋል።

ስለ ሰላም እንዳያስቡ ስምሪት ሰጪዎቻቸው ጠላቶቻችን ከኋላ ሆነው ጠብመንጃ ደቅነውባቸዋል። ስለዚህ ምርጫው አንድና አንድ ነው፤ በተጠመቁበት የባሩድ ጭስ እየናወዙ ማለቅ። በቅርቡ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎችና በሶማሌ ክልላችን ውስጥ የመከነው "የጥፋት ኦፕሬሽን" ለዚህ እውነታ ጥሩ አብነት ይሆናል።

በባሩድ ጭስ ጉልበትንና አሸናፊነትን መመዘን እንኳን በቤታችን ውስጥ ለተፈለፈሉት አሸባሪዎች ቀርቶ በዘመናት ውስጥ ሀገሪቱን ለወረሩት ባዕዳን ጠላቶቻችንም ቢሆን አልበጃቸውም። የሚሻለው የጦር መሣሪያዎችን እየተሽሎከለኩ ለማቀበል የሚንደፋደፉ ዜጎች ወደ ህሊናቸው ቢመለሱና ለተዘረጋላቸው የሰላም እጅ በጎ ምላሽ ቢሰጡ ነው። ያለበለዚያ ግን እንኳንም በሌሊትና በድቅድቅ ጨለማ "አዩኝ አላዩኝ" እየተባለ በሕገ ወጥነት መሣሪያ ለሚቀባበሉት ቀርቶ በአዋጅና በትእቢት ዘመናዊ የጦር መሣሪያቸውን በመረከብና በአውሮፕላን እያጓጓዙ ሀገሪቱን ለመውረር ለሞከሩ ታሪካዊ ጠላቶቻችንም ቢሆን በፍርሃት መንበርከክን ስላልለመደብን የቤት ውላጅ የጥፋት ኃይሎች ወደ ቀልብያቸው ተመልሰው ውስጣቸውን ቢያደምጡና ለታሪክ ክብር ቢሰጡ መከራው ሊቀልላቸው እንደሚችል እንገምታለን።

ዜና ሳይሆን "መርዶ አከል" መረጃ የሚሰጡን የሚዲያ ተቋማትም አቀራረባቸውን ቢፈትሹ አይከፋም። "ዜና ላኪው" መንግሥታዊ ክፍልም ቢሆን "ይህንን ያህል ሺህ የጦር መሣሪያዎች በቁጥጥር ሥር ዋሉ" ብሎ ማስነገሩ ምን ፋይዳ ሊኖረው ታስቦ እንደሆነ ደጋግሞ ቢያስብበት አይከፋም። "እውነት የሆነ ነገር ሁሉ አይነገርም" እንዲሉ "መርዶው" ምን ተጽእኖ እንደሚያመጣ በአግባቡ ሊታሰብበት ይገባል። ለሕዝብ ሥነ ልቦና ጥንቃቄ ይደረግ የመልእክታችን ማሳረጊያ ነው። የተያዙት ግለሰቦችና ቡድኖችም ምን ሕጋዊ እርምጃ እንደተወሰደባቸው ቢገለጽልን እንጠላም። ወንጀሉን ገልጦ ወንጀለኛውንና ፍርዱን ማድበስበሱም ጥቅም ያለው አይመስለንም። ይሄው ነው። ሰላም ይሁን!

**ማረሚያ**

በትናንት እትማችን የተስተናገደው ነጻ ሃሳብ እርእስ "የብራና አረንጓዴ ጎርፍ " የተባለው በስህተት ስለሆነ ፤ ርእሱ "የብራ (ዝናብ የሌለበት) ጎርፍ " በሚል ይስተካከል። ለተፈጠረው የቴክኒክ ስህተት አዲስ ዘመን ይቅርታ ይጠይቃል።

# ቀልድ የጠራው ሞት



**አሥመረት ብሥራት**

ጥሩ የሆነ ጓደኛችን ሌላው ቀርቶ በጣም የምንቀርበው ጓደኛ ፍጹም ስላልሆነ የሚጎዳንን ነገር ሊናገር አሊያም ሲያደርግ ልንመለከት እንችላለን። እኛም ብንሆን ፍጹም እንዳልሆንን የታወቀ ነው። በዚህ ምክንያት የሆነ ሰውን ባልተገባ ሁኔታ የጎዳንበትን ጊዜ ማስታወስ ንዴትን መለስ ለማድረግ ጠቃሚ ነው። አንዳንድ ጊዜ፣ እጅግ በጣም አናዶን የነበረው ነገር ያን ያህል ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ እንዳልነበረ ከጊዜ በኋላ ስንገነዘብ ምናለ ያን ጊዜ ስሜቴን በተቆጣጠርኩ የሚያሰኝ አጋጣሚ ይፈጠራል።

ይሄንን ጉዳይ እንዳነሳ ያደረገኝ የጓደኝነት ልክ የሆኑ ጓደኛሞች በተራ ንዴት ያልተገባ ድርጊት ውስጥ መግባታቸውን ልነግራችሁ ስለወደድኩ ነው። መተያየታቸው ብቻ ደስታን የሚሰጣቸው፣ ለመጠራሪያቸው ሙሉ ስማቸውን መጥራት የሚከብድባቸው እገልዬ የሚለው ቃል ከአፋቸው የማይጠፋው፣ ነግቶ እስኪተያዩ የሚነፋፈቁ ጓደኛሞች ናቸው። ከጓደኝነት በላይ ጓዳ ሸፋኝ ገበና ሸሻጊም እንደሆኑ ይነገርላቸዋል።

በአብሮነት ጎዳና ለመጓዝ ፍቅር ያስተሳሰረው ጓደኝነት፣ ጊዜ እያጠበቀው መቻቻልን መተጋገዝን እያሳየ በጥሩ ፍቅር፣ ቀልድና ጨዋታ፣ ጥልና ኩርፊያ በሙሉ በጓደኝነት መስመር ውስጥ የሚያስጉዝ መንገድን በመቻቻል በደስታ ያሳልፋሉ።

አንዱ ሌላውን በክፉ አይን ለማየት ቀርቶ አጠገባቸው ያለ ሰው የአንዱ ስም በክፉ የሚያነሳውን መስማት ወባ እንደያዘው ሰው የሚያንቀጠቅጣቸው አገር ምድሩን የሚያስቀና የጓደኝነት መስመርን የሚጓዙ፣ ከአንድ ማህፀን የወጡ እስኪመስል ድረስ አብሮነታቸው የጠነከረ የእውነተኛ ጓደኝነት ተምሳሌት ናቸው።

**ተናፋቂው ጓደኝነት**

ጥር ወር 1996 ዓ.ም አዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 ነዋሪ አንዳንች አንከን የማይወጣለት ፍቅር ያላቸው ናቸው ይላል ለአመታት በመቀራረብና በመተሳሰብ የዘለቁት ጓደኛሞች ፍቅራቸው ለብዙሃን ምሳሌ ሆኖ ኖሯል። በመካከላቸው ያለው የእምነት ልዩነት፣ የህይወት ፍልስፍና አለመገናኘት፣ የቤተሰብ ሁኔታ አንድ አለመሆንና ሌሎቹም የጋራ ያልሆኑ መለያዎቻቸው ቢበዙም ከዚህ ሁሉ በላይ ገዝፎ የወጣ የጓደኝነት ፍቅራቸው ሁሉን አስረስቷቸው አንድ አድርጓቸዋል።

እንደ ብዙዎቹ እምነት የጓደኝነት ሙሉ ትርጉም ስፍራ ይዞ የሚታየውና ጎልቶ የሚንፀባረቀው በእነዚህ ሰዎች ነው። ሁለቱ ወዳጆች አብረው የሚበሉ አብረው የሚጠጡ ብቻ መሆናቸው አይደለም ጓደኛ የሚለውን ስያሜ ያሰጣቸው። ሁለቱም አብሮ ከመብላትና ከመጠጣት ያለፈ የህይወታቸውን ክፍተት የሚሞሉበት ፍቅርእና መተሳሰብ ያላቸው መሆኑ ነው።

አንዱ ሲቸግረው ሌላው ይደርስለታል። አይዞህ ካለን ላይ ተካፍለን ብሎ ያጽናናዋል። የጎደለውን ሞልቶ የነበረ የጓደኛውን ስሜት ይመልሳል። አንዱ ሲጨንቀው ሌላው እያየው አንዱ ደስ ሲለው ከሌላው እየተካፈሉ እየተጋሩት ኖረዋል። መወለድ ቋንቋ ነው እስከሚባል ድረስ ሁለቱ ወዳጆች አምሳልነታቸውን አንድ አድርገው ዘልቀዋል። አመታትን የተሻገሩትና የወዳጅነት ዘመን ቱርፋታቸውን የተቋደሱት በመካከላቸው ባለው ፍቅርና መቻቻል ነው። ለዚህም ይሆናል አንዱ ሌላውን ጓደኛዬ ነው የሚለው ቃል የማይገልፅለት የማይመስለው።

ብዙዎች የእነዚህን ወዳጅነትና ፍቅር ይቀኑበት ነበርና የአብሮነታቸውን ሳይንስ ለማወቅ ይጥሩ ነበር። ከሁለቱም ጋር የቅርብ እውቂያ የነበረው ወጣት ጓደኛሞቹን አንድ ያደረጋቸው ነገር ሁለቱም ቀልድና ጨዋታ መውደዳቸው ነው። ቀልድና ጨዋታ ከመውደዳቸው የተነሳ እንደ ህፃን ልጅ ይላፉሉ፣ ይደባደባሉ። ሰዎች እስኪገርማቸው ድረስ አይለያዩም። እንዲያውም አንዱ አንዱን ካጣው ሳላይህ ስውል ትናፍቀኛለህ የሚባባሉ ወጣቶች ናቸው።

ይህ ቅርርባቸው አንዱ ሌላውን የራሱን ያህል እስኪያውቀው ድረስ ልብ ለልብ ያጣመራቸው ሁኔታም ነበር። የሚያውቋቸው አልፎ አልፎ ቢጋጩም ፀባቸው ብዙም አይከርም ይሏቸው ነበር። ሁለቱም ለሳቅና ለጨዋታ ቅርብ የመሆናቸውን ያህል ለኩረፊያም ቅርብ ናቸው። ነገር ግን ኩርፊያቸው እራሱ የቀልድ ስለሆነ የሚያመር አልነበረም። ለምን አኮረፍከኝ ብሎ መጠያየቅም ሆነ ሽማግሌ መካከላቸው ማስገባት ብሎ ነገር አልነበረም። እንደ ወንድማማች ወይም ታላቅና ታናሽ ይጋጫሉ መልሰው ይነጋገራሉ። ኩርፊያው ውሎ አያድርም፣ ቂም አያስቋጥርም።

**ክፉ ቃል**

ጥር 23 ቀን 1996 ዓ.ም ቀን ላይ ሁለቱም ከየዋሉበት መጥተው ተገናኙ። የዋሉበትም እዛው ቀበሌ 15 ክልል ኬር ኢትዮጵያ እርዳታ ድርጅት አካባቢ ነው። ቀናቸውን የቀጠሉት በተለመደው ፍቅርና በወዳጅነት ስሜት ነው ። የሚያውቋቸው ሰዎች በሁለቱም ላይ ከወትሮው የተለየ ስሜት እንደላዩባቸው ይናገራሉ።

ሁሉም ነገር እንደተለመደው ነበር፣ የተለመደው ሳቅ፣ የተለመደው ጫወታ፣ የተለመደው ልፊያ፣ የተለመደው መጎነታተል አለ። ያያቸው ማንነታቸውን እንኳን ከማወቁ በፊት የአብሮነታቸው ፍቅር ከፊታቸው የሚቀዳባቸው ሁለቱ ጓደኛሞች ዛሬም ከቀኑ አስር ሰአት ያሳለፉት ከወትሮው ባልተለየ ሁኔታ ነበር። መጨረሻ ላይ ግን አንድ ቃል ከሁለት ፍቅር መሃል ጥልቅ አለች።

"ሸፋፋ" የምትል ቃል ነበረች። ተናጋሪው የዘወትር ንግግሩን ውጤት እየጠበቀ ከፈገግታና ከተለመደ ጫወታ ውስጥ ነው። አንደኛው እግሩ በመጠኑ ዞር ያለ መሆኑን አይቶ ነው ሌላውን ሸፋፋ ብሎ የሰደበው። በእርግጥ ከዚህ ቀደም ይሄንን ቃል ተጠቅሞት አያውቅም ነበር። ተሰዳቢው ሸፋፋ የሚለውን የቀልድ ስድብ ሲያዳምጥ ውስጡ አንዳች ቁጣ የተተራመሰ መሰለው።

ዘወትር እንደሚያደርጉት ለመተራረብ ነውና ተናጋሪው ከአፉ ላወጣው ቃል ትኩረት አልሰጠውም። የጓደኛውን ስሜት ይጎዳል ብሎም አልጠረጠረም። ነገር ግን እቺ ክፉ ቃል በልቡ ውስጥ ቤት ሰርታለች። የጥላቻ ቤት፣ የመጠላላት ቤት። ሆኖም የእለቱ የፍቅር ውሏቸው ተቋጨና ተለያዩ። ተናጋሪው በውስጡ ነገን እየናፈቀና አብረው የሚውሉበትን ሰአት እየጠበቀ ወደ ቤቱ ሲገባ "ሸፋፋ" የተባለው ደግሞ ከራሱ ጋር እያወራና ብስጭቱ ያመጣበትን ግልፍተኝነት ለማረጋጋት እየሞከረ ሄደ። ጥቂት ሰአታት አለፉ።

**የሞት ጥሪ**

ተናጋሪው ሰው ከቤቱ ወጣ፣ አወጣጡ ሚስቱና ልጁን ሰላም ብሎ ወደ ጎረቤት ለመሄድ ነበር፣ ምክንያቱ ደግሞ ቴሌቪዥን ለማየት ነው። በቤቱ ቴሌቪዥን ስላልነበረ ጎረቤት ወዳለ ጓደኛው ዘንድ ቴሌቪዥን ለመመልከት ሄደ። እዛም እየተጫወተና ቴሌቪዥን የሚተላለፈውን ሙዚቃ እየኮመኮመ ቁምነገር ዜናውን እያደመጠ ቆየ። ቀኑ እየመሸ ነበርና ልቡ ወደ ቤቱ በመሄድና እዛው በመቆየት መካከል ነበር።

ልቡ በልሂድና በአልሂድ መካከል ሲወላውል ከውጭ የተጠራ መሰለው። የትንሽ ልጁ ድምፅ ነበር።" አባዬ ና ትፈለጋለህ" አለው። ይህን የአስር አመት ህፃን የላከው የአባቱ የልብ ጓደኛ የሆነው ያ"ሸፋፋ" የተባለው ሰው ነው። በልቡ ያሰበውን እኩይ ተግባር አንግቦ ወደዚህ ወዳጁ ቤት ሲመጣ በዛ እሳት በለበሰ ስሜቱ ሆኖ የፈለገውን ማግኘት አልቻለም። የሰውየው ሚስት ባልሽ የት ሄደ? ተብላ ስትጠየቅ ነገሩ ስላላማራት ቤት እንደሌለ ተናገራች። ምንም የማያወቀው የአስር አመት ህፃን ልጅ ግን ብቅ ብሎ ጎረቤት ቴሌቪዥን ሊያይ ሄዶ ነው በማለቱ ጥሪው ተብሎ ተላከ።

የሚፈልገው ሰው ማን እንደሆነ ለማየት ብቅ ያለው ወጣት ጓደኛው መሆኑን ሲመለከት ተናገረ። "ምነው በሰላም ነው አብረን ውለን የፈለግከኝ" ብሎ በመጠየቅ ወደ ቆመበት ተጠጋ። ይህ ሁሉ ሲሆን ሚስትና ህፃን ልጅ ቆመው ይመለከታሉ።

ወደ ጠሪው ሲቃረብ ያ ጥሩልኝ ያለው ወጣት በጥፊ ተቀበለው። እራሱን ለመከላከል ሙከራ በሚያደርግበት ወቅት ደግሞ ያላሰበውን ጩቤ ከጎኑ አውጥቶ አንገቱ ላይ ሽጦበት ሩጦ ሄደ። ልጁና ሚስቱ በሁኔታው ተደናግጠው ሲጮሁ የተወጋው ሰው ጥቂት ለመንገታገት ሞክሮ ባለመቻሉ በቁሙ ተዘረረ። ጎረቤቶች ጩኸት ሰምተው ሲወጡ ከተጎጂው አንገት ስር የመጣው ደም አካባቢውን ሞልቶት ነበር። ወደ ህክምና ሊወስዱት ሲያነሱት ግን ህይወቱ አልፋለች።

ማንም ባላሰበውና ባልገመተው ሁኔታ ገዳይ «ሸፋፋ» አለኝ በሚል ምክንያት ቤቱ ገብቶ ጩቤ ታጥቆ ለገድያ መውጣቱ ብዙዎችን አስገርሟል። ቀናቸውን በመተራረብና በመሳሳቅ የሚያሳልፉ ሁለት ጓደኛሞች በግድያ የቆየ የወዳጅነት ፋይላቸውን እስኪዘጉ ድረስ ጓደኛው ገደለው መባሉ ለብዙዎቸ እንቆቅልሽ ሆኖ ነበር።

ተጠርጣሪው ከሸሸበት በህዝብ ትብብር ተይዞ ሲጠየቅ "በፈለገው ነገር በቀልድ ምንም አይመስለኝም ነገር ግን እንዴት በተፈጥሮዬ ይቀልዳል" አለ። ሁሌም የለመዱት መተራረብና መሰዳደብ ለዚህ ላልታሰበ ድርጊት ያደርሳቸዋል ብሎ የጠረጠረ አልነበረም። ሟችም አገር አማን ብሎ የተቀመጠ እንኳን በጓደኛ በሌላ ሰው እጠቃለሁ ብሎ የማያስብ እንዲሁም እስከመጨረሻ ለገዳዩ የነበረው ፍቅር ያልቀነሰ ምስኪን ነው።

በአንዲት ቃል ህይወት ጠፋ። የጓደኛው ሞት ያሳዘነው የሚመስለው ገዳይ "ሳላስበው ሰይጣን አሳስቶኝ ያደረኩት ነገር ነው" አለ። የሁለቱ ፍቅር በመቃብርና በእስር መደምደሙ ግን ግድ ሆነ። እናትና ልጅም ፊታቸው እያዩት የተነጠቁትን አባወራቸውን አፈር አለበሱ።

**ሁለቱ ወዳጆች አብረው የሚበሉ አብረው የሚጠጡ ብቻ መሆናቸው አይደለም ጓደኛ የሚለውን ስያሜ ያሰጣቸው። ሁለቱም አብሮ ከመብላትና ከመጠጣት ያለፈ የህይወታቸውን ክፍተት የሚሞሉበት ፍቅር እና መተሳሰብ ያላቸው መሆኑ ነው**

## ውሳኔ

በበቂ ማስረጃዎችና መረጃዎች ተጠናክሮ የቀረበለትን ክስ ሲመረምር የቆየው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በተከሳሹ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ ለማሳለፍ በቀጠሮ ተገኝቷል። ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል ተከሳሹ በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ መሆናቸውን አረጋግጦ የክስ መከላከያቸውን እንዲያቀርብ ዕድል ሰጥቷል። ተከሳሹም ሰይጣን አሳስቶኝ ነው ከማለት በስተቀር ስለ ወንጀሉ ፈጽሞ አላስተባበለም።

ፍርድ ቤቱ በዕለቱ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ሁለቱ ባልንጀሮች በአጋጣሚ ግጭት አንዱ አጥፊ አንዱ ጠፊ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ገዳይ እጁ ከተያዘበት ጊዜ አንስቶ በሚታሰብ የ12 ዓመት ጽኑ እስራት «ይቀጣልኝ» ሲል ውሳኔውን በማሳለፍ መዝገቡን ዘግቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## አጋጣሚን ለለውጥ መነሻ

ተገኝ ብሩ

ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ማድረግ የሚፈልጉት አልያም መተግበር የሚያልሙት አቢይ ጉዳይ ይኖራቸዋል። ይህ ጉዳይ የሰዎች የዘወትር ሕልም አልያም ማሳካት የሚፈልጉት ዓላማና ግባቸው ነው። ይህን ግብ ደግሞ ሰዎች የመጨረሻ የስኬታቸው ጥግ አድርገው ሊወስዱት ይችላሉ። በዚህም ሐሴትን እንጎናፀፋለን ብለው ያምናሉ። ዘወትር የሚያልሙት ሕልማቸውና ብርቱ መሻታቸው ከተሳካ፤ የደስታ እርካብ ላይ የሚያደርሳቸው ይመስላቸዋል። በዚህም ዓላማቸውን ለማሳካት አልያም ግባቸው ላይ ለመድረስ ያገኙትን ሁሉ አጋጣሚ ይጠቀማሉ።

ለዓላማቸውና ለግባቸው መሳካት የማይፈነቅሉት ድንጋይ፤ የማይቧጥጡት ተራራ አይኖርም። ታዲያ ሰዎች ለግባቸው መሳካት ጥረት የሚያደርጉት ሁሌም አስበውና እቅድ አውጥተው ላይሆን ይችላል። ለዚህ ግባቸው አልያም እቅዳቸው መሳካት አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ትግል ያደርጋሉ። ትልቅና ወሳኝ ያሉት መሻታቸውን ለማሳካት ጥረት ያደርጋሉ። ወደዚያ የሚያደርሳቸው የትኛውንም አጋጣሚ ለመጠቀም ይሞክራሉ።

ለዚህ ደግሞ ውስጣዊ የሆነ የተለየ ግፊት ያድርባቸዋል። ይህ ደግሞ ለግባቸው መሳካት ትልቅ አቅምና እድል ይፈጥርላቸዋል። ይህ አቅም የፈጣሪ ስበት ነው። ስበቱ ደግሞ ብርቱ ፍላጎትና ምኞታችን የፈጠረው በጥረታችንና ትጋታችን የፋፋ ኃይል የሚፈጥርልን ልዩ ሚስጥር ነው። የኛው የሆነ ነገር ግን የማናውቀው የሚያበረታን ኃይል፤ ጥረታችንን የሚደግፍ ፍላጎታችንን ለማሳካት ስንኳትን የሚረዳን ነው።

እኔ በዚህ አጥብቄ አምናለሁ። ሰው ማሳካት የሚፈልገውን ነገር ለማሳካት ሁሌም ይማስናል። ያገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ወደዚያ እንዲያደርሰው ይተጋል። አውቆም ይሁን ሳያውቅ ወደመሻቱ ለመቃረብ ሁሌም ይጥራል። አንድ ሰው ግቡን ለማሳካት በጣረ ቁጥር ወደ መሻቱ ይበልጥ ይሳባል። በዚህ ውስጥ አንድ ነገር ማንሳት ፈለኩ።

እኛ እንደዜጋ ለሀገራችን በጎ ነገርን አጥብቀን እንመኛለን። ለሀገራችን ሰላምና እድገት፣ ለሕዝባችን ለውጥና ስምረት እንዲቃረብ እንጓጓለን።

ይህ መሻታችን ደግሞ ወደፊት ልናየው የምንፈልገውን ብሩህ ገፅታ ያስናፍቀናል። የሚገጥሙንን መሰናክሎች ሁሉ ተቋቁመን ወደፊት የተለወጠና ህዳሴውን ያረጋገጠ ማኅበረሰብ እንዲሁም ሀገር እንዲኖረን ከተመኘንና ለዚህም የጋራ የሆነ መሻት ውስጣችን ካሳደርን ተግባራዊ ማድረጉ የሚከብድ አይመስለኝም። እንደ አገር ማሳካት የምንፈልጋቸው ትልልቅ ጉዳዮች፣ ልንደርስባቸው የምንፈልጋቸውን በጎ ገፅታዎች ለማሳካት የጋራችን ሆነው ለግብ ያንደረድሩን ዘንድ መሥራት ይኖርብናል።

በእርግጥ የበዙ ጉዳዮች ላይ እናብራለን። በጎም ክፉም የተባሉ ጉዳዮቻችን ላይ በአንድነት ስቀናል፤ አልቅሰናልም። ይህ አብሮነት የጋራ ግብ እንዲኖረን ወደፊት የምንደርስበት ሀገራዊ ህዳሴ እንዲሳካ ጥሩ መሠረት ነው። ይህ አንድነት ወደምንፈልገው ነገር ለመሳብ ጥሩ እድል ይፈጥራል። የጋራ እቅድ ወጥነን፣ ልንደርስበት የምንፈልገው ሀገራዊ በጎ ገፅታ ተረድተን ካበርን ማሳካት እጅጉን ይቀላል።

ለግባችን መሳካት አንድ ሆኖ መቆም ያሻል። በአንድነት ውስጥ የሚገኘው ኃይል ደግሞ ብርቱ ነው። በዚያ አንድ ሆነን በመቆማችን ውስጥ የምንቀዳጀው ድል ይቃረብ ዘንድ ደግሞ ልዩነትን አጥቦ ወደ መግባባት የሚያቃርብ ሀሳብ እናራምድ። በጎ ነገራችን ላይ ትኩረት እናድርግ። ይህቺን ታላቅ ሀገር፣ ይህንን ሰፊ ሕዝብ ይዘን እንዴት አንድ ሆኖ መቆም ተሳነን ብለን እራሳችንን እንውቀስ። የሃሳብ ልዩነት በብዝኃነት ውስጥ ተፈጥሯዊ ነው። ይልቁንም የጋራ ሆነ ነገራችን ከሚያለያየን እጅጉን ይሰፋልና እዚያ ላይ እናተኩር። በጎው ላይ በጋራ እንረባረብ። የጋራ የሆነ ግብ አስቀምጠን፤ የጋራችን የሆነችው አገራችንን እናሻግር። ወደፊት ማሳካት የምንፈልጋቸው ብርቱ ሀገራዊ ጉዳዮችን እውን ለማድረግ አንድ እድር የሚያቆሙን ትልልቅ ሀሳቦችን እንከተል።

ስለ ሀገራችን ያለን ልዩ ስሜትና ሀገራዊ ፍቅር ትርጓሜው ጥልቅ ነው። ኢትዮጵያዊ አገሩን ለመውደዱ ማሳያ ከሰሞኑ ሁነቶች ውስጥ እንዱን መዞ ማየት በቂ ነው። ኢትዮጵያውያን አገር መውደዳቸውና ለሀገራቸው አንድ ሆነው መቆማቸው ማሳያው ብዙ ነው። የትላንት በስቲያው ግን ይለይ ነበር። የሆነ ለየት ያለ ስሜት። የአንዳችንን ሐሴት ሌላችን ላይ የሚያጋባ ድንቅ ስሜት።

ሳናውቀው ከውስጥ ፈንቅሎ የወጣና ስለሀገር ያለንን ልዩ ስሜት ያንፀባረቀ ሁነት። ከትላንት በስቲያ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች በደስታ ተፍለቅልቀው፣ በጀግኖች አትሌቶታችን ድል ፈክተው፣ በነዋሪዎች አሸብርቀው አርፍደዋል። በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ተሳታፊ የነበረው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን ከዚህ በፊት ከነበሩት የዚህ አይነት የውድድር ተሳትፎዎቹ የተሻለ ውጤት ይዞ በመመለሱ የተደረገለት ደማቅ አቀባበል፤ የሕዝባችን ደስታ መናፈቅ ቁልጭ አድርጎ ያሳየን ክስተት ከመሆኑ ጋር አንድ ነገር እንዳስብ አደረገኝ።

እንዲህ በአንድነት የምትሰበስብን አንድ ሆነን የምንዘምርላት፤ ያለ ልዩነት ድሏን ስንሰማ የምንደሰትባት ሀገር እያለችን ስለምንድነው ፍካቷ እንዳይቋረጥ ማድረግ የተሳነን? ብዬ አሰብኩ።

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያዊ ለአገሩ ያለው ጥልቅ ስሜት እንደዚህ አይነቱ ገጠመኝ በሚፈጠርበት ጊዜ ነው የሚለየው። እኛ መልካችን ሁለት ነው፤ በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ላይ ፍንትው የሚል ገፅታ አለን። አንድም ሀገር በጠላት ተጠቃች ሲባል ያለ ልዩነት ዘራፍ ለሀገሬ ብለን በአንድነት ቆፍጠን ማለታችን። ሁለትም ልክ እንደሰሞኑ በተለያየ አጋጣሚ ድል ተቀዳጅተን ብስራቱን ስንሰማ አጋጣሚው ወደ አንድነት ያስጉዘንና በጋራ መፈንጠዛችን፤ ድላችን ማጣጣማችን።

ክፉ በሰማ ጊዜ ስለአገሩ ተንበርክኮ የሚለምን ሀገር ወዳድ ሕዝብ ያላት አገር፤ የድል ዜና ሲሰማ አልያም ባንዲራውን ሲመለከት ተንበርክኮ በፍቅር የሚያነባ ትውልድ የሞላባት ታሪካዊት ሀገር፣ የለውጧ መሠረት የሆነው አንድነት ላይ መታጠቅ እንዴት ይሳነን? እንደ ዜጋ መጠየቅ ያለብን ዋንኛ ጉዳይ ይህ ነው። አንድ ሆነን ቆመን ማሳካት የምንፈልገው ሀገራዊ ግብ ላይ እንድንደርስ ዘንድ፤ አልፎ አልፎ የሚታዩና እኛ የምንፈጥራቸው ልዩነቶች ሳይሆን አንድ አድርጎ የሚያዘልቁን ላይ ትኩረት እናድርግ።

ሁነቶች ውስጥ የሚንፀባረቀው አንድ መሆናችን ነው። የእኛ እውነተኛ ማንነትና ባህሪ ነው። ይህንን ነው ኃይል አድርገን መጠቀም ያቃተን። ይህንን ነው ወደምንመኘው ሁለንተናዊ ለውጥ የሚያዳርስ ገፊ ጉልበት ማድረግ ያቃተን። ያለንን መጠቀም ያቃተን የሌለንን ማቅረብ እንዴት ይቻለናል?። ዛሬ ድረስ አብሮነታችን እንዲደረጅ ያደረገው የአንድነት መንፈስ ለጋራ ግባችን መሳካትና ለሀገራዊ ሁለንተናዊ ለውጥ መስፈንጠሪያ ማድረግ ብንችል አስባችሁታል? ውጤቱ ያጓጓል። በዚህ መንፈስ በአንድነት ስለ ሀገራችን የምናደርገው ያልተቋረጠ ጥረትና ጽኑ ፍላጎታችን የሚፈጥረው ልዩ ኃይል የኢትዮጵያን ህዳሴ የሚያረጋግጥ ይሆናል።

# ዓለም አቀፍ

## ዢ እና ባይደን በታይዋን ጉዳይ የማስጠንቀቂያ ቃላትን ተለዋወጡ

የአሜሪካ እና የቻይና መሪዎች በታይዋን ጉዳይ ለሁለት ሰዓታት በዘለቀ የስልክ ንግግራቸው አንዳቸው ሌላኛውን አስጠነቀቁ። ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን አሜሪካ የታይዋንን የህልውና ጥያቄን የሚቀይር የተናጠል እርምጃን አጥብቃ እንደምትቃወም ለቻይናው አቻቸው ዢ ዢንፒንግ ተናግረዋል።

ባይደን አሜሪካ ታይዋንን በተመለከተ ያላት ፖሊስ እንዳልተለወጠም ለቻይናው መሪ ተናግረዋል። ዢ በበኩላቸው ባይደን 'የአንድ ቻይናን መርህ' እንዲያከብሩ ካሳሰቡ በኋላ፤ "ማንኛውም በእሳት የሚጫወት መቃጠሉ አይቀርም" ሲሉ ባይደንን ወርፈዋል። የአሜሪካ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ናንሲ ፔሎሲ ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ወደ ታይዋን ሊያቀኑ ነው መባሉን ተከትሎ በሁለቱ አገራት መካከል ውጥረት ነግሷል።

ቻይና እንደ አንድ የራሷ ግዛት አድርጋ የምታየት ታይዋን ከዋሽንግተን ዲሲ ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ማጠናከሯ እረፍት ይነሳታል። ምንም እንኳ እስካሁን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አፈ ጉባኤዋ ወደ ታይዋን እንደሚጓዙ ይፋ አይደለም ቢልም፤ ቻይና ፔሎሲ ወደ ታይዋን ከተጓዙ፤ መዘዙ ከባድ ነው ስትል አስጠንቅቃለች።

የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ዛሆ ሊጂአን ፔሎሲ ወደ ታይዋን የሚጓዙ ከሆነ፤ አገራቸው "ጠንካራ እርምጃ" ትወስዳለች ሲሉ አስጠንቅቀዋል። የቻይና መከላከያ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ደግሞ ቤጂንግ ወታደራዊ እርምጃ ልትወስድ እንደምትችልም ጠቁመዋል።

"የአሜሪካ ወገን በዕቅዱ የሚቀጥል ከሆነ፤ የቻይና ጦር ዝም ብሎ አይመለከትም። የውጭ ጣልቃ ገብነትን ለማስቆም እና ተገንጣይ ኃይሎች 'ነጻ ታይዋንን' ለመፍጠር የሚያደርጉትን ጥረት ለመቀልበስ ጠንካራ እርምጃ ይወስዳል" ሲሉ ኮሎኔል ታን ኬፊ ለቻይና ዴይሊ ተናግረዋል።

ፔሎሲ፤ የራስ ገዝ ግዛት ወደሆነችው ታይዋን ጉዞ ቢያደርጉ ከእአአ 1997 ወዲህ ታይዋንን የጎበኙ ከፍተኛ ባለሥልጣን ያደርጋቸዋል። ታይዋን ራሷን እንደ ሉዓላዊ ግዛት ብትቆጥርም ቻይና ግን እንደ ተገነጠለች ግዛቷ ነው የምትመለከታት። ቻይና አስፈላጊ ከሆነም በኃይል ታይዋንን መልሳ የግዛቷ አካል ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማትል ከዚህ ቀደም ገልጻለች።

ምንም እንኳ አሜሪካ ታይዋንን እንደ ሉዓላዊት አገር ባትቆጥራትም፤ በዴሞክራሲያዊ መንግድ የተመረጠው መንግሥት እራሱን መከላከል እንዲችል በሚል የጦር



መሳሪያዎችን በሽያጭ መልክ ታቀርባለች። ከትናንት ወዲያ ሐምሌ 21 ቀን 2014 ዓ.ም. ሁለቱ ኃያላን መሪዎች በስልክ በነበራቸው ንግግር ፊት ለፊት ተገናኝቶ መነጋገር ስለሚቻልበት ሁኔታ መወያየታቸውን የባይደን አስተዳደር ከፍተኛ ኃላፊ ተናግረዋል።

ይህ መሪ ባይደን እና ዢ ያደረጉትን የስልክ ንግግር "ቀጥተኛ እና ሐቀኛ" ሲሉ ገልጸውታል። ሁለቱ መሪዎች ከታይዋን በተጨማሪ በከባቢ አየር ለውጥ እና የጤና ደሕንነትን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረዋል ተብሏል። ቻይና እና ታይዋን የተለያዩት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሲሆን በጊዜው ቻይና ራሷ በአንድነት መንግሥት እና በኮሚዩኒስት ፓርቲ መካከል ለሁለት ተከፍላ ጦርነት ላይ ነበረች።

በአውሮፓውያኑ 1949 ኮሚዩኒስት ፓርቲ ድል ሲቀዳጅ የወቅቱ መሪ ማኦ ዜዱንግ ቤይጂንግን መቆጣጠር ቻሉ። ሽንፈትን ያስተናገዱት የብሔራዊ ፓርቲው ደጋፊዎችና መሪዎች ታይዋን ሸሽተው ገቡ። የፓርቲው መሪ ቻንግ ካይ ሼክም ታይዋንን መደበቂያቸው አደረጓት። ትንሽ ቆይተውም ኩሚ ታንግ የተባለውን ፓርቲ እዚያው ታይዋን ውስጥ መሠረቱ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ታዲያ ይህ ፓርቲ ታይዋን ውስጥ ወሳኝ የሚባል የፖለቲካ ክንፍ ሆኖ መቆየቱን የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## የሳዑዲው ልዑል የፈረንሳይ ጉብኝት ቁጣን ቀሰቀሰ

የሳዑዲ አረቢያ ልዑል አልጋ ወራሽ መሐመድ ቢን ሳልማን በፈረንሳይ እያደረጉት ያለው ጉብኝት ቁጣን ቀሰቀሰ። የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ልዑሉ በተለይ ከጋዜጠኛ ጀማል ኻሾግጂ ግድያ ጋር ተያይዞ የጠለሸው ስማቸውን ለማደስ ያደረጉት ጉብኝት ነው በሚል ትችት እየሰነዘሩ ነው።

የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ሐሙስ ምሽት ለሞሐመድ ቢን ሰልማን የእራት ግብዣ አድርገውላቸዋል። የሳዑዲው ልዑል ወደ ፓሪስ የተጓዙት የነዳጅ ዋጋ እየናረ ባለበት እና የኢራን የኒውክሌር መርሃ ግብር ስጋቶች በጠነከሩበት ወቅት ነው። ልዑሉ ቢን ሳልማን በቱርክ በሚገኘው የሳዑዲ ቆንስላ ውስጥ ጋዜጠኛው እንዲገደል ትዕዛዝ አልሰጠሁም ሲሉ ይከራከራሉ።

የኻሾግጂ እጮኛ በመሐመድ ቢን ሳልማን ጉብኝት በጣም መበሳጨቷን ገልጻለች። ፕሬዚዳንት ማክሮን የእጮኛዋን "ገዳይ በሙሉ ክብር" ተቀብለዋል ስትልም ከሳለች። መሐመድ ቢን ሳልማን ከማክሮን ጋር ከመገናኘታቸው አንድ ቀን ቀደም ብለው ፓሪስ ከገቡ በኋላ በቅንጡ ማረፊያ ውስጥ ቆይተዋል።

ሁለቱ መሪዎች ሐሙስ ዕለት ቤተ-መንግሥት ከመገናኘታቸው ከሰዓታት በፊት ሶስት ቡድኖች ሞሐመድ ቢን ሳልማን ኻሾግጂን በማሰቃየት እና በመግደል ወንጀል ተባባሪ ናቸው ሲሉ ክስ መስርተውባቸዋል። ከከሳሾቹ መካከል አንዱ የሆነው ዴሞክራሲ ለዓረብ ዓለም የተሰኘው ተቋም መሐመድ



ቢን ሳልማን የአገር መሪ ስላልሆኑ ያለመከሰስ መብት የላቸውም ብሏል።

የሂዩማንራይትስ ዎች ባልደረባ ቤኔዲክ ጄኔሮድ በበኩላቸው ማክሮን በመብቶች ላይ ያላቸውን ጠንካራ እና ተጨባጭ ቁርጠኝነት ሳያረጋግጡ የልዑሉን ወንጀል ለማረሳሳት ሞክረዋል ብለዋል። ከስብሰባው በፊትም የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ረዳት የሰብዓዊ መብት አያያዝ ጉዳይ "በአጠቃላይ" በንግግራቸው ወቅት እንደሚነሳ ጠቅሰዋል። ነገር ግን አውሮፓ ያጋጠማትን ችግር ለመፍታት ሁሉንም የፈረንሳይ አጋር አገራትን ማነጋገር አስፈላጊ ነውም ብለዋል።

ሁለቱ ሰዎች ከኻሾግጂ ግድያ በኋላ በታሕሳስ ወር በሳዑዲ አረቢያ ጅዳ ከተማ ጨምሮ በተለያየ ጊዜ ተገናኝተው መነጋገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# የሕይወት ክረምት

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

ክረምት መጥቶ ክረምት በሄደ ቁጥር የምንሰማው ተመሳሳይ ነገር፤ "የዘንድሮ ክረምት ይለያል" የሚል ነው። እኔም የዘንድሮ ክረምት ይለያል ብዬ ለመጀመር አሰብኩ። በእርግጥ የዘንድሮው ክረምት ይለያል። የአየር ንብረት ለውጡን በትክክል እየተመለከትን ያለነው በክረምት እና በበጋ መፈራረቅ ውስጥ እየሆነ ነው። የአዲስ አበባ መንገዶች በደቂቃ ውስጥ በዘነበ ዝናብ ከአስፓልትነት ወደ ባህርነት ሲቀየሩ እናያለን። የብርዱ አይነት ተለውጦ ጥዝጣዜው ከአካላችን ጋር ተጣብቆ መላቀቅ የሚከብደውም ይመስላል። ይህን ስናይ የዘንድሮ ክረምት የተለየ ነው ብንል የተሳሳተ አንሆንም።

የዛሬው መንደርደሪያ ታሪካችን በመንገድ ዳር በቆሎ በመሸጥ ልጆቿን የምታሳድግ ብርቱ እናት ጋር ይወስደናል። በጎልማሳነት እድሜ ክልል የምትገኝ የጉሊት ሰራተኛ ነች። በክረምትም በበጋም ያዋጣኛል የምትለውን ይዛ ወደ ጉሊት ትወጣለች። ሰሞኑን በቆሎ ይዛ እየወጣች ነው። በቆሎና የክረምት ወቅት ያላቸው ቁርኝት ለአንባቢው መግለጽ ለቀባሪው ማርዳት ነው። እናም አንድ ቀን በተለመደው የበቆሎ ስራዋ ላይ ነች። መንገድ ዳር ከሰል አቀጣጥላ ከሰሉ ላይ ያስቀመጠቻቸው በቆሎዎችን እያገላበጠች ለደንበኞቿ እንደሚሆን እያደረገች ትገኛለች።

የደረሰውን በቆሎ እየሸጠች ሌላውን በቆሎ እንዲሁ እየጠበሰች ትቀጥላለች። በዚህ ተግባሯ ላይ ሳለች ልጇ እየሮጠች ከቤት መጣች። የልጇም መልእክት እቤት እንግዳ እንደመጣባት የሚገልጽ ነበር። ማንነቱን መግለጥ ያልፈለገ እንግዳ መሆኑንም ተረዳች። ስራዋንም አጠገቧ ላለች የጉሊት ሥራ ባልደረባዋ አደራ ሰጥታ ወደ ቤቷ ሄደች።

እቤት የጠበቃት እንግዳ ባለችበት ደርቃ እንድትቆም አደረጋት። ለእርሷ ወደ ጎዳና ንግድ መውጣት ምክንያት የሆነው ከዓመታት በፊት የት እንደገባ የማታውቀው ባለቤቷ ነበር። በብዙ መንገድ ተንከራታ ብትፈልገውም ልታገኘው ያልቻለችው ግለሰብ ዛሬ ከፊት ለፊቷ ቆሟል። ሕጻናት የነበሩት ልጆቹም አድገው ለእናታቸው መላላክም ላይ ደርሰዋል። እንግዳውን ሰው ግን አላወቁትም።

ሁለቱም የተደበላለቀ ስሜት ውስጥ ሆነው ይተያያሉ፤ ልጆች ግን የሚሆነው አልገባቸውም። ከሁለቱም ዓይን እምባ ይፈሳል። አንዱ የሌላኛውን እምባ ማበስ የሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ግን አልነበረም። ያለ ድምጽ እንዲሁ በእምባ ብቻ እያወሩ ነው፤ ደቂቃዎች ሄዱ። ግለሰቡ ያወጣው የመጀመሪያ ቃል "የህይወት ክረምት የህይወቴን መንገድ አበላሸው" የሚል ነበር። ሚስት አልገባትም፤ ግን ደግሞ ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ገጥሞት እንደሆነ ተረድታለች።

ደቂቃዎቹ ወደ ሰዓታት አደጉ፤ ሰዓታት ወደ ቀናት የሆነውን ሁሉ እየተረከላት ሰነበቱ። ሁሉም ነገር በእውን የሆነ ሳይሆን ፊልም ይመስላል። የተዋጣለት የፊልም ደራሲ የደረሰው፤ የተዋጣለት የፊልም ዳይሬክተር ዳይሬክት ያደረገው፤ የተዋጣለት ተዋንያን የተወኑበት በኦስካር መድረክ ላይ ቢቀርብ ማሸነፉ አይቀሬ የሚመስል ፊልም። የህይወት ክረምት ውስጥ የተገኘ።

እርሷም ያለፉትን ዓመታት እንዴት እንዳለፈች ስትተርክ ተመሳሳይ ነገር ነበር፤ አስደማሚ ምስክርነት። ሰው ከሰው ሲለይ የሚገጥም፤ ሰው ከሰው ጋር አብሮ በመኖርና በመለያየት ውስጥ የሚገጥም የህይወት ከፍታና ዝቅታ። ሁለቱም ያለፉበት የህይወት ክረምት በሚገባ ተረዱ። ከጥንዶቹ ታሪክ ውስጥ የቀደመው ትምህርት በሁለቱም ውስጥ በህይወት በየትኛው ቅጽበት ምን እንደሚሆን የሰው ልጆች የማናውቅ ትልቅ ውስንነት ያለብን መሆናችንን የሚያሳይ ነው።

### የሰው ልጅ ትልቁ ውስንነት

እኛ የሰው ልጆች የበዛ ውስንነት አለብን፤ ከውስንነቶቻችን መካከል ግንባር ቀደሙን የሚይዘው በህይወታችን ውስጥ ቀጥሎ ምን እንደሚገጥመን የማናውቅ መሆኑ ነው። በየሰፈሩ ያሉ የጥንቆላ ቤቶችም ይህን ውስንነት ለመድፈን ሲባል እንደሚሰሩ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ አስተሳሰብ ነው። በአገራችን ከተራ ግለሰብ እስከ ታዋቂ ሰዎች የጥንቆላው ቀጠና ውስጥ ተገኝተው የነገውን እጣፈንታቸውን ዛሬ ላይ አውቀው ለመኖር ሲጥሩ ይስተዋላል። ለንግዳቸው የቱንም ያህል ካፒታል ቢኖራቸው ስለ ነገ ሰግተው ወደ ኢንሹራንስ ከመሄድ ወደ ጥንቆላ ሄደው ግብራቸውን ማውጣት የሚቀናቸውንም ቤት ይቁጠራቸው። የሃይማኖት ድንበር ሳያጥራቸው በየጨለማው፤ በየመንደሩ የሚገኙ ጥቂቶች አይደሉም። "እከሌ እኮ እዚህ ቦታ ነው ያስጠነቆለው" የሚል ወሬ ለእኛ እንግዳም የማይሆነው ለዚህ ነው።

የሰው ልጅ ያለበትን ውስንነት በጥረቱ ለመድፈን ከሚያደርጋቸው ነገሮች መካከል አንዱ ነገሮችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መተንበይ መቻል ነው። የአገራት ኢኮኖሚ በምን ያህል ሁኔታ ሊያድግም ሆነ ሊቀነስ እንደሚችል ይተነበያል። በአየር ንብረት ዙሪያም ሙቀትና ዝናብ ስለመሆኑ ወይንም ከፊል ደመናማ እንደሚሆንም እንዲሁ። ስለዚህ ትንበያው የመሳካት አቅሙ ሳይንስ የደረሰበትን ደረጃም ያሳያል።

በጤናም፤ በሕዝብ ብዛትም፤ በሌሎችም ዘርፎች ሳይንሳዊ የሆነ ትምበያዎች ይሰጣሉ። የዚህ ሁሉ ጥረት ነገን ዛሬ ላይ ሆኖ በማወቅ ለነገ ጉዞ ለመዘጋጀት ነው። ጥረቱ የቀጠለ ቢሆንም አሁንም በመሰረታዊነት የሰው ልጅ ነገን ባለመረዳት ውስንነት ውስጥ የመኖሩን እውነት ግን ሊሽረው አልቻለም። የህይወት ክረምት ከደጃችን ቆሞ በአካል ስናገኘው ያኔ ውስንነታችንን እንረዳለን። ውስንነት ይዞት የሚመጣውን እድልን አሻግረው የተመለከቱ ደግሞ የተለዩት ናቸው።

### የውስንነታችን እድሎች

ውስንነት እድል ሊሆን አይችልም፤ በእርግጥ ግን እድል ሊሆን ይችላል። የተጣረሰ ሙግት። አንድን ነገር በፊትለፊት በሚታየው መንገድ ስናየው በትክክል የሚጠቅመን አለመሆኑን እንረዳ ይሆናል። ነገር ግን በዓለማችን ላይ ለሰው ልጆች የሚጠቅሙ ታላላቅ ግኝቶች የተከሰቱት ውስንነትን ወደ እድል ለመቀየር እምነት አድርገው በሰሩ ሰዎች ነው። እኒያ ሰዎች በውስንነት ወቅት የሚያደርጉት ጥረት ለሌሎች እጅና እግራቸውን አጣጥፈው ለተቀመጡት ሰዎች እንደ መሳቂያ የሚቆጠር ነው። ይሁን እንጂ በእነርሱ ሥራ ወይም ውስንነትን ማለፍና ወደ ተራራው ጫፍ መድረስ ብዙዎች መጠቀም ይጀምራሉ።

ውስንነት ነገሮች ባልታዩበት መንገድ ማየትን ይጠይቃል። ዛሬ ነገሮችን የምናይበት፤ አውጥተን የምናወርድበት መንገድ ከውስንነት ማዶ ያለንን መዳረሻ ያሳየናል። የሰው ልጅ በፍጹም ነገን አለማወቁ የፈጣሪ ፈቃድ ቢሆንም ነገ እንዲህ ቢሆን ብሎ አስቦ ዝግጅት ቢያደርግ እንዲሁ የፈጣሪ ፈቃድ አይሆንም ሊባል አይችልም። የሰው ልጅ በሰፊው ሳይንሳዊ ምርመራ እያደረገ ለነገ ዛሬ ቢዘጋጅ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂም እንደማይሆን እሙን ነው።

አንባቢው ዛሬ በህይወቱ ውስጥ ያሉትን ውስንነቶችን በመዘርዘር እንዴት ነገሮችን ባልታዩበት መንገድ በማየት ወደፊት ለመዘርጋት እንደ እድል እንደሚጠቀምባቸው ማሰብ አለበት። ነገሮች ባልታዩበት መንገድ በማየት ውስጥ ፈተናዎችን ተጋፍጦ ማለፍ አለ። የሰው ልጆች በምድር ላይ የሚያሳልፈው መከራ ሁሉ መጥፊያው ሳይሆን መልሚያውም ጭምር ነው። ካለበት ወደሚቀጥለው የሚሸጋገርበት ድልድይም ነው።

ውስንነት በተጨባጭ ውስን የሚሆነው ለተቀማጭ ብቻ ነው። ‹‹ለተቀማጭ ሰማይ ቅርብ ነው›› እንደሚባለው። ዛሬ በምናልፍበት የህይወት ውጣውረድ ውስጥ ነገሮችን በብልህነት እያዩ ማለፍ የግድ ነው። ያለንበት ዘመን ውስንነታችንን ይበልጥ እያገዘፈ የመጣ ዘመን ይመስላል። ከትላንት ዛሬ የምድር ፈተና ይቀላል ሲባል እየተወሳሰበ፤ ሳይንስ በዘመነ ቁጥር ምድርን ሰላማዊ ሳይሆን በስጋት ውስጥ የምትኖር እያደረጋት ይገኛል። የዓለም አጀንዳው ተጠቃሎ ወደ አንድ ግለሰብ ህይወት ውስጥ ሲመጣ ያለውን ተጽእኖ ለመቀነስና ወደፊት በጽናት ለመጓዝ ከውስንነት ባሻገር መሄድን መልመድ ያስፈልጋል። የህይወት ክረምት ወቅቶች ባህሪያት ውስጥ ስናልፍ ይህን እንረዳለን። እኝኝ የሚለው ዝናብን መነሻ አድርገን እንቀጥል።

### እኝኝ የሚለው ዝናብ

ማይክል ጆርዳን ከሚጠቀስለት አባባሎች መካከል አንዱ እንዲህ ይላል፤ "I've failed over and over and over again in my life — and that is why I succeed." በአጭሩ ማይክል ጆርዳን ስኬታማ የሆነው ደጋግሞ በመውደቁ ነው።

የክረምት አንዱ ማሳያ የማያቋርጠው ዝናብ ነው፤ እኝኝ የሚለው። በተጨባጭ እኝኝ የሚለው ዝናብ የክረምት ወጉን እየፈጸመ ነው፤ በህይወት ክረምት ውስጥ ግን አሉታዊነት ማሳያ ሆኖ እንረዳዋለን። በህይወታችን ውስጥ አንዱን መከራ አለፍን ስንል ሌላ መከራ የሚከታተልበት ወቅት ውስጥ እናልፋለን። ተዘጋ ያልነው ሽንቁር አቅጣጫውን ቀይሮ ሊመጣ ይችላል። ሁሌም ባይሆን በህይወታችን እንዲህ ያለወቅት ያጋጥመን ይሆናል።

በመነሻ ታሪካችን ድንገት የትዳር አጋሯን ያጣች ሴት ምናልባትም የጉልት ንግድን በህልሟም በውኗም አስባው የማታውቅ ይሆናል። ከየአቅጣጫው የመጣው ጦር ግን ወደ ጉሊት ገፍቷታል። ይህ ውስንነትን ማሸነፊያ ማሳያ እንጂ የመሸነፉ አይደለም። ነገርግን ተስፋ ቆርጣ ሌሎች መንገዶችን ብትሄድ ተሸናፊ ነበረች። ገላዋን ሸጣ ለማደር ከራሷ ጋር ብዙ ተሟግታለች። ነገርግን ልጆቼ የሚያፍሩበትን ታሪክ አላስቀምጥም ብለ በተከበረችበት መንደር የጉሊቱን ስራ ጀመረች። እኝኝ የሚለውን ክረምት በጽናት ማለፍ ትችል ዘንድም በረታች። በብርታት መንገድ ላይም ሳለች ድንገት ይሆናል ያላለችው ሆነ፤ የትዳር አጋሯ ከዓመታት በኋላ ከቤቷ በር ላይ ደረሰ።

መገፋት፣ መገለል፣ አለመታመን፣ ብቸኝነት፣ ተስፋ የሚደረግ መጥፋት፣ ቃልን መከዳት ወዘተ እኝኝ በሚለው ክረምት ይመሰላል። ህይወትን በብልሃት የሚመሩ ግን እኝኝ ከሚለው የህይወት ክረምት ባሻገር በጽናት ተጉዘው ከፊትለፊታቸው ያለን የውስንነታቸው ተቃራኒ ገጽ ማሳያ የሆነው ቀን ላይ ይደርሳሉ፤ ብሩሁ ቀን ላይ። ከጎርፉ በኋላ በጉልህ የሚታየው ቀን።

### ከጎርፉ በኋላ

ዝናቡ ደጋግሞ ዘንቦ፤ ምናልባትም ጎርፍ ሆኖ ጥፋትም አድርሶ፤ የሰፈሩን ቆሻሻ ሆነ መልካሙንም ሁሉ ይዞት ሄዶ በስተመጨረሻ አስጨናቂው የጎርፍ ወቅት አልፎ የብርሃን ቀን ይመጣል። የብርሃን ቀኑ ወደ ውጤት የመድረስ ማሳያ የሆነ ቀን ነው። የብርሃኑ ቀን ዛሬ ላይ ካለንበት የመከራ ጎርፍ አንጻር ስናስተያየው እንደሚመጣ ያልጠበቅነው ቀን ነው። ከፊት ባሉት ቀናት ውስጥ ክረምቱ አልፎ የሚመጣ የብርሃን ቀን ማሳያ። ያንን የብርሃን ቀን ተስፋ አድርጎ ዛሬን በጽናት መቆየት ታላቅነት ነው።

ከጎርፉ በኋላ ያለውን ቀን አሻግሮ ማየት አሁንም በሰውነት ውስንነት ውስጥ ማየት ይከብድ ይሆናል። ነገርግን ወደ ውስጥ ተመልከት፤ በልብህ ውስጥ ድምጽ ይኖራል። ከራስህ ጋር ሁን፤ ለራስሽ ጊዜን ስጪ፤ ነፍስሽን በጥሞና አድምጪያት፤ ከበዛው ግርግር ወጣ ብሎ ውስጥን በማዳመጥ አሻግሮ ከጎርፉ በኋላ ያለውን ቀን መመልከት ያስችላል። በግርግር ውስጥ ህይወታቸውን ለመምራት ለወሰኑ ይህ ቀላል ተግባር አይደለም። በራቸውን ዘግተው ልባቸውን ከፍተው ከፈጣሪያቸው ጋር ከሚገናኙት ጋር ግን ይህ ይሆናል፤ ከጎርፉ በኋላ ያለውን መመልከት።

ህይወታቸውን ላመኑበት ዓላማ ለፖለቲካም ይሁን ለሃይማኖት የሚሰጡ ሰዎች አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ዛሬ ካሉበት ነገር አሻግረው መመልከት የቻሉ ሰው መሆናቸው ነው። በጦር ሜዳ የተሰለፈ አንድ ወታደር ከጦርነቱ ማዶ ሰላምን ይናፍቃል፤ ከጦርነቱ ማዶ አሸንፎ ውጤት እንደሚሆን አምኖ ይፋለማል።



በህይወት ክረምት ውስጥ ጎርፉ ላይ ብቻ ቆሞ መቅረት የለም፤ ከጎርፉ በኋላ ሌላ ታሪክ አለ፤ ህይወት ገጽ ላይ ተጽፎ የሚገኝ ሌላ ታሪክ፤ የታገሱና አሻግረው ማየት የቻሉ ብቻ የሚመለከቱት ታሪክ፤ በአግባቡ የተኳለ ዓይንን የሚፈልግ እይታ።

ጎርፉ ካለፈ በኋላ የሚመጣው የብርሃን ዘመን ላይ ወድቀው የሚገኙ ግን ጥቂት አለመሆናቸውን ማሰብ አንዳንዴ የህይወት ክረምት ምነው በቆየ ያስብላል። የህይወት ክረምት በማይመች ሁኔታ ውስጥ ለህይወት ዘመን የሚመች ምርት የሚዘጋጅበት ነው። ዝናቡ ለአርሶአደሩ ለስራው የሚመች ባይሆንም ለበጋው የሚሆነውን ስንቅ የሚሰንቅበት ከአስቸጋሪው ክረምት ማዶ ብራን የሚያይበት ነው። ድልን መጠበቅ ሳይችሉ በድላቸው ወቅት ወድቀው የሚገኙ ሰዎችን ቀጥሎ ባሉት ቃላት ውስጥ ተመልክተን ስለ ህይወት ክረምት የከፈትነውን ገጽ እናጠናቅ።

### የብርሃን ሰለባዎች

የጨለማው ወቅት ታልፎ፤ የህይወት አደይ አበባም ፍክት ብላ፤ የጓዳ ውስጥ ችግር ተፈቶ፤ የጤና እክልም ተቀርፎ ነገሮች መስመር ውስጥ ናቸው በሚባልበት ጊዜ ምንያህሉ በምስጋና ህይወት ውስጥ ይገባል፤ ምንያህሉስ ከእዚህ ቀደም ያልሞከረውን በመሞከር ስሌት የመጥፊያ መንገዱን አንድ ብሎ ይጀምራል።

በዩኒቨርሲቲ ተማሪነት ወቅት በተማሪዎች መካከል የሚስተዋል አጉል ልማድ ምንጩ የጓደኞች ተጽእኖ፣ የቤተሰብ ከተገቢው በላይ የሚላክ ገንዘብ እና ሌሎች ምክንያቶችም ይቀርባሉ። በገንዘብ ተቸግሮ ያደገ አባት ለልጁ የእርሱን ችግር ለመበቀል በማለት የሚሰጠው የተጋነነ ገንዘብ ልጁን ያልተገባ ህይወት ውስጥ እንዲገባ በር ይከፍትለታል። እንደውም በአንዳንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ልጆች ቤታቸው ካሉት ከባባድ መጠጦች መካከል በቦርሳቸው አድርገው ትምህርትቤት ሄደው የሚገኙበት አጋጣሚ እንዳለም እንሰማለን።

ዛሬ በምንም አቅጣጫ ይሁን ሊናገር የሚችለው ዛሬን ግፋ ካለም ትላንትን እንጂ ነገን ሊናገር አይችልም። ነገ ውስጥ ከጨለማው ወደ ብርሃን መሸጋገር አለ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ከብርሃንም ወደ ጨለማ መመለስ አለ። ከብርሃን ወደ ጨለማ የሚሆነው መመለስ ብርሃንን በአግባቡ ካለመያዝ የሚመጣ ሲሆን ሃዘኑ ድርብርብ ይሆናል።

"ከተራብ ይልቅ ለጠገበ አዝናለሁ" የሚለው አገራዊ ብሂል የሚሰጠን መልእክት ከፍ ያለ ነው። ብሂሉ የሚሰጠንን ትርጉም ይዘን ለአፍታ ቆም ብለን በህይወታችን ውስጥ በምን ደረጃ እየታየ እንደሆነ መመርመሩ አይከፋም። የብርሃን ሰለባ ላለመሆን በመጠንቀቅ፤ ዛሬ ላይ በምንገኝበት ሁኔታ ባለመሰማራት፤ በመጽናት ከፊታችን ያሉት ቀኖች ከውስንንነታችን በላይ የምንራመድባቸው ይሁንልን። የህይወት ክረምት መንገድ አድካሚ ቢሆንም ወደ ውስጣቸው የሚመለከቱ ግን በድል ይወጡታልና።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከአስከፊ የሕይወት ገጽታ ወደ ኦፓል ማእድን ሳኪነት

**ይበል ካሳ**

የኦፓል ማእድን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ ንግድ ተሰማርቶ እየሰራ ነው፤ በዚህ ስራ እስከሚሰማራ ድረስ ግን ብዙ ፈተናዎችን አሳልፏል። ፈተናዎቹን አሸንፎ፣ ተጠምዶባቸው ከነበሩ ሱሶች ከማውጣት አልፎ፣ ራሱን ከፍታ ላይ ማስቀመጥ ችሏል። ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገም ነው። ማእድን ላኪው አቶ በላይ ደምሴ።

እኛም አቶ በላይ ያለፈባቸው የሕይወት ውጣ ውረዶችና በተለይም የበርካታ ወጣቶች ሕይወት በከንቱ ባክኖ እንዲቀር የሚያደርገውን የሱስና የሱሰኝነት እስር ቤት ሰብሮ አሁን ለሚገኝበት ስኬት የበቃበት የሕይወት መንገድ እጅግ አስተማሪ ነውና አቶ በላይን የዛሬ የስኬት አምድ እንግዳችን አድርገነዋል።

ተወልዶ ያደገው ደቡብ ወሎ፤ ደላንታ ወረዳ ወገል ጤና ከተማ ነው። ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ክፍል ያለውን ትምህርቱን በወገልጤና ትምህርት ቤት ተከታትሏል፤ ከስምንተኛ እስከ አስረኛ ክፍል የተማረውም በዚያው በወገልጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው።

የመሰናዶ ትምህርቱን ደሴ በሚገኘው ሆጤ መሰናዶ ትምህርት ቤት እየተከታተለ ባለበት ወቅት አንድ ማስታወቂያ ይመለከታል። አስራ አንደኛ ክፍል እያለ። የፌዴራል ፖሊስ የሥራ ማስታወቂያ ነው። ወጣቱ ከልጅነቱ ጀምሮ ለስፖርት ልዩ ዝንባሌ ያለውና ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችንም አዘውትሮ የሚሠራ ቁመናውም ለእዚህ የሰጠ ነበርና ማስታወቂያውን በዋዛ አልተመለከተውም፤ ለፖሊስነት ተወዳድሮ አለፈናም በ1994 ዓ.ም ፌዴራል ፖሊስን ተቀላቀለ። በስራው አዲስ አበባ ተመድቦ ከመጣ በኋላም እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ ፌዴራል ፖሊስን አገለገለ።

"አዲስ አባባ ውስጥ ፌዴራል ፖሊስ ሆኜ እያገለገልኩ ሳለ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በሕይወቴ ደስተኛ አልነበርኩም» የሚለው አቶ በላይ ፣ ከዚህ ሕይወት ዞር ያለ እየመሰለው ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስና አልኮል መጠጣት ውስጥ ይገባል። ቀስ በቀስም በእነዚህ ሱሶች በእጅጉ እየተጠመደ የመጣበትን መጥፎ አጋጣሚ ያስታውሳል። እንደ ዋዛ የተጀመረው የሱስ አምጭ ነገሮች ልምምድ እየሰፋ መጣ፤ አዕምሮና አካሉ መሸከም ከሚችለው መጠን በላይ የሱስና የሱሰኝነት የመከራ ቀንበር አረፈበት፤ ሱስና ሱሰኝነት ብቻ ሳይሆን እሱ የወለደው መዘዝ እየተወሳሰበና እየገዘፈ መጥቶ ከአቅሙ በላይ ሆነበት፤ ሕይወቱ እጅጉን ተመሰቃቀለ።

በዚህ የተነሳም የፖሊስነት ሥራውን በአግባቡ መሥራት የማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ። የተከበረውንና የሚወደውን የፖሊስነት ሙያውን ትቶ ወደ ትውልድ አገሩ ወገል ጤና ደላንታ ተመለሰ። በዚያም ከአስጨናቂው የሱስና የሱሰኝነት ሕይወት ጋር እየታገለ በትንሿ የወገል ጤና ከተማ በተላላኪነትና በደላላነት ኑሮን እንደ አዲስ "ሀ" ብሎ ጀመረ።

የሱስሰኝነት ልክፍቱ ግን የፖሊስነት ሥራውን በቀላሉ እንደተወው በቀላሉ ሊተወው የሚችለው አልሆንለት አለው። ሥራውን ለቆ ወደ ትውልድ ሀገሩ መመለሱ እንኳንስ ለችግሩ መፍትሔ ሊሆነው አንድ ጊዜ አግኝቶ ሁለተኛ ለመድገም ቀናትን መጠበቅ ግድ እንዲሆንበት አደረገው፤ የዕለት ጉርስን አግኝቶ ማደር ጀብዱ በሆነበት የደላላነት ሥራ፣ ራስን ከመምራት አስቸጋሪ የኑሮ ግብግብ ጋር ተደማምሮ ከመሻሻል ይልቅ የሱሰኝነት ደረጃው ይበልጡኑ ተባብሶ በእርሱ አገላለጽ "ከሰውነት ተራ እስኪወጣ" አደረሰው።

ችግሩ ከሱሰኝነትም አልፎ እጅግ አስከፊ የሚባል የጤና ችግርን አስከተለ፤ እያደር ራሱን በሕልውና ስጋት ውስጥ ያገኘው ጀመር። "የነበርኩበትን ሁኔታ በምን ቃል እንደምገልጸው ይከብደኛል። ሱስ ከሰውነት ተራ እስከመውጣት ብቻ አይደለም ለአእምሮ ህመም ጭምር እንድዳረግ ጭምር አርጎኝ ነበር፤ በተደጋጋሚ ራሴን ለማጥፋት ሞክሬ እግዚአብሔር አትርፎኛል" በማለት ያን የመከራ ጊዜውን ያስታውሰዋል።

ፌዴራል ፖሊስ ሆኖ ማገልገል ከጀመረበት 1994 ዓ.ም አንስቶ ሥራውን እስከለቀቀበት 1999 ዓ.ም ፣ ከዚያም በወገል ጤና ከተማ እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ለሰባት ዓመታት በድለላ ሥራ እስከቆየበት በጥቅሉ ከአሥራ ሁለት ዓመታት በላይ በከባድ ተስፋ አስቆራጭ ሕይወት ቆይቷል፤ አንድ ቀን ግን "የሞት ያህል ቢከብደኝምም ከዚህ አስከፊ የሱሰኝነት ሕይወት፣ ራሴ ከገባሁበት አስፈሪ ማጥ እንደምንም አሸንፌ ለመውጣትና ለተሻለ ሕይወት መውለድ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ" ይላል። "ከዚያም በውሳኔዬ ፀናሁ፤ እግዚአብሔር ተጨምሮበት ከእብደትና ከሞት ደረጃ አድርሶኝ ከነበረው ከዚህ አስከፊ የሱሰኝነት ሕይወት ወጣሁ" ሲል አቶ በላይ ይገልጻል።



**አቶ በላይ ደምሴ**

ሕይወቱን የሚለውጥበትን የተሻለ ሥራ መሥራት እንዳለበት ከራሱ ጋር ይማከር ጀመር። ለዚህም ከሁሉም የተሻለ ሆኖ ያገኘው ደግሞ በደላላነት ዘመኑ የተዋወቀውን የኦፓል ንግድ ሆነ።

የትውልድ አካባቢው የኦፓል ማእድን በስፋት የሚገኝበትና የሚመረት ነው። በርካታ የአካባቢው ነዋሪዎችም በዚህ የጌጣጌጥ ማእድን ማውጣት ስራ ተሰማርተው ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ማእድኑን በቀጥታ ለነጋዴዎች የሚሸጡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ እሴት ጨምረው ነው የሚሸጡት። ሌሎች ደግሞ ኦፓሉን ከአምራቾች እየሰበሰቡ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ያቀርባሉ። አቶ በላይ ይህን ግብይት ነው የተቀላቀለው።

የኦፓል ንግድን እያወቀው በመጣ ቁጥር ከፍተኛ ፍቅር አድሮበታልና፣ ‹‹በሠራው እለወጥበታለሁ›› ሲል የኦፓል ማዕድን ንግድ ላይ አተኮረ። አቶ በላይ ከነበረበት የሱሰኝነት ሕይወት ብቻ አይደለም በጥረቱ የወጣው፤ አሁን ከፍተኛ ማማ ላይ ላስቀመጠው የኦፓል ማእድን ላኪነት ልምድና እውቀት እንዲጨብጥ ያደረገውንም የድለላ ስራውን በ2008 ዓ.ም የደላላነቱን ሥራ በመተው የኦፓል ማዕድን ንግድ ሥራውን በራሱ መሥራት ጀመረ።

ኦፓል የሚወጣበት አካባቢ የትውልድ አካባቢው ነው፤ በዚያ ላይ በደላላነት በሠራባቸው ዓመታት ስለሥራው ሁኔታ በቂ ዕውቀትና ልምድ አካብቷል፤ ከብዙ ሰዎች ጋርም ተዋውቋል። እናም ‹‹ስራው ያን ያህል አልከበደኝም›› ብሎ በስራው ገፋበት። የመጀመሪያ ስራውም ተስፋውን አለመለመለት። ‹‹በመጀመሪያ ሙከራዬም በሦስት ሺ ብር የገዛሁትን ኦፓል፣ ሃያ ሺ ብር ሸጥኩት" በማለት የኦፓል ማዕድን ንግድ ሥራ አጀማመሩን ያስታውሳል።

ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2012 ዓ.ም ድረስ ከደላንታ አዲስ አባባ እየተመላለሰ ለአራት ዓመታት ያህል በአገር ውስጥ በኦፓል ማዕድን ንግድ ሥራ ተሰማርቶ ሰራ፤ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ሥራውን የበለጠ በማስፋፋትና አዲስ አበባ ላይ "በላይ ደምሴ ኤክስፖርተር" በሚል ድርጅት ከፍቶ ኦፓል ወደውጭ መላኩን ተያያዘው።

የማዕድን ሥራ ከፍተኛ ዕውቀት የሚጠይቅ መሆኑን በላይ ይናገራል። "ደላላ ሆኜ በማሻሽጥበት ወቅት ከማገኛት አነስተኛ ሳንቲም በላይ ሥራው እንዴት እንደሚሠራ ለማወቅ ነበር ከፍተኛ ጥረት የማደርገው። » የሚለው አቶ በላይ፣ የማዕድን ሥራ ዝም ተብሎ የሚገባበት ሥራ አይደለም፤ ዕውቀት ይጠይቃል ሲል ይገልጻል። ያለዕውቀት ከሆነ የሚገባበት በከፍተኛ ደረጃ ሊያከስር ይችላል›› ሲል ስራው ምን ያህል እውቀትና ልምድ እንደሚፈልግም ይጠቁማል።

በዕውቀት የሚሠራ ከሆነ ደግሞ ማዕድን ለሚሠራው ሰው ብቻ ሳይሆን ለሀገር ዕድገትም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንደሚችል አቶ በላይ ይገልጻል። እሱ ከደላላነት ጀምሮ ሥራውን ከተዋወቀበት ጊዜ አንስቶ ሥራውን በደንብ ለማወቅና በአግባቡ ለመሥራት ጥረት አደርጓል፤ ጥረቱ ከበርካታ የዘርፉ ባለሙያዎች ጋር አስተዋውቆታል፤ በዚህም ጠቃሚ ዕውቀትና ልምድ መቅሰም ችሏል።

በዚህም ከሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በተጨማሪ ከሀገር ውጭ በተለይም ከህንዳውያን የማዕድን ባለሙያዎች ጋር በመተዋወቅና አብሮ በመሥራት ጭምር ዕውቀቱንና ልምዱን ይበልጥ ማዳበር እንደቻለም ይናገራል፤ እነዚህ ሁሉ በሥራው የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችለውታል።

"ሕንዳውያንን የመረጥኩበት ምክንያት እነርሱ ለማዕድን ያላቸው ፍቅር የተለየ በመሆኑ ነው፤ ለማዕድን ትልቅ ክብርና ፍቅር አላቸው። » የሚለው አቶ በላይ፣ ከህንዳውያኑ ጋር መስራቱ በብዙ መልኩ እንደጠቀመው ነው የሚናገረው። ‹‹ከእነርሱ ባገኘሁት ዕውቀት ጥሬ ማዕድኑን በመላክ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀምና ማእድናቱን በማስጌጥ እሴት ጨምሬባቸው የምሸጥበት ዕድል ተፈጥሮልኛል" ሲል ያብራራል።

ሥራውን በልምድ ከመሥራት አውጥቶ በዘመናዊ መንገድ ለማከናወንና ወደተሻለ የዕድገት ደረጃ መውሰድን በተመለከተም ምን ሃሳብ እንዳለው ላቀርብንለት ጥያቄ አቶ በላይ በሰጠው ምላሽ፤ የማዕድን ሥራ ከፍተኛ እውቀትን የሚጠይቅ በመሆኑ በቀጣይ በዘርፉ የሚሰማሩት ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ ቢሆን የሚመረጥ መሆኑን መክሯል።

ልምድም ቀለል ተደርጎ መታየት እንደሌለበት ነው የገለጸው። ‹‹እስካሁን በልምድ እየሰራን የምንገኘውም ከዘርፉ ባለሙያዎች ጋር በመገናኘት ዘመናዊ ዕውቀት መቅሰምና ራሳችንን የበለጠ ማሳደግ ይኖርብናል" ይላል።

ከሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በተጨማሪ ከሀገር ውጭ በተለይም አብረውት ከሚሰሩት ህንዳውያን የማዕድን ባለሙያዎች ዕውቀቱንና ልምዱን ይበልጥ ማዳበር እንደቻለና፣ ከህንዶቹ ያገኘውን እውቀት፣ ቴክኖሎጂና ልምድ ለሀገር ውስጥ ሠራተኞቹና የሥራው ባልደረቦቹ ሽግግር ለማድረግ መሞከሩንም ይናገራል። በዚህም በሥራው የበለጠ ተጠቃሚ ከመሆኑ በተጨማሪ ለሀገሩም ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝበት ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱንም ይገልጻል።

ቀደም ሲል በማዕድን ዘርፉ በርካታ ችግሮች እንደነበሩ አቶ በላይ ያስታውሳል። እሱም በሥራው ወቅት ከፍተኛ ችግር ያጋጥመው ነበር። ፈቃድ ለማውጣትና በህጋዊ መንገድ በዘርፉ ተሰማርቶ ለመሥራት በከፍተኛ ውጣ ውረድና አሰልቺ የአሠራር ሂደት ውስጥ ማለፍ የግድ ነበር። ሰዎች ወደ ህገ ወጥነት እንዲሄዱና ኮንትሮባንድ እንዲስፋፋ የሚያደርግ አሠራርም እንደነበረም ያስታውሳል። "ይሁን እንጂ ዞሮ ዞሮ ህገ ወጥነት መጨረሻው ጥፋት በመሆኑ እኔ በበኩሌ ችግሩን ሁሉ ችዬ ህጋዊውን መንገድ ተከትዬ በመስራቴ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ አልሆንኩም" ይላል።

በአሁኑ ወቅት ግን መንግሥት በዘርፉ ከፍተኛ ማሻሻያዎችን ማድረጉን ጠቅሶ፣ በዚህም አብዛኞቹ ችግሮች እየተቀረፉ መምጣቸውን ይገልጻል። በማሻሻያዎቹ ምክንያት ማዕድናትን ለመላክ ከፍተኛ ጊዜና ወጪን የሚጠይቁ ውጣ ወረዶች እንዲያጥሩና እንዲቃለሉ ተደርገዋል።

ማሻሻያዎቹን ተከትሎ ከዚህ በፊት በኮንትሮባንድ በኬንያና በሱዳን በኩል በከፍተኛ ደረጃ ይወጡ የነበሩ ማዕድኖች በአሁኑ ወቅት በቀጥታ በጉምሩክና በኢትዮጵያ አየር መንገድ አማካኝነት ወደውጭ እየተላኩ ናቸው። ይህም ለላኪዎቹም ለሀገሪቱም ከፍተኛ ጥቅም አለው፤ በሥራው ላይ ትልቅ ለውጥ እንዲመጣ አስችሏል ይላል። ወደፊት በዘርፉ መሰማራት ለሚፈልጉትም በጣም አበረታች ይሆንላቸዋል። ስለሆነም የማዕድን ሚኒስቴርም ሊመሰገን ይገባዋል" ሲል ያስረዳል።

በላይ በአሁኑ ወቅት የተለያየ ዓይነት የኦፓል ማዕድን ምርቶችን ወደ ህንድ፣ አሜሪካ፣ ጀርመንና ፈረንሳይ እየላከ ይገኛል። ለማዕድን ሥራው የሚያግዙት አሥር የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማዕድን ባለሙያዎችን ቀጥሮ ያሰራል። ስምንት የሀገር ውስጥ ሠራተኞችም አሉት። በአዲስ አበባ የራሱ መኖሪያ ቤትና መንቀሳቀሻ ዘመናዊ መኪና አለው።

አጠቃላይ የሀብት መጠኑንም አስር ሚሊዮን ብር አድርሷል። አሁን ላይ ለበርካታ ዓመታት ሕይወቱን አመሰቃቅሎና ከሰውነት ተራ ከመውጣት አልፎ እስከ ተስፋ መቁረጥ አድርሶት የነበረውን እጅግ አስቸጋሪ የሱሰኝነት ሕይወት በሚደንቅ ጥረትና በከፍተኛ ቆራጥነት አሸንፎ፣ ከእጅ ወደአፍ ከማይዘለው የደላላነት ሥራ ተነስቶ ከራሱ አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ ሥራ ባለቤት መሆን ችሏል።

አቶ በላይ ሌላም ራእይ አለው። "ከራሴ፣ ከቤተሰቦቼና ከጥቂት ሰዎች አልፌ ሥራዬን የበለጠ በማስፋፋት በዘርፉ ሀገሬንም ይበልጥ የመጥቀም ፍላጎት አለኝ" ይላል፤ ከኦፓል በተጨማሪ በሌሎችም ማዕድናት ላይ ተሰማርቶ ራሱም ጠቅሞ ሀገሩንም የመጥቀም ራዕይ እንዳለው ይናገራል። እኛም እንግዳችን ራዕዩ እንዲሳካለት መልካሙን እንመኝለታለን። አበቃን።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የመንገድ ዘርፍ ችግሮችን እንደሚፈታ የታመነበት አዲሱ የመንገድ ፖሊሲ



የመድረኩ ታዳሚዎች የመንገድ ዘርፉ የሚመራበትን ግልጽ አቅጣጫና ቀጣይ ግብና ተልዕኮውን በግልጽ ያመላከተ ሲሉ ፖሊሲውን ገልጸውታል፤

**መላኩ ኤሮሴ**

መንገድ በኢትዮጵያ ዋነኛው የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ሲሆን ከሰው እና ከእቃ እንቅስቃሴ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነውን የሚሸፍን በመሆኑም በአገሪቱ ዘላቂ ልማት ላይ ወሳኝ ተጽዕኖ ያለው ነው። በዚህም መነሻ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ለመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ከፍተኛ በጀት እየተመደበ መጠነ ሰፊ ስራ ተሰርቷል። ይህን ተከትሎም በመንገድ አውታር ልማት የታየ ተጨባጭ ለውጥ ቢኖርም የዘርፉ ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና እና ዘላቂነት ከአገልግሎት እና ከአፈፃጸም ደረጃ አንጻር አሁንም ፈርጀ ብዙ ችግሮች እና ክፍተቶች እንዳሉበት ይገለጻል። የመንገድ ዘርፍ የሕግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ደግሞ ዘርፉን ከጎዱት ችግሮች አንዱ ነው።

በተለይም በመንገድ ግንባታ ላይ የፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት ሚና በግልጽ አለመቀመጡ አንዱ ችግር ነው። በዚህም ምክንያት ወዲህና ወዲያ የሚሳሳቡ ብዙ ጉዳዮች አሉ። ከፍትሃዊነት እና ከጥራት አኳያ የሚነሱ ጉዳዮች አሉ። በተለይ ከወሰን ማስከበር እና ከካሳ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ችግር የዘርፉን ልማት እየጎዳው መሆኑ እየተጠቆመ ይገኛል።

በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ያስችላል የተባለ የመንገድ ፖሊሲ ባለፉት ሁለት ዓመታት ሲዘጋጅ ቆይቷል። ፖሊሲው ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተወያዩበት ሲሆን፣ በቅርቡም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተሳተፉበት ተጨማሪ ግብዓት የሚሰባሰብበት የመጨረሻው የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በመድረኩ ላይ ረቂቅ ፖሊሲውን ያቀረቡት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ የትምጌታ አስራት እንደተናገሩት፤ በተለይም ለሕብረተሰቡ የመንገድ ፍላጎት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ ከመስጠት ጋር ተያይዞ የሚታዩ ጉድለቶች፤ የመንገድ ፕሮጀክቶች አመራረጥን እና ፍትሃዊ የመንገድ ስርጭትን በተመለከተ የሚነሱ በርካታ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች፣ በፌዴራል፣ በክልልና በተለያዩ ደረጃዎች የሚያዙ፣ የሚታቀዱና የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች መናበብ እና ቅንጅት ውስን መሆን፤ ባለፉት ዓመታት በዘርፉ በተደረገው ከፍተኛ ርብርብ እና በወጣው ከፍተኛ ወጪ የተፈጠረውን የመንገድ ሀብት በሚጠበቀው ልክ በአግባቡ መንከባከብ አለመቻል፤ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት የሚያጋጥመው መዘግየትና የፕሮጀክት ወጪ ጭማሪ እንዲሁም በዘርፉ የሚሳተፉ ብቃት ያላቸውን አገር በቀል የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች በሚፈለገው ደረጃ ማፍራት አለመቻል በዘርፉ መሠራት ያለባቸውን ቀጣይ የማሻሻያ ስራዎች አስፈላጊነት የሚያመላክቱ እውነታዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የግንባታ ዋጋ፣ የወሰን ማስከበር ችግር እና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት አካቶ ፕሮጀክት ተግባራዊ ማድረግ እየተወሳሰበ መምጣቱ ሌሎች ከሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ጋር ተደምረው ዘርፉ ሁለንተናዊ ማሻሻያ እና ግልጽ የፖሊሲ አቅጣጫ እንደሚፈልግ ማሳያ ናቸው።

በተጨማሪም የመንገድ ዘርፍ ፖሊሲ አለመኖር የመንገድ ዘርፍ ኤጀንሲዎችን ተግባር እና ኃላፊነት እንዲሁም የሚመለከታቸውን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ተቆጣጣሪ አካላት (በዋነኝነት የፖሊሲ፣ የሕግ፣ የቁጥጥር፣ የእቅድ ዝግጅት፣ የማኔጅመንት እና የኦፕሬሽን ተግባራት) በግልጽ ከመወሰንና የአስተዳደር መዋቅሩንና ተቋማዊ ማዕቀፉን ለደንበኛና ቅልጥፍና ተኮር ማኔጅመንት ምላሽ ሰጪ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር በቂ ነጻነት ኖሯቸው መስራት እንዲችሉ ከማድረግ እና ለዘርፉ የሚስያስፈልገውን ፋይናንስ በዘላቂነትና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ከማግኘት አኳያ ውሱንነት ያለበት ነው ብለዋል። በአጠቃላይ ዘላቂ የመንገድ ልማት የሚመራበት፣ ምላሽ ሰጪ የአስተዳደር መዋቅር እና ተቋማዊ ማዕቀፍ፣ የፋይናንስ ግኝትና አስተዳደር ሥርዓት፣ አጠቃላይ ዘላቂና አስተማማኝ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንትና ወጥነት ያለው እና የተቀናጀ የእቅድ ዝግጅት የሚመራበት የመንገድ ዘርፍ ፖሊሲ ማዘጋጀት በዘርፉ ለሚካሄደው ሁለንተናዊ ሪፎርም ወሳኝ እርምጃ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

ፖሊሲው በዋነኝነት በአገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታዎች፣ በኢትዮጵያ መንግሥት የልማት አጀንዳዎች፣ በዓለምአቀፍ ስምምነቶች፣ በዘርፉ አቅም ግንባታ፣ ማዘመንና በተቋማዊ ሽግግር ዓላማዎች ላይ ተመስርቶ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ብቃትና ውጤታማነት፣ የማሕበራዊ መስተጋብርን መጎልበት እና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ለማረጋገጥ በሚያስችል ቁመና ላይ እንዲደርስ ማድረግና በዚህ ቁመናው ለሀገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግና የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ታስቦ የተዘጋጀ የዘርፉን ቀጣይ አካሄድ በተመለከተ አቅጣጫ የሚሰጥ ሰነድ መሆኑም ነው የተመላከተው።

ከፖሊሲው መሰረታዊ እሳቤዎች መካከል የቀጣይ የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫን፣ የፀደቀውን የትራንስፖርት ፖሊሲን፣ በረቂቅ ደረጃ ያለውን የኮንስትራክሽን ፖሊሲን እንዲሁም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ፖሊሲዎችና ሕጎችን፣ የዜጎችን መሰረታዊ ፍላጎት ለማርካት በከተማና በተለይም በገጠር አካባቢዎች የበለጠ ተደራሽነት፣ የጉዞ እንቅስቃሴ እና አማካይ የጉዞ ቅርበት እንዲኖር ማድረግን የሚመለከቱትም በመሰረታዊ እሳቤዎቹ ከተካተቱት መካከል እንደሚገኙበት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በአህጉራዊና ዓለምአቀፍ ደረጃ የጉዞ እንቅስቃሴንና የንግድ ትስስርን ለመደገፍ የመሰረተ-ልማት ዝርጋታም ሆነ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የተደረሰባቸው ስምምነቶች፣ መግባባቶች እንዲሁም ግዴታዎችን፤ በአካባቢና በአህጉር ደረጃ ተጓዥንና ንግድን ለመደገፍ መንገድንና ትራንስፖርትን በተመለከተ የተደረሰባቸው ስምምነቶችም ከመሰረታዊ እሳቤዎቹ መካከል ተካተዋል።

ሌሎች በፖሊሲው መሰረታዊ እሳቤዎች ከተካተቱት መካከልም፤ የትራፊክ ፍሰት፣ ደረጃና መሠረታዊ ተደራሽነት ሚዛናዊ እንዲሆን ማድረግ፤ ሚዛናዊ የሀብት አጠቃቀምንና በገጠር የልማት እቅዶች መካከል ያለውን ትስስርን እንዲሁም የረጅም ጊዜ የፋይናንሲንግ እቅድን ግምት ውስጥ በማስገባት የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅድ ማዘጋጀትን፤ የመንገድ መሰረተ ልማትን ተከትለው የሚሰሩና የሚያቋርጡ ሌሎች መሰረተ ልማቶችን (ዩቲሊቲዎችን) በዲዛይን ማካተትን እና በመንገድ ግንባታ ወቅት ስታንዳርዳቸውን በጠበቀ መልኩ ቦታ ማመቻቸትን ይጠቀሳሉ።

የመንገድ ዘርፍ ፖሊሲ ዋና ዓላማዎች፤ በገጠርና በከተማ አካባቢዎች የሚኖረውን ሕዝብ የጉዞ ፍላጎት መሰረት ያደረገ የመንገድ መሰረተ ልማት መኖሩን ማረጋገጥ፤ በተቀናጀና በተደጋገፈ የመንገድ ልማት መሠረት የመንገድ ትራንስፖርት ወጪን መቀነስና የተቀላጠፈ አገልግሎት ተደራሽነትን ማስፋት፤ የሴክተር ተቋማትንና ሌሎች የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶችን ኃላፊነት በግልፅ ማሳየትና የሚደጋገፉበትን አጠቃላይ አቅጣጫ ማመላከት የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

የመንገዶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ባለፉት 25 ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ ተካሂዷል፤ ከዚያ በፊት የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ እጅግ አነስተኛ የነበረ በመሆኑ አሁንም የመንገድ መሰረተ ልማት ልዩ ትኩረት ይሻሉ።

አሁን ወደ አዲስ ምዕራፍ ሲገባ የመንገድ ግንባታው ዘርፍ የነበሩ ችግሮችን መገምገም፣ ዘርፉን ለማሳደግ አስቻይ ነገሮችን ማየት እንዲሁም አሁን የ10 ዓመት እቅድ ሲዘጋጅም ሁሉንም ነገር ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። በአጭር ፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ የሚመለሱትን መለየት ይገባል። ሕጎችን እና አካሄዶችን ጭምር መገምገምም ተገቢ ነው። በረቂቅ አዋጁ ላይ የተካሄዱ ውይይቶች አካሄዶችችን እና እይታዎችን የሚቀይሩ ናቸው።

እስካሁን የአስፋልት መንገዶች በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ነው ሲሰራ እንደቆዩ የጠቀሱት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ ይህ አካሄድ ከዚህ በሁዋላ እንደማያዋጣም ነው የጠቆሙት። መንገድ ቶሎ መገንባት ካለብን፣ የኢትዮጵያውያንን ፍላጎት ቶሎ መመለስ ካለብን በብዙ ተቋማት በተከፋፈለ ድርሻ ነው መንገድ መገንባት ያለበት፤ ህጉም ይህንኑ ነው የሚፈቅደው ሲሉ ያብራራሉ።

ይህን ጉዳይ አብነት ጠቅሰው ሲያብራሩም፣ 246ሺህ ኪሎ ሜትር እንደ ሀገር ይሰራል ይላል። ይህ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ነው። በክልል፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እንዲሁም በሌሎች አካላት ነው። ማን ምን ይሰራል የሚለውን ዘርዝሮ ማስቀመጥ ወሳኝ በመሆኑ በፖሊሲው ላይ መቀመጡን ጠቁመዋል።

እንደ ኢንጂነር ሀብታሙ ማብራሪያ፤ ብዙ መንገድ እና ጥራት ያለው መንገድ ለመስራት ተከፋፍሎ ካልሆነ በጥቂት አካላት ሊሰራ አይችልም ከሚል መነሻ ነው። ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው ብዙ መንገድ መገንባት የምንችለው ከሚል ነው። ለዚህ የፖሊሲ አቅጣጫ እና የሕግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል። ለመንገድ ልማት ገንዘብ ብቻ አይደለም የሚያስፈልገው፤ አካሄድ ያስፈልጋል።

የዘርፉን እድገት ወደ ላቀ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚያስችል ዘርፈ ብዙ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሀገራዊ የመንገድ መሰረተ ልማት ጥያቄዎች የሚስተናገዱበትን አግባብ ፣ የተፈጠረውን ሀብት በአግባቡ የመጠበቅ ፣ የአገር ውስጥ የስራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች አቅም በሚፈለገው መልኩ ከማሳደግ አኳያ ሰነዱ የጎላ ሚና እንደሚያበረክት ተናግረዋል። ክልሎች በመንገድ ዘርፍ ልማቱ ላይ ያላቸውን ሚና እና ሃላፊነት ማሳደግ ላይም የላቀ አበርክቶ እንዳለው ገልጸዋል። የወሰን ማስከበር ፣ የግብዓት ችግሮች እና ሌሎችንም የዘርፉን ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ማነቆዎች ለመፍታት ፖሊሲው በላቀ ደረጃ ያግዛል ብለዋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ እንደተናገሩት፤ ፖሊሲው ከመንገድ ዘርፍ ጋር ተያይዞ ቀጣይ አገራዊ ግብን ታሳቢ አድርጎ የሚነሱ ችግሮችን የሚፈታ ነው። በዘርፉ ያሉ ውስብስብ ችግሮችን መፍታት በቀጣይ የሚኖረውን እድገት ታሳቢ አድርጎ የባለድርሻ አካላትን ሚና እና ሃላፊነትን በግልጽ አስቀምጧል። ተቆጣጣሪ ተቋማት ከዚህ ዘርፍ የሚወስዱት ድርሻ በተመሳሳይ ይታወቃል። የክልልና የፌዴራል ተቋማት ኃላፊነትም እንዲሁ በግልጽ ባለመቀመጡ የሚና መደበላለቅ መኖር፤ በዘርፉ ያሉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ግልጽ በሆነ መልኩ የስራ ድርሻቸውንና የኃላፊነት ደረጃቸውን እንዲሁም የሚመሩበትን አቅጣጫ እንዳያውቁ ከማድረጉ ባሻገር በዘርፉ የሚያጋጥሙ ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታት እና ልማቱ በትክክለኛው አቅጣጫ ላይ ስለመሆኑ የሚመዘንበት ግልጽ የፖሊሲ አቅጣጫ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ፕሮግራሞች ተተግብረው ከተጠናቀቁ በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎች እንዲነሱ ምክንያት ሲሆን ታይቷል። ስለዚህ መሰል ችግሮች እንዲፈቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ግልጽ አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ እና አመራር የሚሰጥ አንድ ወጥ የፖሊሲ ሰነድ አስፈላጊ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፤ የመንገድ ዘርፍን በግልጽ አቅጣጫ በመምራት ከዘላቂነት፣ ከአስተዳደር መዋቅር፣ ከፕሮጀክት አመራር፣ ከተቋማዊ ማዕቀፍ፣ ከኢኮኖሚያዊ እና የፋይናንስ ግኝትና አስተዳደር እንዲሁም ከማህበራዊ ገጽታዎች፣ ከአየር ንብረት ለውጥ፣ ከምርምር እና ልማት፣ ከአጠቃላይ ተቋማዊ እና የዘርፍ አቅም ግንባታ፣ ከብቃት እና ከተጠያቂነት ጋር የተያያዙ የረጅም ጊዜ ቁልፍ ችግሮችን ለመቅረፍ ፤ የኢትዮጵያ መንግሥትን የልማት አጀንዳዎች ለመደገፍ እና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የፖሊሲ ሰነዱ ተዘጋጅቷል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በተለይም በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡት የዜጎች መብት፣ የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊ እና የባህል መብቶች፣ የልማት መብት፣ የአካባቢ ደህንነት መብት፣ እና የመንግሥት አወቃቀር እና የፌዴራል መንግሥት ድርሻ የዚህ የመንገድ ፖሊሲ መሠረታዊ መነሻዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ሰነዱ የኢትዮጵያ መንግሥት የኢኮኖሚ እድገትን በማፋጠንና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ለማሳካት ያለውን ራዕይ መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

በሂልተን ሆቴል በተካሄደው በመንገድ ፖሊሲ እና የመንገድ አዋጅ ረቂቅ ሰነዶች ላይ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ፣ ከሁለቱም ምክር ቤቶች ፣ ከክልል ባለድርሻ አካላት ፣ ከተለያዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ፣ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ተቋማት የተውጣጡ ተሳታፊዎች ታድመዋል። ታዳሚዎቹ ዘርፉ የሚመራበትን ግልጽ አቅጣጫና ቀጣይ ግብና ተልዕኮን በግልጽ ያመላከተ ሀገራዊ ሰነድ መዘጋጀቱን በመጥቀስ አድንቀዋል። በረቂቅ ፖሊሲውና በሕግ ሰነዱ ላይ ቢካተቱ ያሏቸውን የማዳበሪያ ምክረ ሃሳቦችንም አክለዋል።

በውይይት መድረኩ ላይ የተሳተፉት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ዳባ በበኩላቸው ለመንገድ ግንባታ አንዱ ማነቆ የሆነው የወሰን ማስከበር ችግር እና የካሳ ጉዳይ ነው። አዲሱ ፖሊሲ የወሰን ማስከበር እና የካሳ ጉዳዮችን ክልሎች በራሳቸው እንዲያከናውኑት የሚያደርግ ነው። ይህ ትልቅ እርምጃ ነው ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በእውነተኛ ወንድማማችነት ላይ የተመሰረተው የኢትዮ-ሩሲያ ግንኙነት ተጠናክሮ ይቀጥላል!

ከአንድ ምእተ አመት በላይ ያስቆጠረው የኢትዮጵያና የሩሲያ ህዝቦች ግንኙነት በየወቅቱ እየታደሰ አሁን ላይ በአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ይገኝል። ግንኙነቱ ከኢትዮጵያም አልፎ አፍሪካዊ መልክ እየተላበሰ ይገኛል። ይህንንም ተከትሎ የአገሪቱ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ አገራት የሚያደርጉት ጉብኝት ከፍ ያለ ትኩረት የሚቸረው ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ አስቸጋሪ በሆነ የውጪ ጫና ውስጥ በነበረችባቸው ያለፉት አራት ዓመታት የሩሲያ ሕዝብና መንግስት ለኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ያለውን አጋርነት በአደባባይ በተጨባጭ አሳይቷል። በእነዚህ ጊዜያት በአገሪቱ ላይ የተሸረቡ ዓለም አቀፍ ሴራዎች አቅም እንዳያገኙም ተደርገዋል።

በተለይም በለውጡ ኃይል ላይ ጫናዎችን በመፍጠር ታሪካዊ ጠላቶቻችንም ሆኑ የለውጡ አካሄድ ያልተመቻቸው ኃይሎች የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን በመጠቀም በአገሪቱ ላይ ጫናዎችን ለማሳደር ያደረጉትን የተደጋገሙ ጥረቶች እንዳይሳኩ የሩሲያ መንግስት ያሳየው አጋርነት በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ በደማቅ ቀለም የተጻፈ ነው።

ቀደም ባለውም ዘመን ቢሆን ሩሲያውያን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሚገኙበት ወቅት ፈጥነው በመድረስ አጋርነታቸውን ያሳዩ የክፉ ቀን ወዳጆች መሆናቸው ይታወሳል። የዚያድባሬ ወራሪ መንግስት የውስጥ ክፍተቶችንና ዓለም አቀፍ ሁኔታውን ተመልክቶ የከፈተውን የግዛት ማስፋፋት ወረራ በአጭር ጊዜ ለመቀልበስ በተደረገው ርብርብና ተጋድሎ ከፍ ያለ ስፍራ እንደነበራቸው ይታወሳል።

ኢትዮጵያውያን እንደ አገር የመከዳት አደጋ ውስጥ በገቡባቸው ወቅቶች ሁሉ የሩሲያ ህዝብ እና መንግስት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ፈጥኖ በመድረስ ያሳዩትና ዛሬም እያሳዩት ያለው አጋርነት፤ ኢትዮጵያውያን በክፉ ቀናቶቻችው አጋር እንዳላቸው በእርግጠኝነት እንዲያስቡ አቅም እየሆናቸው መጥቷል።

ይህ የሩሲያ አጋርነት ከኢትዮጵያ አልፎ "ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄዎች በሚል "አፍሪካዊ መንፈስ ተላብሶ ብቅ ብሏል። ይህም ለመላው አፍሪካውያን እንደ አንድ ትልቅ የብስራት ዜና እየተቆጠረ ነው።

የሩሲያ አዲሱ አፍሪካዊ አጋርነት በርግጥም አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው የመፍታት አቅምና ብቃቱ እንዳለቸው ያመላከተና፤ ለረጅም ዘመናት ሰፍኖ የቆየውን ስለ አፍሪካና አፍሪካውያን ያለውን የተዛባ አመለካከት ማረቅ የሚያስችል እንደሆነም ይታመናል።

ይህ ኢትዮጵያዊም ሆነ አፍሪካዊ መንፈስ ያላቸው አፍሪካውያን በሙሉ የሚጋሩት መርህ፤ አፍሪካውያን ለችግሮቻቸው መፍትሄ ብቻ ሳሆን የችግሮቻቸውን እውነተኛ ምንጮች ተረድተው ቀጣይ እጣ ፈንታቸውን ብሩህ የሚያደርጉበትን ዕድል ሊፈጥር የሚችል መልካም አጋጣሚ ነው።

በቅኝ ገዥዎች ስለ አፍሪካና አፍሪካውያን ሲተረኩ የነበሩ የተዛቡ ትርክቶችን፤ ትርክቶቹ የወለዱትን የስነልቦና ጫናና ጫናው የፈጠረውን የማንነት




መደበላለቅ በማጥራት፤ አፍሪካውያን የእጣ ፈንታቸው ሰሪዎች መሆናቸውን የሚያመለክትም ነው።

ይህ የሩሲያ አጋርነት ይህን ትልቅና ለዘመናት የተደበቀን እውነት አደባባይ አውጥቶ አፍሪካን ወደ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ለመውሰድ የሚደረገውን ጥረት አቅም የሚያላብስ፤ ለመላው አፍሪካውያን እንደ አንድ ታሪካው ድል ተደርጎ ሊቆጠር የሚችል የ21ኛው ክፍለ ዘመን ስኬት ነው።

ዓለም ባልተገባ መልኩ በተዛቡ ትርክቶች ከተወሰደበት የተሳሳተ መንገድ መመለስ የሚያስችል፤ አፍሪካውያንም የበለጸገች አለም በመፍጠር ሂደት ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ እንዲወጡ በር ከፋች ነው።

በተለይም በቅኝ ግዛት ዘመን ቅኝ ገዥዎች አፍሪካውያን የጋራ እጣ ፈንታቸውን በጋራ እንዳይወስኑ፤ አገራትና ህዝቦች በጥርጣሬና በጠላትነት እንዲተያዩ የዘረጓቸውን ሴራዎች በጣጥሶ በመተማመንና በወንድማማችነት መንፈስ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እንዲከፍቱ ወሳኝ አቅምም ነው።

ይህን የሩሲያ ቀና መንገድ አለም አቀፉ ህብረተሰብ እንደ መልካም ተሞክሮ ሊወስደው፤ አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው የሚፈቱበትን አድል ሊያመቻቹ፤ ይህ እድል የበለጸገች አፍሪካን በመመስረት ሂደት ውስጥ አልፋና ኦሜጋ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ጉሮ ወሸባዬ ...

**ዘካሪያስ ዶቢ**

ኢትዮጵያውያን ከጥንት አንስቶ ለጀግኖቻቸው ታላቅ ክብር አላቸው። ይህንንም በተለያዩ መንገዶች ሲገልጹ ነው የኖሩት። በተለይ ለጀግኖች አትሌቶች የሚሰጠው ክብር ሁሌም ይታወሳል። ከሚሰጡት ልዩ ክብር አንዱ ድል አድርገው ሲመለሱ ደማቅ አቀባበል ማድረግና መሸለም ነው። ይህንንም ትናንት በደማቅ ስነስርአት ፈጽመውታል።

ኢትዮጵያውያንና መንግስታቸው በአሜሪካ ኦሬጎን በተካሄደው 18ኛው የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ተሳትፈው አንጸባራቂ ድል የተቀዳጁትን የአትሌቲክስ ጀግኖቻቸውን ጉሮ ወሸባዬ፣ ጉሮ ወሸባ፣ ዘማች ድል አድርጎ ሲገባ፣ እኛም ኮራን በናንተ፣ ወዘተ እያሉ በማዜም በደማቅ ስነስርአት ተቀብለዋቸዋል፤ ሽልማቶችም አበርክተውላቸዋል። አትሌቶቹ በተለይ ከትናንት በስትያ ሙሉ ቀኑን በአቀባበልና በሽልማት ስነስርአት ውስጥ ነው ያሳለፉት።

ህዝቡ በአዲስ አበባ ከተማ ዋና ዋና ጎዳናዎች ተገኝቶ ደማቅ አቀባባል አድርጎላቸዋል። መንግስት ደግሞ በብሄራዊ ቤተመንግስት ደማቅ አቀባበልና የሽልማት መርሀ ግብር አካሂዷል፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ሜዳሊያ ላስገኙት አትሌቶች ቦታ፣ ለልኡካን ቡድኑም 10 ሚሊዮን ብር ሸልሟል። በሁሉም በኩል የተካሄደው አቀባበልና ሽልማት በእጅጉ ደማቅና ክብሩን የሚመጥን ነው።

አትሌቶች ድሎችን አስመዝግበው በተመለሱ ቁጥር ደማቅ አቀባበሎች ሲደረጉላቸው ነው የኖሩት። የአሁኑ አቀባበል ግን በእጅጉ ደማቅና ታሪካዊ ሊባል የሚገባውም ነው። አቀባበሉም ሽልማቱም ድሉን የሚመጥን ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

መንግስት አደራ ሰጥቶ ወደ ውድድሩ ስፍራ እንደሸኘ ሁሉ ድል በድል ሆነው ለተለመሱት የአትሌቲክሱ ጀግኖች ደማቅ አቀባበልና ሽልማት አድርጓል። አትሌቶቹም አደራቸውን በሚገባ ተወጥተው መጥተዋል፤ ታላቅ ድል አስመዝግበው ነው የተመለሱት። ይህን ድል የሚመጥን ታላቅ ምስጋና ተደርጓል።

ኢትሌቶቹ አራት የወርቅ አራት የብርና ሁለት የነሀስ በአጠቃላይ አስር ሜዳሊያዎችን በማግኘት፣ ከአለም ከአማሪካ ቀጥሎ ሁለተኛ፣ ከአፍሪካ አንደኛ ሆነው በማሸነፍ አገራቸውንና ህዝባቸውን አኩርተዋልና አቀባበሉ በእርግጥም ይገባቸዋል። ድሉ ይህ ብቻም አይደለም፤ በአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ድል ከፍተኛው የተባለ የሜዳሊያዎች ብዛት የተመዘገበበት እንዲሁም ክብረወሰኖች የተሰባበሩበት ድልም ነውና አቀባበሉና ምስጋናው ድሉን የሚመጥን ከፍታው ከፍ ያለ ታሪካዊ ሊባል የሚገባውም ነው።

የኢትዮጵያ አትሌቶች በአንድነት ሆነው እየተናበቡ ነው ድል ሲያስመዘግቡ የኖሩት። ያ ታሪክ ዘንድሮም ተደግሟል። ይህ መሆኑም ኢትዮጵያ ተጨማሪ ሜዳሊያዎችን እንድታገኝ በር የከፈተ ታላቅ ስራ የታየበት ነው። ለአገር እንጂ ለግል ማንነት የሚደረግ ውድድር እንደሌለ በዚህ ሻምፒዮናም በሚገባ እንዲታይ አርገዋል።

የውድድሩ ወቅት በአገር ውስጥም በውጭ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የኢትዮጵያ ወዳጅ አገሮች ዜጎች ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ትስስር ጥንካሬ የታየበት ሆኗል፤ በእያንዳንዱ ውድድር ኢትዮጵያውያን አብረው ሮጠዋል፤ ሲያሸንፉም አብረው ፈንድቀዋል።

ይህ የአንድነትና ተናቦ ድል የማስመዝገብ ተግባር በተለይ አገሪቱ በምትገኝበት በዚህ የፈተና ወቅት ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው የማያስመዘግቡት ድል፣ የማይንዱት ተራራ እንደሌለ በሚገባ አመልክቷልና። የኢትዮጵያ አሸናፊነት የማይገሰስ፣ ሁሌም የሚኖር መሆኑን ለመላ አለም ጭምር መልእክት የተላለፈበት ነው። ኢትዮጵያ በተለያዩ መስኮች ወትሮውንም አሸናፊ ናት፤ ይህ ድል ደግሞ በጦር ሜዳ ውሎም በልማቱም መስከ እየተመዘገበ ካለው ድል ጋር ሲቀናጅ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን አሸናፊነትና ተሻጋሪነት ሌላ ጉልህ መገለጫ ይሆናል።

አቀባበሉም ሌላ የኢትዮጵያውያን አንድነት በጉልህ የታየበት ሆኗል። የኢትዮጵያውያን አንድነት ሌላ ማሳያ ትልቅ መድረክ መሆንም ችሏል። እንደዚህ አይነት መድረኮች ለጠላትም ለወዳጅም ከሚኖራቸው ትልቅ ፋይዳ አኳያ ኢትዮጵያን እናፈርሳለን ለሚሉት ጠላቶቿ መሪር መርዶ ይሆናል፤ ኢትዮጵያ የማትፈረስ ስለመሆኑ ሌላ ትልቅ ማሳያ ነውና፤ ለወዳጆቿ ደግሞ ይበልጥ አብረውን እንዲዘልቁ ማድረግ የሚያስችል አቅምን ይፈጥራል።

ይህን ታላቅ ድል ያስመዘገቡት አገር በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ በቆየችበት ወቅት እንደመሆኑም የአይበገሬነት መገለጫ ነው፤ እንደሚታወቀው አገራችን ባለፈው አንድ አመት ለብዙ ፈተናዎች ተዳርጋለች፤ ሁሉንም ግን በድል እየተወጣች ትገኛለች። በጦር ሜዳና በልማቱ መስክ እየታዩ ያሉት ታላላቅ ድሎች በፈተና ውስጥ ተሆኖም አገርን ማሻገር እንደሚቻል ያመላከቱ ናቸው። አገር ፈተናዎችን ወደ እድል እየቀየረች ነው እነዚህን ድሎች ያስመዘገበችው።

የስፖርቱም ዘርፍ በፈተናዎች ውስጥ ነው የሚገኘው። አትሌቶቹም በዚህ ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ሆና ነው አለምን ጭምር ያስደነቀ ድል ያስመዘገቡት። እንደሚታወቀው ስታዲዮሞቻችን የፊፋን ዝቅተኛ የአለም አቀፍ ስታዲየም መስፈርት አያሟሉም ተብለው ምንም አይነት አለም አቀፍ ጨዋታ እንዳያስተናግዱ በካፍ እገዳ ተጥሎባቸዋል። በዚህ የተነሳም ለአፍሪካ ዋንጫም ይሁን ለአለም ዋንጫ የሚደረጉ ማጣሪያዎችን በሌላ አገር ሜዳዎች ስታደርግ ቆይታለች። ስታዲዮሞቹ መመዘኛውን እንዲያሟሉ በሚል ለሚካሄድ እድሳት ተዘጋጅተዋል።

ይህ ሁኔታ እግር ኳሱን በአያሌው የጎዳ ቢሆንም፣ አትሌቲክሱም አልተጎዳም ተብሎ አይታሰብም። የትራክ ውድድሮችና ልምምዶች የሚካሄዱበት የአዲስ አበባ ስታዲየም ለእድሳት ከተዘጋ ከአመት በላይ ሆኖት አትሌቲክሱ አይጎዳም ተብሎ አይታሰብም!!

አትሌቶቹ ይህን ፈተና ሁሉ አልፈዋል። ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያን በእጅጉ ያኮሩት በእዚህ እና እንደ አገር ባሉ በርካታ ጫናዎች ውስጥ አልፈው ነውና ድላቸው የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን አይበገሬነት አሁንም ማሳየት ያስቻለ ታላቅ ድል ነው።

ኢትዮጵያውያን እነዚህን ጀግኖች ጎዳና ወጥተው በመቀበል ጉሮ ወሸባዬ..... እኛም ኮራን በናንተ... ወዘተ እያሉ በማዜም አቀባበል ማድረጋቸውና ምስጋናቸውን ማቅረባቸው መንግስትና የተለያዩ አካላት ሽልማቶችን መስጠታቸው ለድሉ የሚመጥን ታላቅ ምላሽ ተደርጎ ይወሰዳል። የቀደሙትን ድሎች ማሰብም ያስችላል፤ በቀጣይም የላቁ ድሎች እንዲመዘገቡ አደራ መስጠትም ይሆናል። አትሌቶች በአትሌትክሱ ዘርፍ ፍልሚያ ገጥማችሁ ድል በድል ሆናችሁ ተመልሳችሁዋልና ጀግኖች ናችሁ። እናም

ጉሮ ወሻባዬ ፣ ጉሮ ወሸባ ፣
ጉሮ ወሸባዬ፣ ጉሮ ወሸባ፣
ጉሮ ወሸባዬ ወሸባ

ዘማች ድል አድርጎ ሲገባ›› የሚለው ይመጥናችሁዋል፤ እንኳን ደስ አላችሁ፤ አንኳን ደስ አለን።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ህይወትን - በማምሻ ዕድሜ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ከአፋቸው አንድ ቃል ለማውጣት ሲታገሉ እንባቸው ኮለል ብሎ ይወርዳል። ተረጋግተው ለማውራት ይጀምራሉ። መልሶ ውስጣዊ ሀዘን ያሸንፋቸዋል። የፊታቸው ገጽታ መከፋታቸውን እያሳበቀ ነው። የሚተናነቃቸውን እንባ ለማገድ እየዋጡ ቃላት ከአንደበታቸው ለማውጣት ይሞክራሉ።

ብሶታቸውን ሸሽገው የውስጣቸውን ላለመተንፈስ ከራሳቸው ጠብ ይዘዋል። ቆይቶ ግን እጅ ሰጡ። ስንቱን ልንገርሽ ? በሚል አይነት የሆዳቸውን መዘርገፉን ተያያዙት። ብዙ ርቀት መሄድ አልቻሉም። ልማደኛው እንባቸው እየተንቆረቆረ ገደባቸው። በደቂቃዎች እፎይታ በራሳቸው ዝምታ ተዋጡ። ታገስናቸው። ጥበቃችን ያስጨነቃቸው ይመስላል። አረፍ እንዳሉ ንግግራቸውን ቀጠሉ።

### ልጅነቴ ማርናወተቴ የለም

ብርቄ ሙለታ በለምለሙ ተጂ አስጎሪ በቾ በምትባል ስፍራ ቢወለዱም ዕድገታቸው ግን በእናት አባት እጅ አልነበረም። ወላጆቻቸውን ነብስ ሳያውቁ ነበር ያጡዋቸው። ቆይቶም በአሳዳጊዎቻቸው ፈቃድና ይሁንታ እንዲያድጉ ሆነ። ብርቄ ልጅነታቸው እንደእኩዮቻቸው አልሆነም። ለምለሙን መሬት የቦረቁበት ለትንሽ ጊዜ ነበር ።

አሳዳጊዎቻቸው በእናትና አባታትነት ቢቀበሏቸውም ከልጅ እኩል የሚጫወቱበትን እድል አልሰጧቸውም። እናም ልጅነትን እንደፈለጉ ሳያጣጥሙ፣ ሳይቦርቁበት እንዲኖሩት ብቻ ተፈረደባቸው። በወቅቱ ባልጠና ጉልበታቸው ይህንን አድርጊ አይባሉም። ከፍ እስኪሉም ምንም ጎድሎባቸው አያውቅም። አሳዳጊዎቻቸው የምድሩ በረከት የተረፈላቸው ስለነበሩ በግብርናው ሲሳይ ከሚያገኙት ሁሉ ያቋድሷቸዋል። እነሱ ለልጅ ጣፋጭና ትዝታ ይሆናል ያሉትን ሁሉ ያደርጉላቸው ነበር። ከአንድ ነገር ውጪ። እርሱም አብዝቶ መጫወት ነው። ከልጆች እኩል እንዳም ብዙ ገደቦች ይጣልባቸዋል። የብርቄ ውሎ ብቸኝነት ነበርና የልጅነት ትዝታ የላቸውም። እናትና አባት እንደሌላቸው የሚሰማቸውም በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ነው። የወላጅን ፍቅር ባሰቡት ልክ አለማግኘታቸው ባይተዋርነት እንዲሰማቸው አድርጓል። ብርቄ ገና ልጅነታቸውን ሳይጠግቡ ባል እንዲያገቡ ሆነ። ትዳር መያዝ ጎጆ መውጣትን አልጠሉትም። አዲሱ ዓለም ህይወታቸውን ከብቸኝነት እንደሚታደግ አምነዋል።

### ባለትዳሯ ልጅ

ብርቄ ፍቅርን ከእናት አባት ቢያጡም ከባል አገኛለሁ የሚል ሀሳብ ነበራቸው። ትዳራቸው ጣዕም አልባ እንዳይሆን በጨቅላ አዕምሯቸው ብዙ ለፍተዋል። እንዳሰቡት አልሆነም። ነገሮች ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮደግፍ›› ሆኑባቸው። አባወራቸው መጀመሪያ ላይ ጎንበስቀና እንዳላለ ቆይቶ ‹‹ዓይንሽን ላፈር›› ወደማለቱ ገባ።

ምንክንያቱን በቀላሉ መረዳት አልቻሉም። ከአሳዳጊዎቻቸው ቤት መውጣታቸው አስቆጫቸው። በዚያ ቤት ብዙ ነገሮች ሙሉ ነበሩ። እዚህ ግን የሚጎድለው ይበዛል። በዚያ ላይ የዱላው ነገር።

ለሚሰሩት ተግባር ሁሉ ምክንያት ፈላጊው ባለቤታቸው ወጥቶ በገባ ቁጥር ይደበድባቸዋል። በማያባራ ለቅሶና ሰቀቀን አንገታቸውን ደፍተው ዓመታትን ተቀመጡ። ምርጫ ቢኖራቸው ቤተሰቤ የሚሏቸው ዘንድ ይመለሱ፣ አሊያም ሌላ ቦታ ይሄዱ ነበር። ይህን የሚያደርጉበት አቅም ላይ አልነበሩም። አሁን ይሆነኛል ያሉት ጎጆ ገሀነም ሆኖ እንዲኖሩበት ተገደዋል። ጠዋት ማታ በዕንባ ውለው ያደራሉ። ለትዳር ልጅ መሆናቸው ሳያንስ ዱላን ማስተናገዳቸው ውስጣቸውን ሰብሮታል።

ብርቄ በሀሳብ ይናውዛሉ። ምን ዘዴ መቀየስ እንዳለባቸው አልተረዱም። እናት አባቷን በሞት አጥታ በአሳዳጊዋ ግፊት ጎጆ እንድትወጣ የተፈረደባት ልጅ መድረሻ አይኖራትም። ነገሩን አምኖ ከመቀመጥ ውጪ። የዓመታት ዱላውን ታግሰው ጊዜ እስኪያልፍ ሲሉ ቆይተዋል።

የዱላው ብዛት ክፉኛ ጎድቷቸዋል። በታዳጊ እድሜያቸው አላምጠው እየዋጡ አይደለም። የላይኛው ጥርሳቸው በከፊል ረግፏል። ወገባቸውም ቢሆን ጉዳተኛ ነው። እንዲህ መሆኑ ጥረው ግረው ለራሳቸው እንዳይኖሩ ገድቧቸዋል። የዛኔው ብርቱ ዱላ ዛሬን ዋጋ አስከፍሏቸዋል። በስቃይ ከዘለቀ ህመም ጋር እየኖሩ ነው። ያም ሆኖ ‹‹አምላክ ባይረዳኝ፣ በሕይወት አልወጣም›› ይላሉ የባለቤታቸውን ድርጊትና የደረሰባቸውን ስቃይ ሲያወሱ። ብርቄ የልጅነት ትዳራቸው አልዘለቀም። ስቃዩ ማቄን ጨርቄን ሳይሉ ቀዬአቸውን ለቀው ጠፉ።

### ትንሿ ሰራተኛ

በባላቸው ምሬት አዲስ አበባን የተቀላቀሉት ወይዘሮ ከተማዋ እንዳሰቡት አልሆነችላቸውም። የሚያውቁት ሰው የለም፤ የሚያርፉበትም ቤት እንዲሁ። መንከራተትና መሳቀቅ የቀናት ጉዟቸው ሆነ። ደጋግ ሰዎች ግን አላጡም። ‹‹ሳይደግስ አይጣላ›› እንዲሉ ሆኖ የሚጠጉበት ሰው አገኙ። ይህ ደግሞ ያልጠነከረው ጉልበት እንዲበረታ፣ በዱላ የጎበጠው ወገብ እንዲቃና፣ ተስፋና እድል ሰጣቸው። መስራትና መለወጥን ተመኙ።

ብርቄ ወገባቸውን ታጥቀው ለስራ ሮጡ። ከእንግዲህ ማንም እንደሌላቸው አውቀዋልና ራሳቸውን ለመቻል ታገሉ። እናት አባት፣ እህት ወንድም፣ የቅርብ ወዳጅና ዘመድ በሌለበት ያገኙትን ዘመድ የማድረግ ውዴታ ግዴታቸው ሆኖ ጎንበስ ቀናውን ጀመሩት። ከእዚህ በኋላ የራሳቸው ብርታት ራሳቸው ብቻ መሆናቸውን አምነዋል። ቢወድቁ መነሳት፣ ቢረቱ ተስፋ ባለመቁረጥ በርትቶ መቆም እንዳለባቸው ቆርጠዋል። አሁን በጎ አድራጊዋን እናት ተመርኩዘው በእርሳቸው ቤት እያደሩ ኑሯቸውን ቀጥለዋል።

የኑሯቸው መግፊያ አማራጭ የጉልት ላይ ሥራ ሆኖ ቆይቷል። ሽንኩርት፣ ቲማቲምና ጎመን ኑሯቸውን ማጣፈጫና የገቢ ምንጫቸው ሆነውላቸዋል። በወዝ በላባቸው የሚያድሩበትን ሥራ በማግኘታቸውም ወጣትነታቸውን እንዲያስቡት፣ ያለፉበትን እንዳይረሱት ሆነዋል። ይህ በዚህ ከቀጠለ ኑሯቸው እንደሚቀየር፣ ሕይወታቸው እንደሚሻሻል አምነዋል።

ሁለተኛው ቤታቸው ከዚህ የተሻለና በዘመድ የታጠረ ነበር። የቆዩበትን አመስግነው ሲወጡ ብዙ አልተከፉም። አዲሱ ቤት ከአካባቢያቸው የመጣችና ዘመዴ የሚሏት መሪም ቤት ነው። በእሷ ቤት ሳሉ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተምረዋል። አንዳቸው ለሌላቸው የሚያሳዩት መተሳሰብ ከልብ የመነጨ ነበር። ከእርሷ ጋር ሲኖሩ ከተለያዩ ሥራዎች ተገኝተዋል። በተለይ በቀላሉ ሰርተው የገቢ ምንጭ ያገኙበት እንጀራና አንባሻ ጋግሮ መሸጥ ዋነኛው ተግባራቸው ነበር። በሚያገኙት ገቢ ሁልጊዜ ደስተኛ ነበሩ። ቤታቸው ሙሉ ሆኖ ለሌላ አስኪተርፉ አትርፈዋል።

ብርቄ ሁሌም የተሻለውን ይዘው ሥራቸውን ማስፋት ያልማሉ። በወቅቱ ደግሞ ውጤታማ ሆነዋል። ይህ ሙከራ ግን እስከ መጨረሻው አልቀጠለም። እናት አባታቸውን የነጠቃቸው ሞት ዛሬም ከበራቸው ደርሶ ጓዳቸውን አንኳኳ። እናት፣ እህትና መካሪ የሆነቻቸውን ደጓን መሪም ወሰደባቸው።

ለእሳቸው ከእርሷ ሌላ ማንም አልነበራቸውም። እህትነትን ዝምድናን ያወቁባት፤ መተሳሰብን ያዩባት ነበረች። ከእርሷ የቀረበ ዘመድ አያውቁም። ድንገቴው ሞቷ ባዶነታቸው ዳግም መለሰባቸው። ‹‹አለችኝ›› የሚሏትን እስከመጨረሻው ሲለዩዋት ሰማዩ ተደፋባቸው። ውስጣቸው እንዳይሆን ሆኖ ተሰበረ።

ከማንም ጋር ስላልነበሩና ብቻቸውን ስለቀሩ የሚያደርጉት ግራ ገባቸው። ዘመድ አዝማድ በሌለበት ሕይወትን መምራት በእጅጉ ከበዳቸው። በዚህም አዲስ አበባ መኖር አስጠላቸውና ባህር ማዶን ተመኙ፤ ተሳካላቸው።

### ኑሮ በአረብ አገር

ጊዜው ውጪ አገር መሄድ ቀን ያወጣል፣ ብር ያሳፍሳል የሚባልበት ነበር። በዚህ ወቅት በተለይ አረብ አገር ሄደው የተመለሱ ጥቂቶች በብዙ መልኩ ተለውጠው ታይተዋል። ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለዘመድ አዝማዱም ሲተርፉ ተስተውሏል።

ይህ አይነቱ እውነት ያስቀናቸው የትናንቷ ወጣት ይሻላልን መርጠው ባህር ማዶ ተሻገሩ። አረብ አገርን ‹‹አገሬ›› አሉ። ረጅም ዓመታትን በዚያው አሳለፉ። በዓመታት ቆይታና ልፋታቸው ግን አንድም ጠብ ያደረጉት ጥሪት ሳይኖር ባከነ። የያዙት ወርቅ፣ የቋጠሩት ገንዘብ አልነበረም። የተሰቃዩበትንና ያላቸውን ገንዘብ ጨረሱ። አንድ ቀን ደግሞ ከተለየ ምሬትና ሀዘናቸው ጋር ባዶ ሻንጣቸውን ይዘው አገራቸው ተመለሱ።

በአረብ አገር ህይወት ያላሰቡትን በሽታ ሸምተዋል። ችግርን አይተዋል። በልፋት ብቻ የታጠረ ኑሮን የተስፋ መቁረጥ ቆይታን አሳልፈዋል። አገር የሌለው ሰው ማለት ምን እንደሚመስል አይተዋል። ጥቂት ልረፍት፣ ልተኛ የማይባልበት ቤት መኖርን አይተዋል። ወጥቶ መግባትን፣ በሰላም ውሎ ማደርን፣ በወጉ መተንፈስን ናፍቀዋል። በመጨረሻ ህወታቸውን አትርፈው ‹‹ የአገሬ ሰው ይብላኝ፣ ይግደለኝ›› ብለው ባዶ እጃቸውን ሲገቡ በምስጋና የአገራቸውን መሬት ለመሳም በቅተዋል።

### ንፍሮ ነጋዴዋ

አሁን ብርቄ ከአረብ አገር አሰስከፊ ህይወት አምልጠው ለእናት ምድራቸው በቅተዋል። በአገር ቤት አዲስ አየር፣ አዲስ ሰላምና ተስፋ እንዳለ እየተሰማቸው ነው። ምንም ይሆን ሰርተው እንደሚያድሩ ያውቃሉ። እናት ምድራቸውን ሲረግጡ አፈሯን የመሳማቸው ምስጢር ይህ ነበር። በእርግጥ አገርቤት ሲገቡ ሁሉ ነገር ተለውጧል። በአደራ የተሰጠው ቤት ጭምር ከቦታው የለም። የትናንቱ ትናንት ሆኖ አልፏል። የሚያርፉበትን ቤት ጭምር ነጥቀዋቸዋል። ያም ሆኖ አልከፋቸውም። ዛሬ አይዞሽ፣ አለንሽ የሚላቸው የአገር ሰው ጋር ናቸው። የሚያስጠጋ፣ የሚያስጠልላቸው አያጡም።

ደርሶ የሚሰማቸው ህመም ጤና ቢነሳቸውም አንድም ቀን ተኝተውለት አያውቁም። እጅ አይሰጡትም። ከበሽታቸው እየታገሉ ኑሯቸውን ይገፋሉ። ሕመም ቢጠናባቸው እንኳን ደፋ ቀና ማለታቸውን አይተውም። ቢያንስ ጦም አያሳድረኝም ከሚሉት ሥራ ይውላሉ። አንባሻና እንጀራ እየጋገሩ ይሸጣሉ። በሚያገኙት ገንዘብ ለተጠጉበት ቤት ክፍያና ለአንዳንድ ነገሮች ይደጉማሉ።

በሽታው ፋታ ሲሰጣቸው ደግሞ አለፍ ካለ ሥራ ይገኛሉ። በተመላላሽ ሰራተኝነት ልብስ ያጥባሉ፣ እንጀራ ይጋግራሉ፤ ልጆችን ይንከባከባሉ። ፒያሳ አካባቢ ባለ ዳቦ ቤት ይሰራሉ። ለሰባት ዓመታት ሌሊት 11 ሰዓት እየወጡ ሲሰሩ ጎን ለጎን በዳቦ መጋገር ሥራ ሰርተፍኬት ጭምር አግኝተዋል።

ከዚያ ሲያልፉ ደግሞ መሳለሚያ አካባቢ ከሚገኝ ፋርማሲ በጽዳት ሥራ ተሰማርተው አገልግለዋል። ሥራው ግማሽ ቀን በመሆኑ ግማሽ ቀኑን ለሌላ ሥራ ያውሉታል። ትርፍ ቀናቸውን ለተጨማሪ የሰው ቤት ሥራዎች ማዋል ልማዳቸው ሆኖ ዘልቋል። አንዳንዴ ተስፋን የሚያጨልሙ ነገሮች በሕይወት ውስጥ ማጋጠማቸው አይቀርም። በዚህ ታታሪነታቸው መሀል ትልቅ ጋሬጣ ተደነቀረባቸው። ፋርማሲው በመንገድ ግንባታ ምክንያት ፈርሶ ሥራቸው ተቋረጠ። ብርቄ ዕድሜያቸው ቢገፋም መሥራት እንጂ መቀመጥን አያውቁም። መልሰው ለራሳቸው ሥራ ፈጠሩ።

ትኩስ ንፍሮዋቸውን ቀቅለው፣ ጠዋት፣ ማታ ገበያ ይዘው ይወጣሉ። እንዲያ ቢያደርጉም ብርዱና በሽታቸው አልስማማ ብለው አወኳቸው። ውጋት፣ ቁርጥማቱ አላስቀምጥ አላቸው። በስቃይ መሀል ሆነው እንጀራቸውን አከበሩት ሳያቋርጡ በስራው ገፉበት።

ብርቄ ለኑሮና ህይወታቸው የሚደርስላቸው የለም። ጦም ላለማደር በርሀብ ላለሞት እስከመጨረሻው ይታገላሉ። ለጎናቸው ማረፊያ ቤትን አላጡም። ይህ ባይሆን ችግራቸው ልቆ በእስተርጅና የጎዳና ተዳዳሪ ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ደግነቱ እነ አቶ በቀለ ጉርማን ጥሎላቸው ሊኖር ከሚችል አሳዛኝ ህይወት ተረፉ።

### አዛውንቷ ዛሬ

ወይዘሮ ብርቄ ዛሬ በአዲስ ከተማ ክፍለከተማ ወረዳ አራት 01 ቀበሌ በእነ አቶ በቀለ ቤት ተጠልለው ይኖራሉ። እሳቸው ቤት የገቡት በሰራተኝነት ነበር። ይሁን እንጂ ሁሉም አግብተው በመውጣታቸውና አስጠጊያቸው በመታመማቸው ከቤት ቀሩ። ብርቄ ለዚህ ቤተሰብ የተለየ ቅርበት አላቸው። ልጆቹን አሳድገው፣ ድረው ኩለዋል።

አሁን ማንም እሳቸውን ሊያስወጣ አይሻም። ዛሬን የልጅ ልጆችን እየተንከባከቡ እንዲኖሩ ተፈቅዶላቸዋል። ባለቤቱ በቤት ውስጥ ባይኖሩም ቤታቸውን እንደራሳቸው እንደሚጠብቁ ያውቃሉና ‹‹ኑሪበት፣ እረፊበት›› ብለዋቸዋል። የቤቱ ባለቤት በጎነት ቢኖርም የእርሳቸው ካጠገባቸው ያለመኖር ብዙ አጉድሎባቸዋል። ቤቱ አሁንም ቤተሰብ የሞላበት በመሆኑ ጠማቸውን አያድሩም፤ ለወጪውና ለዕለት ጉርስም ተጨንቀው አያውቁም። እንደዛሬው አንዳንዴ ግን ነገሮች ድብልቅልቅ ይሉባቸዋል። በቤቱ የቱን ሸፍነው የቱን እንደሚተውት ያስባሉ። የቤት ኪራይ ባይከፍሉም ኑሮ ከዕድሜ ተዳምሮ ህይወት ከብዷቸዋል። መስራትና ገቢ ማግኘት ግዴታቸው እንደሆነ ቢረዱም የአቅማቸው ማነስ ከበሽታው አላንቀሳቅስ ብሏቸዋል። ዳቦ ቤት በሚሰሩ ጊዜ ወድቀው የተሰበረው እግራቸው ዛሬን እንደልብ አላላውሰ እያላቸው ነው። ከአደጋው በኋላም በእግራቸው ጉዳት ምክንያ ትስራ የሚቀጥራቸው ሳያገኙ ቆይተዋል።


ባሉበት ቤት እንጀራና ዳቦ ቢጋግሩና እንደቀድሞው ቢሸጡ ይመርጣሉ። ይህን ለማድረግ ግን ለመብራት ክፍያው አቅም የላቸውም። ይህ ችግር እንጀራ ጋግረው እንደይበሉ ጭምር ፈተና ሆኗል። በዚህ ምክንያት የእለት ጉርሳቸው በዳቦ ይሸፈናል። እሳቸው ግን አሁንም አርቀው ያስባሉ። የተሻለ ገቢ ካገኙ ዳቦውን ወደ እንጀራ ያሳድጉታል። ይህ የሚሆነው የሚሸጡት ንፍሮ ከቲፑ ተዳምሮ ጥሩ ካገኙ ነው።

አሁን ብርቄ በሴፍትኔት መርሀግብር የቀጥታ ተረጂ ናቸው። በወር 700 ብር ያገኛሉ። ይሁንና በዚህ ገቢ ብቻ ኑሮን መግፋት ከብዷቸዋል። ብርቱዋ ወይዘሮ ደጋግመው ‹‹ለእኔ የሚሆን ሥራ ካላችሁ እባካችሁ ታደጉኝ›› ይላሉ። እኛም በጎ ማድረግ የሻቱ ሁሉ ቀርበው እንባቸውን ያብሱላቸው ዘንድ ታሪካቸውን ወደ እናንተ አድርሰናል።



ፎቶ፡- እዮብ ተፈራ

# ስፖርት



## ከማራቶን ጀግኖቹ አንደበት

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና መወዳደር የጀመረችው ከመነሻው መሆኑን ሰነዶች ያሳያሉ። የፊንላንዷ ሄልሲንኪ እአአ 1983 ባዘጋጀችው የመጀመሪያው ቻምፒዮና ላይም ከአምስቱ ውድድሮች በማራቶን አትሌት ከበደ ባልቻ ባስመዘገበው ብቸኛው የብር ሜዳሊያ ኢትዮጵያ ከዓለም 15ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀችው። ከሩጫ ውድድሮች ሁሉ ረጅሙና ከፍተኛ ጥንካሬን በሚጠይቀው በዚህ ርቀት በድጋሚ ድል ለማስመዝገብም ሰባት ቻምፒዮናዎችን መታገስ ነበረባት።

እአአ በ2001 ኤድመንተን ላይ የምርጥ ማራቶን አትሌቶች መፍለቂያ የሆነችው ኢትዮጵያ አትሌት ገዛኸኝ አበራ ባጠለቀው የወርቅ ሜዳሊያ በርቀቱ ሁለተኛው ሆኖ ተመዘገበ። እስካሁን በተካሄዱት 18 ቻምፒዮናዎችም በአጠቃላይ ኢትዮጵያ 15 ሜዳሊያዎች (5 የወርቅ፣ 6 የብር እና 4 የነሃስ) ሲኖሯት፤ ከእነዚህ መካከል 12 የሚሆኑትን በማስመዝገብ ወንድ አትሌቶች የበላይነቱን ይይዛሉ።

የበዛ ጽናትን በሚፈልገውና እልህ አስጨራሽ በሆነው የማራቶን ውድድር፤ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በተጠናቀቀው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናም 3 ሜዳሊያዎችን በሁለቱም ጾታ በማስመዝገብ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን ደረጃ ልትይዝ ችላለች። በወንዶች በኩል አትሌት ታምራት ቶላ እና ሞስነት ገረመው ተከታትለው በመግባት የወርቅና ብር ሜዳሊያዎቹን ሲያጠልቁ፤ በሴቶች ደግሞ ብቸኛዋ እንቁ አትሌት ጎተይቶም ገብረስላሴ ወርቁን በእጇ በማስገባት ቻምፒዮን ሆናለች።





የማራቶን ባለድሎቹ አትሌት ታምራት ቶላና ሞስነት ገረመው በቀጣይ ለሌላ ድል መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል፣

በዚህ ርቀት በተለይ በወንዶቹ በኩል ተከታታይ ድል ሲገኝ (በዶሃ እና ኦሪጎን ቻምፒዮናዎች የወርቅና ብር ሜዳሊያዎች)፤ የኦሪጎኑን ጨምሮ በአምስት ተከታታይ ቻምፒዮናዎች ላይ ደግሞ አምስት የብር ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ የሚፎካከራት የለም። ይህም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በመድረኩ ባስቆጠረቻቸው ሜዳሊያዎች ብዛት ኬንያን ተከትላ በሁለተኛነት ትቀመጣለች። በዚህ ስኬት ውስጥ ከፍተኛ ስኬት ያላቸው አትሌቶች ደግሞ ታምራት ቶላ እና ሞስነት ገረመው ናቸው። ሞስነት ሁለት የብር ሜዳሊያዎችን ሲወስድ፤ ታምራት ደግሞ የወርቅና የብር ሜዳሊያዎችን በማግኘት የጀግንነት ገድሉን ከሌላኛው አትሌት ሌሊሳ ዴሲሳ ጋር ይጋራል።

የዚህ ክብር ባለቤት እንዲሁም ኦሪጎን ላይ ከአሸናፊነት ባለፈ የቻምፒዮናውን ክብረወሰን ያሻሻለው አትሌት ታምራት ቶላ፤ ለኦሪጎኑ አጠቃላይ ድል አስቀድሞ ለኢትዮጵያ ህዝብ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክቱን ይገልጻል። በማስከተልም «ሰው በሚሰራበት ነገር ላይ ስኬታማ ለመሆን ጥረት ያደርጋል፤ እኛም ወደ ኦሪጎን የሄድነው ለዚሁ ሲሆን ስኬታማም ሆነናል። በዚህ የዓለም ቻምፒዮና ክብረወሰን መስበር ብቻም ሳይሆን ማሸነፍ በራሱ ትልቅ ነገር ነው። ከቡድኑ አባላት ጋር በጋራ በሰራነው ስራ ይህ ውጤት ሊመዘገብ ችሏል። ለዚህም የአትሌቲክስ ፌዴሬሽናችንን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉን፣ አሰልጣኞቻችንን እንዲሁም ከእኛ ጋር የነበሩትን ሁሉ ላመሰግን እወዳለሁ» ብሏል።

የሪዮ ኦሊምፒክ የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤቱ ታምራት የስኬቱ ምስጢር ከአምስት ዓመት በፊት እአአ በ2017 በተካሄደው የለንደን ዓለም ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ ማስመዝገቡን ተከትሎ በቀጣይ ወርቅ ማምጣት እንዳለበት በማመን ጠንክሮ በመስራቱ እንዲሁም በወቅቱ የሰራቸውን ስህተቶች በማረሙ እንደሆነም ይናገራል። እንዳሰበውም ተሳክቶለት የወርቅ ሜዳሊያውን ማጥለቅ በመቻሉ ደስተኛ ሆኗል። ቀጣይ ዕቅዱም ከሁለት ዓመት በኋላ በሚካሄደው የፓሪሱ ኦሊምፒክ ለአገሩ ተመሳሳይ ስኬት ማስመዝገብ መሆኑንም አመላክቷል።

የኦሪገኑ የማራቶን ውድድር ፈታኝ እንደነበር የሚገልጸው የብር ሜዳሊያ ባለቤትና ሌላኛው የኢትዮጵያዊያን የኩራት ምንጭ የሆነው አትሌት ሞስነት ገረመው፣ በዓለም ላይ ፈጣን እና ምርጥ ከሆኑ የማራቶን ሯጮች መካከል በቀዳሚነት ይቀመጣል። በኦሪጎን ከጓደኞቹ ጋር በመሆን አገሩን ቀዳሚ ለማድረግ አቅዶ በተጓዘው መሰረት ውጤታማ መሆን ችሏል።

ፈታኝ የነበረውን ውድድርም በድል በማጠናቀቅ ቡድኑ ከዓለም ሁለተኛ ከአፍሪካ አንደኛ ሆኖ በማጠናቀቁ ደስተኛ መሆኑን ጠቅሶ ለኢትዮጵያ ህዝብም የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክቱን አስተላልፏል። በሁለቱም ጾታ በዚህ ርቀት ውጤት እንዲገኝ ምክንያት የሆነው በቡድን ተሳስቦ መስራትና በቡድኑ ውስጥ በነበረው ፍቅር መሆኑንም ይገልጻል። የማራቶን ቡድኑ ወደ ኦሪጎን ከመጓዙ አስቀድሞ በርቀቱ ውጤት መምጣት እንዳለበት በተነጋገረው መሰረት ስኬታማ መሆን እንደቻሉም አትሌቱ አስረድቷል።


## የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

የባለንብረቱ ስም መሃመድ ከድር የሰሌዳ ቁጥር 1-10225 ደ/ህ ተሽከርካሪ ባጃጅ የሻንሲ ቁጥር MD2A25BZBEWC96320 ሞዴል RE-45 የሞተር ቁጥር AZZWEC45034 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ታርጋ 1-10225 ደ/ህ ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በቁጥር 1366/ጉዞፖ/15/42 በቀን 4/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል:: ታርጋውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማሳገጃ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን::

**በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክስላዊ መንግስት የጉራጌ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

## ኦሮሚያ ክልል

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-92743 ኦሮ የሆነ ሰሌዳ ጠፍቶብኛል ብለው ባለንብረቱ አቶ ፈይሶ ሀጅ በቀን 06/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል:: በዚሁ መሰረት ሰሌዳውን ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማስረጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን::

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የምዕራብ አርሲ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን**

ንብረትነቱ ቤኛ አሼ ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥር 2 ኦሮ- 1705076 የሆነ የተሽከርካሪ ሰሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለፅ ሌላ በምትክ እንዲሰጣቸው ጠይቀውናል:: በመሆኑም ሰሌዳውን ወድቆ ፣ተሰርቆ በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃውን ትእዛዝ ይዞ እንዲቀርቡ እያሳወቅን ይህ ካልሆነ ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን::

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባለስልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በአመልካች አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም እና በተጠሪ የሐንስ አዲስ መኮንን መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 5ኛ ፍ/ር ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልስዎን በጽሁፍ ለ27/11/2014 ዓ.ም በ4:00 ሰዓት ይዘው እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል::

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች አይናለም ወይንሸት ሲሳይ እና ጓደኞቻቸው የብሎኬት ማምረት የህ/ሽ/ማ እና በተከሳሾች/በተጠሪዎች 1. አቶ ዳንኤል አልታዬ አሳምነው 2. አቶ በለጠ ጀምበሬ 3. ወ/ሮ ብርሃኔ ማሞ ተ/ሃይማኖት 4. ወ/ሮ ወይንሸት ታደሰ 5. አቶ ባህሩ አወል 6. ወ/ሮ ወይንሸት የይ ሀይሌ 7. ወ/ሮ በላይነሽ አልታዬ አሳምነው መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ኢንቨስትመንት ምድብ 4ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች/ተጠሪዎች ለ29/11/2014 ዓ.ም በ4:05 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርብ ፍርድ ቤቱ አዟል::

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ሙሴ ኃ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-79159 የተሽከርካሪው አይነት ሻወር ትራክ የሻንሲ ቁጥር WJME3TRS40C314049 ሞዴል AT380T38H የሞተር ቁጥር F3BEE681G*B220-237059* የሊብሬ ቁጥር 0127463 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ14/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የን/ስ/ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አሸናፊ ግደይ መረሳ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B44595 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር LLV2A3A24A0217592 ሞዴል LF7162E የሞተር ቁጥር LF481Q3*101201876* የሊብሬ ቁጥር 378375 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ14/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአ/ቃልቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አቤኔዘር ተፈሪ አሰፋ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-08924 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር TT0466-03 ሞዴል TT0466-03 የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0264247 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ13/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም እዮብ ደስታ በረከት የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B00093 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JTDBW23E253066212 ሞዴል NZE120L-AEPDKV የሞተር ቁጥር 1NZ-A085103 የሊብሬ ቁጥር 582675 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ13/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሰሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የን/ስ/ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዘላለም ጌታነህ አያሌው የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-38775 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5CLSB08A327484 ሞዴል ZZ425753241V የሞተር ቁጥር 07120742779F የሊብሬ ቁጥር 0095309/0284642 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ12/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአ/ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሲ እና ኢ ወንድማማቾች የብረት ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-84176 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር MROFR22GXC0677925 ሞዴል KUN25L-PRMDHV የሞተር ቁጥር 2KD-5691276 የሊብሬ ቁጥር 190095 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ12/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል:: ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአ/ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

በአመልካች አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም እና በተጠሪ ሺጋነህ አያሌው መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልስዎን በጽሁፍ ለ29/11/2014 ዓ.ም በ8:00 ሰዓት ይዘው እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል::

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**